# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 219 ሚያዝያ 9 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# መንግሥት የኑሮ ውድነትና የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ለመቅረፍ ተጨባጭ እርምጃ እየወሰደ ነው

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በአገሪቱ የሚስተዋለውን የኑሮ ውድነትና የውጭ ምንዛሬ እጥረት ለመቅረፍ መንግሥት ተጨባጭ እርምጃ እየወሰደ መሆኑ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ነመራ ገበየሁ ገለጹ፡፡

ዶክተር ነመራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ ለኢኮኖሚ እድገቱ ተግዳሮት የሆነውን የውጭ ምንዛሬ እጥረት ለመፍታት መንግሥት ከዚህ ቀደም ባልተለመደ መልኩ ስንዴና ሌሎች አዳዲስ ምርቶችን ለውጭ ገበያ ማቅረብ ጀምሯል፡፡ ኢትዮጵያ ቀደም ሲል ስንዴን ከውጭ ለማስገባት ታወጣ የነበረውን የውጭ ምንዛሬ ማስቀረት ተችሏል፡፡ የተለያዩ አለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅቶችም ከኢትዮጵያ ስንዴን በውጭ ምንዛሬ መሸመት ላይ ናቸው፡፡

መንግሥት የውጭ ምንዛሬን ለማመንጨት ከስንዴ በተጨማሪ ሌሎች አዳዲስ ምርቶችን ወደ አለም ገበያ ለመላክ ይሰራል ያሉት ዶክተር ነመራ፤ በተመሳሳይ መልኩ የቱሪዝም መዳረሻዎችን ለማስፋት ዓባይ ግድብን ጨምሮ እንደ ጎርጎራ፣ኮይሻና ወንጪ ያሉ አገራዊ

መንግሥት የኑሮ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ዶክተር ነመራ ገበየሁ



## “ልዩ ኃይልን መልሶ ማደራጀት ሠራዊቱን ከማጠናከሩም ባሻገር በብሔር ተዋፅዖ ምልዑ እንዲሆን ያደርገዋል”

-ብርጋዴር ጄነራል አሰፋ አእፈሮም

**ውብሸት ሰንደቁ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ልዩ ኃይልን መልሶ ማደራጀት ሠራዊቱን ከማጠናከሩም ባሻገር የሰራዊቱን የብሔር ተዋፅዖ ምሉዕ እንዲሆን ያደርገዋል ሲሉ የቀድሞው የመከላከያ ሠራዊት አባል ብርጋዴር ጄነራል አሰፋ አዕፈሮም ገለጹ፡፡

ብርጋዴር ጄነራል አሰፋ አዕፈሮም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ሁሉንም የሚወክል ሠራዊት ሊኖራት ይገባል፡፡ ለዚህም ልዩ ኃይልን መልሶ የማደራጀት ሥራው የክልሎች ልዩ ኃይሎች ወደ ሰራዊቱ

«ልዩ ኃይልን ... ወደ ገጽ 2 ዞሯል

## "ከፈንታሌ-ኤርታሌ" ፕሮጀክት ለሀገር የሚተርፍ ገቢ የመፍጠር አቅም አለው

**ጌትነት ተስፋማርያም**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የገበታ ለትውልድ ፕሮጀክት አካል የሆነው "ከፈንታሌ-ኤርታሌ" የቱሪዝም መስህብ ልማት ከአፋር አልፎ ለሀገርም የሚተርፍ ገቢ የመፍጠር አቅም እንዳለው የአፋር ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ አስታወቀ።

የአፋር ክልል ኮሙኒኬሽን ምክትል ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሐዋ አሊ አቡበከር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ መነሻነት በአፋር ክልል ተግባራዊ የሚደረግ ከፈንታሌ-ኤርታሌ የገበታ ለትውልድ ፕሮጀክት ተግባራዊ ይደረጋል።

የገበታ ለትውልድ ፕሮጀክቱ ከፈንታሌ አካባቢ ተነስቶ እስከ ኤርታሌ የሚደርስና በርካታ ስፍራዎችን የሚያጠቃልል የቱሪዝም ፕሮጀክት መሆኑን ወይዘሮ ሐዋ አስታውቀዋል።

"ከፈንታሴ -ኤርታሴ" ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል














“የደረቅ ወደብ ማስፋፊያው ከታቀደ አምስት አመታት ቢያልፉም እስካሁን ግንባታው አልተጀመረም”

- የኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር

“የተጋነነ የመሬት ካሳ ክፍያ በመጠየቁ ግንባታውን መጀመር አልቻልኩም”

- የኢትዮጵያ ባህር፣ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ

ገጽ 4







# የከተማ አስተዳደሩ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል እየሰራ ነው

**ገመቹ ከድር**

አሰላ፡- በከተማዋ የነበሩ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን ለማስተካከል በርካታ ርምጃዎች መወሰዳቸውን የአሰላ ከተማ ከንቲባ ገለጹ:: ከፍተኛ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር በታየባቸው 14 ተቋማት የማስተካከያ እርምጃ ተወስዷል ብለዋል::

የአሰላ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ጋዛሊ ሀሹ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የከተማውን አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል ከፍተኛ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር በታየባቸው 14 የመንግስት ተቋማት የማስተካከያ ርምጃ ተወስዷል:: ከስራ ማሰናበት፣ ከደረጃ ዝቅ ማድረግ ፣ ለህግ ማቅረብ ፣ ከሃምሳ በላይ በሚሆኑ ሰራተኞች ላይ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያና ሌሎች አስተዳደራዊ ርምጃዎች ተወስዷል::

ለአረንጓዴ ልማት በተለያዩ ቦታዎችና ወንዞች ዳርቻ በተገነቡ 400 ህገወጥ ግንባታዎች ላይ በተወሰደው ማስተካከያ እርምጃ ሰባት ሄክታር መሬት ወደ መሬት ባንክ ተመልሷል ያሉት ከንቲባው፤ ከጉዳዩ ጋር ንክኪ የነበራቸው አርባ አምስት ሰዎች በገንዘብና እስራት እንዲቀጡ መደረጉን ጠቁመው፤ ወደፊት በተመሳሳይ ሁኔታ የሃብት ብክነት እንዳይከሰት ግንዛቤ የማስጨበጥ



ፎቶ - ገበቦ ገብሬ

**የአሰላ ከተማ ከንቲባ አቶ ጋዛሊ ሀሹ**

ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ገልጸዋል::

እንደ አቶ ጋዛሊ ገለጻ፤ የተወሰዱ እርምጃዎችን ተከትሎ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱን በዘላቂነት ለማሻሻል የሚያስችሉ የተለያዩ አቅጣጫዎችና ፕሮግራሞች ተግባራዊ ተደርጓል:: ሰኞ ፣ረቡዕ እና ዓርብ በቋሚነት ባለ ጉዳዮች የሚስተናገዱባቸው ቀናት ተደርጓል:: ከዚህም በተጨማሪ ተገልጋዮች ባሉበት ቦታ ሆነው አስፈላጊውን መረጃ እንዲያገኙ ለማድረግ በከተማው የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከኅገል ጋር ተያይዟል:: አመራር አካላት ባሉበት ቦታ ሆነው አገልግሎት አሰጣጥ ሂደቶችን ለመከታተል የሚያስችሉ ሴኩዩሪቲ ካሜራዎች ተገጥመዋል::

በተጨማሪም ከንቲባ ችሎት በሚባል ፕሮግራም ሃሙስ እለት ባለጉዳይና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አንድ ላይ እንዲመጡ በማድረግ አፋጣኝ ምላሽ እየተሰጠ ነው ብለዋል::

እስከ አሁን ድረስ በተወሰዱ እርምጃዎችና ተግባራዊ በተደረጉ ፕሮግራሞች አገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱ ከበፊቱ አንጻር መሻሻል ማሳየቱን ገልጸው፤ በዘላቂነት አገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋ ለማድረግ በትኩረት እየተሰራ ነው ብለዋል::

በአገልግሎት አሰጣጥ መሻሻል ቅሬታ አይኖርም ማለት አይደለም ያሉት አቶ ጋዛሊ፤ ጊዜ የሚጠይቁ የከተማዋ ችግሮች በተለይ የውሃ አቅርቦት ችግሮችን ለመፍታት በአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር የውሃ ፕሮጀክት በመገንባት ላይ መሆኑን ጠቁመው፤ ሆኖም ፕሮጀክቱ በግንባታ መሳሪያዎች ዋጋ ንረት ተጓቷል ሲሉ ጠቅሰዋል::

ስንዴ ምርት ለውጪ ገበያ ለማቅረብ በተጀመረው እንቅስቃሴ ህገወጥ ነጋዴዎችን ለመቆጣጠር በተደረገው ቁጥጥር ሂደት በተፈጠሩ ችግሮች ከአርሶ አደሩ ወደ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች በሚፈለገው መጠን ለገበያ ባለመቅረቡ ኑሮ ውድነት አስከትሏል ያሉት ከንቲባው፤ ይህ ደግሞ በከተማ ነዋሪዎች ላይ ተፅዕኖ መፍጠሩን ገልጸው፤ ከዩኒየን ማህበራት እና ከግብርና ጽህፈት ቤት ጋር በመነጋገር መፍትሄ እንደተሰጠው ገልጸዋል::

ከንቲባ ጋዛሊ፤ በስራ ዕድል ፈጠራና በአረንጓዴ አሻራ ልማት በከተማው ሰፊ ስራዎች መሰራታቸውን አያይዘው ገልጸዋል:: እስከ አሁን ድረስ በተሰሩ ስራ እድል ፈጠራ ስራዎች ለ15ሺህ ዜጎች ስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል:: ከተማዋን ጽዱና ውብ ለማድረግ በአረንጓዴ አሻራ ልማት መርሀ ግብር አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ችግኞች ተተክለው 98 ፐርሰንቱ ጸድቀዋል:: ለዘንድሮ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ ችግኞች በመዘጋጀት ላይ ይገኛሉ ሲሉም ገልጸዋል::

ከተማ ልማት ፣ መሬት አስተዳደር ፣ ትራንስፖርት ጽህፈት ቤት ፣ አሰላ ከተማ መጠጥ አገልግሎት ፣ አሰላ ከተማ አስተዳደር ፣ ንግድ ፣ ኢንቨስትመንትና ገቢዎች ማስተካከያ እርምጃ ተወስዶ መሻሻል ከታየባቸው ተቋማት ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውንም ከንቲባው ጠቁመዋል::

# የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ማዕከል ግንባታ በቅርቡ ይጠናቀቃል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የሚገኘው የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ማቋቋሚያ የእንስሳት እርባታና ተዋጽዖ ማዕከል ግንባታ በቅርቡ እንደሚጠናቀቅ የመዲናዋ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ብዙአየሁ ጉታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ኮዬ ፈቼ የጋራ መኖሪያ አካባቢ በ14 ሄክታር መሬት ላይ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ማዕከል እየተገነባ ነው፡፡ ይህ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ማቋቋሚያ የእንስሳት እርባታና ተዋጽዖ ማዕከል ግንባታ በቅርቡ ይጠናቀቃል፡፡

ማዕከሉ ለሁለት ሺህ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች የስራ ዕድል የሚፈጥር መሆኑን የገለጹት አቶ ብዙአየሁ፤ ፕሮጀክቱ ከ800 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት ተይዞለት የግንባታው አፈፃጸም 95 በመቶ መድረሱን አብራርተዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ ማዕከሉ በውስጡ በ80



ብሎኮች፤ አስር የዶሮ ዕርባታ ሼዶች፤ 10 የወተት ላሞች ሼዶች፤ 10 የስጋ ከብቶች ማደለቢያ ሼዶች የተገነቡለት ሲሆን፤ ተዋፅኦውን ለማቅረቢያና ለመሸጫ የሚሆኑ 32 ሱቆችን በውስጡ ይዟል።

ፕሮጀክቱ ከ800 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት እንደተያዘለት ያብራሩት አቶ ብዙአየሁ፤ የዶሮ ሼዶቹ እያንዳንዳቸው አራት ሺህ ዶሮዎችን የመያዝ አቅም አላቸው ሲሉ ጠቅሰዋል።

የላሞቹ ሼዶች እያንዳንዳቸው ሠላሳ ላሞችን እንደሚይዙና የስጋ ከብቶች ማደለቢያ ሼዶች ደግሞ እያንዳንዳቸው ሠላሳ የቀንድ ከብቶችን የሚይዙ መሆኑን አብራርተዋል።

ከዚህም በተጨማሪ የአስተዳደር ሕንፃዎች፤ የእንስሳት መኖ ማዘጋጃና ማከማቻ፤ የእንስሳት ክሊኒክ እንዲሁም ለማህበራቱ በቢሮነት የሚያገለግሉ ክፍሎች እንደተሟሉ ጠቅሰው፤ የማዕከሉ ግንባታ ከዚህ በፊት ለሙከራ በተገነባው የእንስሳት እርባታ እና ተዋጽዖ ቦታ ላይ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ይህም የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት እና የከተማዋን ነዋሪ የእንስሳት ተዋፅኦ ፍላጎት ለማርካት ጉልህ ሚና አለው ብለዋል።

እንደ አቶ ብዙአየሁ ገለፃ፤ ፕሮጀክቱ የሚፈልገው ከፍተኛ መጠን ያለው የውሃ አቅርቦትን ከግምት በማስገባት 300 ሜትር ኪዩብ ውሀ የመያዝ አቅም ያለው ሪዘርቫየር ተገንብቶ ተጠናቋል፡፡ ከእንስሳቱ የሚወጣው እዳሪ በተዘጋጀለት መውረጃ ሄዶ ለባዮ ጋዝ በመዋል ማዕከሉ የኃይል ፍላጎቱን ከራሱ እንዲያገኝ የሚያስችል ስራ ጎን ለጎን እየተከናወነ ይገኛል፡፡

የማዕከሉን ግንባታ የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ በባለቤትነት እንዲሁም የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን በስራ ተቋራጭነት ይዘውታል።

# የሳይበር ጥቃት ለቀጣናው ሀገራት ከፍተኛ ስጋት ሆኗል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የሳይበር ጥቃት ለምስራቅ አፍሪካ ቀጣና ሀገራት ከፍተኛ የደህንነት ስጋት መሆኑን የፌዴራል ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ቢሮ አስታወቀ:: የምስራቅ አፍሪካ ፖሊስ አዛዦች ህብረት ድርጅት (EAPCCO) ጉባኤውን በአዲስ አበባ ከሚያዝያ 3 ቀን እስከ ሚያዝያ 5 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ አካሂዷል።

በወቅቱ የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ጠቅላይ መምሪያ የፎረንሲክ ምርመራ ምክትል ዋና መምሪያ ኃላፊ ረዳት ኮሚሽነር ከተማ ደባልቄ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በምስራቅ አፍሪካ ቀጣና የሳይበር ጥቃት ወንጀሎች እየተበራከቱ ይገኛሉ።

አብዛኛዎቹ ድንበር ዘለል ወንጀሎች ላይ ምርመራ በሚደረግበት ጊዜ ወንጀሎቹ ከሳይበር ጥቃት ጋር ግንኙነት አላቸው ያሉት ረዳት ኮሚሽነሩ፤ የሳይበር ጥቃትን መከላከል የሚቻልባቸው መንገዶችን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባ አመላክተዋል።

ችግሩ ቢጠናከርም ቀደም ባሉ ጊዜያት በምስራቅ አፍሪካ ፖሊስ ኮሚሽኖች የጋራ ስብሰባ ላይ የሳይበር ጥቃት እንደ አጀንዳ እንደማይያዝ አስታውሰዋል።

አሁን ላይ ግን በመዲናዋ በተደረገው ጉባኤ ላይ የሳይበር ጥቃት የመከላከል ጉዳይ አስፈላጊነቱ ታምኖበት እራሱን የቻለ ኮሚቴ እንዲዋቀርለት ተደርጓል ብለዋል።

የቀጣናው ሀገራት በዘርፉ ባለሙያ በማብቃት፣አስፈላጊ ቁሳቁሶች በማሟላት እንዲሁም የልምድ ልውውጥ በማድረግ ወንጀሉን በጋራ ለመከላከል የሚያስችል ኮሚቴ ማዋቀራቸው ችግሩን ለመከላከል የሚደረገውን የጋራ ጥረት የሚያጠናክር መሆኑን ጠቁመዋል።

ረዳት ኮምሽነሩ እንዳስታወቁት፤ ኢትዮጵያም በዘርፉ ያለውን የባለሙያዎች ክህሎት በማሳደግና የሳይበር ጥቃትን በመከላከል የበኩሏን ሚና እየተወጣች ይገኛል።

ቀጣይነት ባለው መልኩ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ማዘመንና የሰው ኃይልን ማብቃት ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ያሉ ክፍተቶችን ለመሙላት በትኩረት እየሰራን ነው ብለዋል::



ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች በሳይበር ወንጀል ምርመራ ላይ ተጨማሪ ስልጠና እንዲያገኙ ወደ ደቡብ ኮሪያ ለመላክ ዝግጅት ተደርጓል። የቴክኖሎጂ መሳሪያ እጥረቱን ለማቃለል ከቻይና መንግስት ጋር በቅርበት እየተሰራ ይገኛል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ጠቅላይ መምሪያ ኃላፊ ምክትል ኮምሽነር ጀነራል ዘላለም መንግስቴ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በምስራቅ አፍሪካ ቀጣና የሳይበር ጥቃት፣ ሽብርተኝነት፣የአደንዛዥ ዕፅ ወንጀሎች እንዲሁም ህገወጥ የሰዎችና የጦር መሳሪያ ዝውውር በጋራ መከላከል የተቀናጀ ስራ እየተከናወነ ይገኛል።

የምስራቅ አፍሪካ ፖሊስ አዛዦች ህብረት ድርጅት ጉባኤ ሲካሄድ አባል ሀገራቱ በሳይበር ደህንነትና ወንጀል መከላከል ዘርፎች ያላቸውን ልምድ ተለዋውጠዋል።

የወቅቱ ምስራቅ አፍሪካ ፖሊስ አዛዦች ህብረት ድርጅት ፕሬዚዳንት የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ጀነራል ደመላሽ ገብረሚካኤል መሆናቸው ይታወቃል።

ዜና



ዶክተር ጴጥሮስ ወልደጊዮርጊስ

## ቦንጋ ዩኒቨርሲቲ ለመጀመሪያ ጊዜ ተማሪዎችን በቡና ሳይንስ ሊያስመርቅ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በ2015 የትምህርት ዘመን መጨረሻ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ 37 ተማሪዎችን በቡና ሳይንስ የትምህርት መስክ እንደሚያስመርቅ ቦንጋ ዩንቨርሲቲ አስታወቀ። ዩኒቨርሲቲው ካለው 200 ሄክታር መሬት ውስጥ በ150 ሄክታሩ ላይ የግብርና ምርቶችን እያከናወነ መሆኑ ተገልጿል።

የቦንጋ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ጴጥሮስ ወልደጊዮርጊስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የቡና ምርት ኢትዮጵያ ትልቁ የውጭ ምንዛሬ የምታገኝበት ሸቀጥ በመሆኑ በ2015 ዓ.ም መጨረሻ 37 ተማሪዎችን በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በቡና ሳይንስ የትምህርት መስክ ይመረቃሉ፡፡

ኢትዮጵያ ቡናን ለዓለም ያበረከተች ሀገር ብትሆንም እስካሁን ድረስ የቡና ትምህርት መስክ ብቁ ባለሙያዎችን ማፍራት አዳጋች ሆኖ ነበር ያሉት ዶክተር ጴጥሮስ፤ የቦንጋ ዩኒቨርሲቲ ሴኔት የቡና ሳይንስ ትምህርት ክፍል እራሱን ችሎ በ2012 ዓ.ም እንዲከፈት ማድረጉን ተናግረዋል፡፡

በቡና ምርት ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመመርመር ከዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆን ቡናን በትምህርትና ምርምር አስደግፎ ለመምራት ዩኒቨርሲቲው በመጀመሪያና በሁለተኛ ዲግሪ የቡና ሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርት ክፍል በማቋቋም ተማሪዎችን እያስተማረ መሆኑን አስታውቀዋል።

በሚቀጥለው ዓመት በሁለተኛ ዲግሪ በቡና ሳይንስ ተማሪዎች የሚመረቁ ሲሆን፤ ዩኒቨርሲቲው በቀጣይ ጊዜትም የቡና ሳይንስ ትምህርት መስከን በዶክትሬት ዲግሪ ደረጃ ማስተማር እንደሚጀምር ዶክተር ጴጥሮስ ጠቁመዋል፡፡

ስለ ቡና ታሪክና ተክል እንኳን በተግባር የተደገፈ ልምድ መስጠት የማይችሉ የሌሎች ሀገራት ዩኒቨርሲቲዎች በድፍረት ስለ ቡና ሳይንስ እያስተማሩ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የቡና መገኛ በሆነችው ኢትዮጵያ ሳይንሱ እንደ አንድ የትምህርት ዘርፍ ሳይሰጥ መቆየቱን ጠቁመው፤ በቦንጋ ዩኒቨርሲቲ ትምህርቱ መጀመሩ የሀገሪቷን የቡና ተጠቃሚነትን የሚያሳድግና በኢኮኖሚ ላይ ትልቅ አቅምን የሚፈጥር ነው ሲሉ አስረድተዋል።

ከርዳታ ጥገኝነት ለመላቀቅ እንደ ቡና ያሉ ምርቶችን በትምህርትና ምርምር አስደግፎ መምራት ያስፈልጋል ብለዋል።

በመሆኑም ቦንጋ ዩኒቨርሲቲ ችግሩን ለመፍታት በቡና ላይ ትኩረቱን አድርጎ የሚሰራ በሀገር ደረጃ የመጀመሪያ የሆነው የቡና ሳይንስ የትምህርት ክፍል በማቋቋም ተማሪዎችን በማስተማር ላይ መሆኑን ገልጸዋል።

በዚህም ረገድ በአካባቢው ያለውን ሀብት እንዴት መጠቀም እንደሚቻል፣ ማህበረሰቡን በሰፊው ተጠቃሚ ለማድረግና በስራ ላይ ሊገጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶች ላይ ሰፊ ጥናት መደረጉን አብራርተዋል፡፡

የትምህርትን ጥራት ለማረጋገጥ ዋናው መንገድ ጽንሰ ሃሳብን ወደ ተግባር መለወጥ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ለዚህም እንዲረዳ በዩኒቨርሲቲው ግቢ በ82 ነጥብ 3 ሄክታር መሬት ላይ የቡና እርሻ እንደሚገኝ ገልፀዋል።

ቦንጋ ዩኒቨርስቲ ካለው 200 ሄክታር ለተለያዩ ግንባታዎች የሚውለውን 50 ሄክታር በመለየት በተቀረው 150 ሄክታሩ ላይ ቡና፣ ማንጎ፣ አቦካዶ፣ አናናስ፣ ፓፓያ፣ ሙዝ፣ ቅመማቅመም፣ አፐልና እንሰት ምርቶችን በስፋት በማምረት እየሰራ ይገኛል ብለዋል።

ምርቶቹን ወደ አግሮ ኢንዱስትሪ በመቀየር ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለመተካት እንደታሰበም ፕሬዚዳንቱ ጠቁመዋል፡፡

እ.ኤ.አ. በ2030 ቦንጋ ዩኒቨርሲቲ በተፈጥሮ ሀብት አያያዝና አጠቃቀም በአፍሪካ ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባር ቀደም የመሆን ራዕይን ይዞ እየተንቀሳቀሰ እንደሆነ ገልጸው፤ ዩኒቨርሲቲው ከመማር ማስተማር በተጨማሪ በግብርናና በማህበረሰብ አቀፍ ተግባራት እንደሚሳተፍ ዶክተር ጴጥሮስ ተናግረዋል፡፡

# በ12 የግል የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ላይ ርምጃ ተወሰደ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስምንት ወራት በአዳዲስ የግል የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ላይ በተደረገ ድንገተኛ ፍተሻ ህግ ተላልፈው በተገኙ የ12 የግል የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ላይ እርምጃ መወሰዱን የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን አስታወቀ፡፡ 68 የግል የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተላለፈባቸውን የእርምት እርምጃ ወደ ጎን በመተው እየሰሩ መገኘታቸው ተጠቁሟል፡፡

የኢፌዴሪ ትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን የተቋማት ቁጥጥርና የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጥ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ቸሩጌታ ገነነ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተገኘን መረጃ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥና መቆጣጠር ከተሰጡት ተልዕኮዎች መካከል ናቸው፡፡ ከዚህ ቀደም በትምህርት ስርዓቱ ላይ አገር የገባችበትን አሳሳቢ ሁኔታ በሚመጥን መልኩ የተሰራ ስራ ብዙም አልነበረም፡፡ ስለዚህ ችግሩን ባገናዘበ መልኩ ተቋሙ ራሱን በአዲስ አደረጃጀት የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ እየሰራ ነው፡፡

ባለስልጣኑ በግል የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ላይ የሚያደርገውን ቁጥጥር አጠናክሮ መቀጠሉን የገለጹት ምክትል ዋና ዳሬክተሩ፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ በተያዘው አመት ብቻ 132 በሚደርሱ አዳዲስ የግል የከፍተኛ የትምህር ተቋማት ላይ ድንገተኛ ፍተሻ ተደርጓል፡፡ በፍተሻው ከተሰጣቸው ፈቃድ ውጪ ህግን ተላልፈው በተገኙ ተቋማት ላይ የእርምት እርምጃ ተወስዶባቸዋል ብለዋል፡፡



ቸሩጌታ ገነነ

አብዛኛዎቹ ስህተታቸውን እንዲያስተካክሉ ሲደረጉ ፍተሻ ከተደረገባቸው የግል የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ላይ 12 የሚሆኑት የተቋም መዝጋት፤ ፕሮግራም መዝጋትና ሌሎች ከፍተኛ ርምጃዎች ተወስደውባቸዋልም ብለዋል፡፡

በቁጥጥር ስራው ላይ ከዚህ በፊት የነበረው ትልቅ ክፍተት የህግ ጥሰት ፈጽመው የነበሩ ተቋማት የተሰጣቸው የእርምት ርምጃ ማስተካከላቸውን የማረጋገጥ ውስንነት ነበር፡፡ ተቋማት ውሳኔውን ተፈጻሚ ማድረግና አለማድረጋቸው ማረጋገጫ አልነበረም፡፡ ውሳኔ ከተወሰነ በኋላ ኮሌጆቹ ኃላፊነት የሚሰማቸው ሲያስተካክሉ ኃላፊነት የማይሰማቸው ደግሞ ሳያስተካክሉ ሊቀጥሉ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ተቋማቱ በተሰጣቸው ውሳኔ መሰረት ማስተካከላቸውን ለማረጋገጥ የፍተሻ ስራ ተሰርቷል ሲሉም አስረድተዋል፡፡

ከ244ቱ ተቋማት በ138 ላይ የተላለፈባቸውን የእርምት ርምጃ ተግባራዊ ማድረግና አለማድረጋቸውን ፍተሻ ተደርጎ ግማሽ የሚሆኑት ሲያስተካክሉ ሌሎቹ 68 የሚሆኑት የተሰጣቸውን ማስተካከያ ችላ ብለው በጥፋታቸው ቀጥለው መገኘታቸውን ምክትል ዳይሬክተሩ ተናግረዋል፡፡

የተቋማቱን ጥፋት ህብረተሰቡ እንዲያውቅ በማድረግ ጠንካራ ርምጃ ለመውሰድ ዝግጅት የተደረገ ስለመሆኑ የገለጹት አቶ ቸሩጌታ፤ የህግ ተፈጻሚነትን ከማስፋት አንጻር ከባለድርሻ አካላት ጋር አብሮ መስራት አስፈላጊ ነው፡፡ በየቀኑ የሚስተዋሉትን ጉዳዮች መረጃ በመለዋወጥ አብሮ በመስራት በትምህርት ስርዓቱ የሚፈጸመን ህገ ወጥነትን መከላከል አስፈላጊ ነው፤ ስለሆነም ከክልል ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እንሰራለን ብለዋል፡፡

# በክልሉ የበጋ መስኖ ሥራ 170 ሺህ ሄክታር የሚጠጋ መሬት በዘር ተሸፍኗል

## - በበጋ መስኖ ስንዴ ከ748ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በክልሉ ለማልማት ከታቀደው 208ሺህ ሄክታር መሬት እስካሁን ድረስ 170 ሺህ ሄክታር የሚጠጋው መሬት በዘር መሸፈኑን የደቡብ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ። 20ሺህ ሔክታር መሬትን በበጋ ስንዴ በማልማት 748ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ለመሰብሰብ እየተሰራ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

በደቡብ ክልል በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የገጠር ክላስተር አስተባባሪና የክልሉ ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡስማን ሱሩር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልል በበጋ መስኖ ለማልማት ከታቀደው 208ሺህ ሄክታር መሬት ውስጥ እስካሁን ድረስ 80በመቶ በዘር መሸፈን ተችሏል። ከጥር አንድ እስከ አስር ቀን 2015ዓ.ም ባለ ጊዜ ውስጥም የዘር ስራ ለማጠናቀቅ የድጋፍና ክትትል ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡

በዘንድሮው በበጋ መስኖ ከሚለማው መሬት ውስጥ 188ሺህ ሄክታሩ መሬት ላይ የሚለሙት አትክልት፣ ፍራፍሬና የተለያዩ ሰብሎች መሆናቸውን ገልጸው፤በክልሉ በበጋ ስንዴ 20ሺህ ሔክታር መሬት በማልማት 748ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ለመሰብሰብ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በበጋ ስንዴ ልማት ከሚሸፈነው 20ሺ ሄክታር ውስጥ እስካሁን ከ9ሺህ 500 ሔክታር መሬት በላይ በስንዴ ዘር እንደተሸፈነ አመልክተው፤የተሻለ ምርት ማግኘትም 90 በመቶ የሚሆነውን መሬት ትራክተር በመጠቀም የእርሻ ዝግጅት መደረጉንና እንደ አካባቢው ሁኔታ ተስማሚ የሆነ ማዳበሪያና ምርጥ ዘር መጠቀም መቻሉን ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ ኡስማን ገለጻ፤ የበጋ ስንዴ ልማት በክልል እና በሀገር ደረጃ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ከፍተኛ ፋይዳ አለው፡፡እንዲሁም ከአገር ውስጥ ፍጆታ የተረፈውን ምርት ለውጭ ገበያ በማቅረብም የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ያስችላል፡፡



አቶ ኡስማን ሱሩር

በበጋ መስኖ ልማት ምርታማነትን የሚቀንሱ ችግሮችን በመለየት መፍትሄ ለመስጠት በትኩረት እየተሰራ ነው ያሉት አቶ ኡስማን፤ በክልሉ ለመስኖ ልማት የሚሆኑ የውሃ ምንጮች ለማስፋት አነስተኛ ጉድጓድ ቆፍረው በሚያለሙ አካባቢዎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የውሃ መሳቢያ ፓምፖች በማዳረስ ረገድ ውጤታማ ስራዎች መሰራታቸውን ጠቅሰዋል፡፡

ሆኖም የነዳጅ እጥረት በማጋጠሙ አርሶ አደሮቹ የነዳጅ ጥያቄ በማንሳታቸው በየደረጃው ካለው አመራር ጋር በመነጋገር ችግሩን ለመፍታት እየተሰራ እንደሆነ ኃላፊው ጠቁመዋል።

እየተካሄደ ባለው የበጋ መስኖ ልማትም በህብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ መነቃቃት መፍጠሩን ያነሱት አቶ ኡስማን፤ በበጋ መስኖ ልማትም ወጣቶች፣ ሴቶችና ከስደት የተመለሱ ዜጎች በቡድን በመደራጀት ወደ ስራ እንዲገቡ መደረጉን ተናግረዋል፡፡

የበጋ መስኖ ልማቱም ትኩረት ተሰጥቶት በማህበረሰብ ንቅናቄ እየተመራ በአመራሩና ሙያተኛው ድጋፍ እየተሰጠ የሚያጋጥሙ ችግሮች ወዲያው እየተፈቱና በቁርጠኝነት እየተሰራ እንደሆነ ገልፀዋል።

የበጋ መስኖ ልማት ካስገኛቸው ጠቀሜታዎች አንዱ አርሶ አደሩ ተጨማሪ ገቢ እንዲያገኝና ጊዜውን በአግባቡ ለልማት እንዲያውል ማድረጉን አመልክተዋል፡፡

ከታህሳስ እስከ የካቲት ወራት ባለ ጊዜ ውስጥ ምርት የሚሰበሰብበትና ምርቱ ገበያ ላይ የሚሸጥበት ወቅት በመሆኑ ብዙ አርሶ አደሮች ምርት በመሸጥ ገንዘብ የሚያባክኑበት ጊዜ እንደሆነ የገለፁት አቶ ኡስማን፤ አሁን ግን ያ ቀርቶ በማሳ እንዲውሉና ገንዘባቸውን ካላስፈላጊ ወጪ እንዲቆጠቡ ምቹ አጋጣሚ መፈጠሩን ጠቁመዋል ።

የክልሉ የበጋ መስኖ ልማትን ከሁሉም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት ወደ ተግባር እንደተገባ አቶ ኡስማን አስታውሰዋል።

# “የደረቅ ወደብ ማስፋፊያው ከታቀደ አምስት አመታት ቢያልፉም እስካሁን ግንባታው አልተጀመረም”

- የኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር

# “የተጋነነ የመሬት ካሳ ክፍያ በመጠየቁ ግንባታውን መጀመር አልቻልኩም”

- የኢትዮጵያ ባህር፣ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አዲስ አበባ፡- የኮምቦልቻ ደረቅ ወደብ ማስፋፊያ ግንባታ ከታቀደ ከአምስት ዓመታት በላይ ቢሆንም ግንባታው እስካሁን አለመጀመሩን የከተማ አስተዳደሩ አስታወቀ። የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ በበኩሉ፤ የተጋነነ የመሬት ካሳ ክፍያ ግንባታው እንዳይጀመር እንቅፋት መሆኑን ጠቁሟል።

የኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር ዋና ከንቲባ መሀመድ አሚን የሱፍ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የኮምቦልቻ ደረቅ ወደብ ለከተማው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ የሚያስገኝ ማስፋፊያ ፕሮጀክት ቢሆንም ግንባታው እስካሁን አልተጀመረም።

የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ለኮምቦልቻ ደረቅ ወደብ ማስፋፊያ ግንባታ የመረጠው ቦታ አርሶ አደሮች በመስኖ የሚያለሙበት በመሆኑ ለ25 ሄክታር መሬት 525 ሚሊዮን ብር በካሳ መመሪያው መሰረት እንዲከፍል መጠየቁን አንስተዋል።

ድርጅቱ የካሳ ክፍያው እንደበዛበት በመግለጹ ከተማ አስተዳደሩ ይህንን በመረዳት ለግንባታ ከተመረጠው ቦታ በቅርብ ርቀት የሚገኙ እና የካሳ ክፍያቸው ያነሰ ሦስት አማራጭ ቦታዎችን ማዘጋጀቱን ተናግረዋል።

ነገር ግን የባህር፣ ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አማራጭ ቦታዎችን ለመውሰድ ፍቃደኛ አይደሉም ብለዋል።

አገልግሎቱ ለካሳ ክፍያ የቀረበልኝ የብር መጠን ከፍተኛ ነው ብሏል ያሉት ከንቲባው፤ ጉዳዩ የአርሶ አደሩ መብት ቢሆንም ጥያቄው ከከተማ አስተዳደሩ ስልጣን በላይ በመሆኑ አስተዳደሩ የሚፈታው አይደለም ብለዋል።

የኮምቦልቻ ደረቅ ወደብ ማስፋፊያ ግንባታ እንዲገነባ ከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ ፍላጎት አለው ያሉት ከንቲባው፤ ነገር ግን የአርሶ አደሩን እና የአገልግሎቱን ፍላጎት ማጣጣም አልተቻለም። በዚህም የኮምቦልቻ ደረቅ ወደብ ማስፋፊያ ግንባታ ሳይጀመር ቀርቷል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ በበኩሉ፤ “የተጋነነ የመሬት ካሳ ክፍያ በመጠየቁ የኮምቦልቻ ደረቅ ወደብ ማስፋፊያ ግንባታን መጀመር አልቻልኩም” ብሏል።

በኢትዮጵያ ባህር፣ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ የወደብና ተርሚናል አገልግሎት ዘርፍ ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ምህረተአብ ተክሉ እንደተናገሩት፤ የኮምቦልቻ ደረቅ ወደብ ማስፋፊያ ግንባታ ለመስራት ከታቀደ አምስት ዓመት አልፎታል። ሶስት ዓመታት በጀት ተመድቦለት ግንባታው አልተጀመረም። ለማስተር ፕላን፣ ለአዋጭነት ጥናትና የመጀመሪያ ደረጃ ግንባታ ለማከናወን ከ150 ሚሊዮን ብር በላይ ተመድቦለታል። አጠቃላይ ግንባታው ከ500 ሚሊዮን ብር በላይ ይፈጃል።

ያም ሆኖ ግን ለተመረጠው ቦታ የተጠየቅነው ካሳ ተገቢ አይደለም። ምክንያቱም የካሳ ክፍያው የቦታውን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም።

አቶ ምህረተአብ እንዳሉት፤ በአንድ በኩል ቦታው የመስኖ ቦታ ነው ይባላል እንጂ በቦታው ምንም አይነት የውሃ ጥርቅም የለም። ሁለተኛ በዓመት ሦስት ጊዜ ይለማል ይባል እንጂ ትክክለኛ የሆነ መረጃ የለውም ብለዋል።

የኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር በኢትዮጵያ ባህር፣ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት በጠየቀው መሰረት ሌላ አማራጭ ማቅረቡን ገልጸው፤ ነገር ግን ቦታዎቹ ኮምቦልቻን ከሚያቋርጠው የባቡር ሃዲድ ርቀው የሚገኙ ናቸው ብለዋል።

በተጨማሪም በአማራጭነት የቀረቡት ቦታዎች ላይ ደረቅ ወደብ ለመገንባት ከፍተኛ የሆነ ወጪ ይጠይቃል። ከዚህም ባለፈ በከተማ አስተዳደሩ የሚደረገው ተደጋጋሚ የኃላፊዎች ለውጥ ለግንባታው እንቅፋት ሆኗል ብለዋል።

ከዚህ በፊት ኮምቦልቻ ድርጅቱ የሚገለገልበት ደረቅ ወደብ የነበረ መሆኑን ተናግረው፤ ሆኖም ደረቅ ወደቡ በቤቶች የተከበበና የተሟላ መሠረተ ልማት የሌለው እንደሆነ ገልጸዋል።

# መንግሥት የኑሮ ውድነትና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ፕሮጀክቶች ግንባታቸው እየተፋጠነ መሆኑንና ይህም

ሌላኛው የውጭ ምንዛሬ መገኛ መንገዶች መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡

ምንም እንኳ ፕሮጀክቶቹ የውጭ ምንዛሬ ለማመንጨት የየራሳቸው አቅም ቢኖራቸውም የአገሪቱን የማስፈጸም አቅም፣ፕሮጀክቶቹ የሚያመነጩትን ገቢና የሚፈጥሩትን የሥራ እድል ታሳቢ በማድረግ ግንባታቸው በቅደም ተከተል የሚከናወን ይሆናል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የፕሮጀክቶቹ ግንባታ ሲጠናቀቅ በሀይል ማመንጨትና በቱሪዝም ዘርም የሚያስገኙት የዉጭ ምንዛሬ ትልቅ አቅም እንደሚፈጥር አስገንዝበዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በተደረገው የኢኮኖሚ ሪፎርም ለዘመናት በመንግሥት ብቻ ተይዘው የነበሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን በከፊል ወደ ግሉ ሴክተር የማዞር እንቅስቃሴ የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ለመቅረፍ ብሎም ለኢኮኖሚው እድገት ትልቅ ጅማሮ መሆኑን ያብራሩት ዶክተር ነመራ፤ ከዚህ አንጻር የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች ተሳተፎ እያደረጉ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ መንግሥት የኑሮ ውድነቱን ለመግታት ሰፋፊ እንቅስቃሴ እያደረገ ነው ያሉት ሚኒስትር ደኤታው፤ በአንድ በኩል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ለግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ከመቼውም ጊዜ በላይ ትኩረት መስጠቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ምንም እንኳ ክፍተቶች ቢኖሩትም አሁን ያለው ምርት በፍትሐዊት ለሸማቹ ሕብረተሰብ እንዲደርስ አበረታች ጅምሮች መኖራቸውን ተናግረዋል፡፡

ኑሮ ውድነቱ አሁን በድንገት የተከሰተ ጉዳይ ሳይሆን የአለም አቀፋዊና የአገራዊ ምክንያቶች ውጤት መሆኑ መታወቅ አለበት ያሉት ዶክተር ነመራ፤ በአገር የሰሜን ጦርነት፣በአለም የሩሲያና ዩክሬን እንዲሁም የኮረና ወረርሽኝ አሁን በተፈጠረው የኑሮ ውድነት ትልቁ መንስኤ እንደሆነ አንስተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚም ከአለም ገበያ ተጽዕኖ ውጪ ባይሆንም በንግድ ሥርዓቱ ላይ የሚስተዋለውን ችግር ለመፍታት ጥረት ከማድረግ በተጓዳኝ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ልዩ ትኩረት ስለተሰጠ፣ ችግሩ በዘላቂነት እንደማይቀጥልም ጠቁመዋል፡፡

# “ልዩ ኃይልን መልሶ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንዲቀላቀሉ በማድረግ ሰራዊቱን ከማጠናከሩም ባሻገር የሰራዊቱን የብሔር ተዋፅዖ ምሉዕ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

የክልል ልዩ ኃይል የሚባለው አካል የኢትዮጵያን ሰራዊት የሚገዳደር እስከመሆን ድረስ በመፍረጠም ኢትዮጵያን አደጋ ላይ እስከ መጣል የደረሰበት ጊዜ እንደነበር ያስታወሱት ብርጋዴር ጄነራሉ፤ ልዩ ኃይል የሚባለው አካል በክፉ ጊዜ ኢትዮጵያን የታደገ መሆኑ መረሳት የለበትም ብለዋል፡፡

የክልል ልዩ ኃይል የሚባለው ህጋዊ መሰረት የሌለው መሆኑን ገልጸው፤ ክልሎች የራሳቸውን ልዩ ኃይል እየመለመሉ እና እያስታጠቁ መምጣታቸው እንዲፈረጥሙ አድርጓቸዋል ብለዋል፡፡ በዚህም ፀረ ኢትዮጵያ ለሆኑ አካላት ጥሩ አጋጣሚ እስከመሆን መድረሱን አስታውሰዋል፡፡

በተጨማሪም የክልሎች ልዩ ኃይሎች መፈርጠም በክልሎች መካከል መጠራጠር እንዲፈጠር አድርጓል ያሉት ብርጋዴር ጄነራል አሰፋ፤ ይህንን መጠራጠር ለማስቀረት አንድ ሀገራዊ አስተማማኝ የመከላከያ ሠራዊት ሊፈጠር ይገባል ሲሉ ገልፀዋል፡፡

ሕዝቡ ከዚህ በፊት የደረሰበትን የሞት እና የንብረት ውድመት ጉዳት በማሰብ የልዩ ኃይሉን አዲስ አደረጃጀት በጥርጣሬ ሊያየው እንደሚችል ጠቁመው፤ መንግሥት በግልጽነት መረጃዎችን በመስጠት ጥርጣሬ እንዳይፈጠር መሥራት እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

ልዩ ኃይልን መልሶ ከማደራጀት ጋር ተያይዞ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚታየው ውጥረት ከስጋት የመነጨ መሆኑን ጠቅሰው፤ መንግሥት ይህንን ሲፈፅም በክልሎች መካከል መጠራጠሮች እንዳይፈጠሩ በበቂ ሁኔታ ማወያየት እና መረጃዎችን መስጠት አለበት ሲሉም አክለዋል፡፡

በአንድ ሀገር ሊኖር የሚገባው አንድ የመከላከያ ሰራዊት እንደሆነ የጠቀሱት ብርጋዴር ጀነራል አሰፋ፤ ልዩ ኃይልን መልሶ የማደራጀት ሥራው ሕዝቡ በልበ ሙሉነት የራሱ ሠራዊት እንደሆነ እንዲያስብ ዕድል የሚፈጥር እና ዋስትናውም እንዲረጋገጥ የሚረዳ በመሆኑ በትኩረት ሊሠራ የሚገባው መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ሆኖም ልዩ ኃይልን ወደ መደበኛ የመከላከያ ሠራዊት እና ፌዴራል ፖሊስ ለመቀላቀል ጊዜ የሚፈጅ እና ውጤቱ እየተረጋገጠ የሚደረግ ተግባር መሆኑን በማንሳት፤ መንግሥት ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ሕዝቡን ወደ ታች ወርዶ ማዳመጥ እና እንደ አዲስ ስለሚካሄደው አደረጃጀት ማስረዳት አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

ልዩ ኃይልን አዲስ ተልዕኮ በመስጠት መከላከያን የማጠናከር ሥራ የመንግሥት ኃላፊነት መሆኑን ጠቁመው፤ ሆኖም የሚደረገውን ነገር ሕዝቡ እያወቀው እና ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ እየተሰጠ ሊሆን ይገባዋል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያን እንደምንወዳት የሚረጋገጠው ጠንካራ ሠራዊት በመገንባት ነው ሲሉም አክለዋል፡፡

# "ከፈንታሌ-ኤርታሌ" ፕሮጀክት ለሀገር ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደ ምክትል ቢሮ ኃላፊዋ ገለጻ፤ በአፋር ክልል የገበታ ለትውልድ ፕሮጀክት የሚተገበርባቸው አካባቢዎች የተፈጥሮ ፍል ውሃዎችና በቱሪዝም ልማት ከፍተኛ ገቢ ማምጣት የሚያስችሉ ተፈጥሯዊ ሐይቆችና የውሃ አካላት ይገኛሉ። በተጨማሪ ፖታሺየምና የተለያዩ የማዕድን ሀብቶች የሚገኙ በመሆናቸው ከቱሪዝም ሀብቱ ጋር አስተሳስሮ መስራት ይቻላል።

በአርታሌ ላይ የሚገኘውና ከዓመት ዓመት የሚንቀለቀለው ክፍት እሳተ ጎመራ በራሱ በርካታ ቱሪስቶችን የሚስብ መሆኑን አንስተው፤ በገበታ ለትውልድ ፕሮጀክት የተሻለ ገቢ የሚያስገኙ ሰፋፊ የሆቴልና የቱሪዝም አገልግሎት መስጫ ማዕከላት በአፋር እንደሚገነቡ ጠቁመዋል።

ዳሎል በአንጻሩ በዓለማችን ዝቅተኛው ስፍራ ተብሎ የተመዘገበ ቦታ ነው። ቱሪስቶች ከፍተኛ ስፍራዎች ላይ ወጥተው ታሪክን መስራት እንደሚፈልጉ ሁሉ የዳሎልን መሬት ረግጠው ብቻ በዓለም ዝቅተኛ ስፍራ ላይ ተገኝቻለሁ የሚለውን ታሪክ ለማስመዝገብ በሚል ቦታውን የሚጎበኙ ፈረንጆች መኖራቸውን ተናግረዋል።

ስፍራው በራሱ ድንቃድንቅ መዝገብ ውስጥ የሰፈረ በመሆኑ ጎብኚዎችን እያስተናገደ ቢሆንም፤ በገበታ ለትውልድ ፕሮጀክት ደግሞ ሰፋፊ የቱሪዝም አገልግሎት መስጫዎችና የተለያዩ መሰረተ ልማቶች ሲገነቡ ለኢትዮጵያም የሚተርፍ ገቢን ማስገኘት የሚያስችል አቅም እንዳለው መገመት አይከብድም ብለዋል።

የገበታ ለትውልድ ፕሮጀክት አንድ አካል የሆነው ዳሎል የተለያዩ የውጭ ሀገራት ሰዎች በርካታ ዶክመንቶችን አዘጋጅተውለትና በመፅሐፍም መልክ አሳትመው ሲጠቀሙበት ቢስተዋልም፤ ስፍራው ግን በሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ዘንድ እምብዛም የሚታወቅ እንዳልሆነ አንስተዋል።

በመሆኑም ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ እርስ በእርሱ ሊተዋወቅና አንዱ ክልል ያለውን የቱሪዝም መዳረሻ ማወቅና ትስስሩን በሚያጠናክር ሁኔታ መጠቀም የሚቻልበትን መንገድ ማስፋት ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ባለፉት ዓመታት በድርቅ፣ በጎርፍ፣ በአንበጣና በሰሜኑ ጦርነት የተነሳ ተደራራቢ ተግዳሮቶች ቢገጥሙም ችግሮቹን በመቋቋም አሁን ላይ የመልሶ ማቋቋምና የልማት ስራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ተናግረዋል።

አፋር በቱሪዝም መስክ ከክልል አልፎ ሀገርን መጥቀም የሚያስችል ዕምቅ አቅም ስላለው በቀጣይ የክልልን የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የቱሪዝም መስህቦችን ማልማት ላይ ትኩረት መደረጉንም ገልጸዋል።

ወይዘሮ ሐዋ እንዳስታወቁት፤ ባለሀብቶችና ኗሪዎችም የተለያዩ ተቋማት የገበታ ለትውልድ ፕሮጀክት በሚያርፍባቸው ከፈንታሌ እስከ ኤርታሌ በሚገኙ መዳረሻዎች ላይ ሀብትና ጉልበታቸውን በማፍሰስ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የጥፋትና የግጭት ትርክቶችን በጋራ እንግታ!

እያንዳንዱ ዜጋ የራሱንም ሆነ ያለበትን ማኅበረሰብ ፤ ከዚያም ባለፈ የሀገሩን ሰላም የመጠበቅና የማስጠበቅ ኃላፊነት አለበት ። ይህ ኃላፊነቱ የሚመነጨው ዛሬዎቹን ጭምር ነገዎቹ በሰላም ላይ የቆሙና ያለ ሰላም የተሟላ ትርጉም የሌላቸው በመሆኑ ነው።

የራሱን ሰላም በአግባቡ መጠበቅ ያልቻለ ዜጋ ፤ለማኅበረሰቡም ሆነ ለሀገሩ የሰላም ምንጭ ሊሆን ይችላል ተብሎ አይታመንም ፤ ከዛ ይልቅ ለሚኖርበት ማኅበረሰብም ሆነ ሀገር የሰላም ጠንቅ ሊሆን የሚችልበት ዕድል ሰፊ ነው። ይህ ደግሞ በእለት ተእለት ሕይወታችን ተደጋግሞ የሚያጋጥመንና አብዝተን የምናስተውለው እውነት ነው።

በተለይም ከለውጡ ማግስት ጀምሮ እንደ ሀገር አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት ለመገንባት እያደረግነው ባለው ጥረት ውስጥ ፤ ለራሳቸው ሰላም ያጡ ግለሰቦች በተለያየ መንገድ የኔ የሚሉትን ማኅበረሰብ ጨምሮ ሀገርን ሰላም ለማሳጣት እየሄዱበት ያለው የጥፋት መንገድ ከላይ የተገለጸውን እውነታ በተጨባጭ የሚያመላክት ነው።

ሰላም በማጣት የተመሰቃቀለ ማንነታቸው ለፈጠረው የጥፋት ስብዕናቸው መሸፈኛ የተለያዩ ስያሜዎችን ለራሳቸው በመስጠት ሕዝባችንን በፈጠራ ወሬዎች እና ትርክቶች ብዙ ዋጋ አስከፍለዋል፣ ዛሬም በዚህ ስብዕናቸው የሕዝባችንን ዛሬዎች ብቻ ሳይሆን ነገዎች ላይ ጥላ ሊያጥሉ በሚችሉ የጥፋት ተልዕኮዎች ተጠምደው ይታያሉ።

ዛሬ የሚሉትን ነገ የማይደግሙ፣ ትናንት ካሏቸው ጋር ዛሬ በአደባባይ የሚጋጩ ፣ ለዚህም ምክንያታዊ በመሆን ራሳቸውን ከተያዙበት የማንነት ምስቅልቅል ለመታደግ የሚሞክሩ፤ በሂደቱም ያገኙትን ሁሉ በመፈረጅ ራሳቸውን ጤነኛ አድርገው ለማቆም የሚጥሩ ናቸው።

ስለ ሀገር አንድነት ተሟጋች ነን እያሉ ፤መሽቶ እስኪነጋ ሀገርን በሚያፈርስ ሴራ ተጠምደው የሚውሉ ፤ የሆነ ብሔር ተቆርቋሪ ነን እያሉ ፤ የዚያን ብሔር መልካም እሴቶችን በማጥፋት፣ አይደለም ከሌሎች ከራሱ ጋር ተስማምቶ እንዳይኖር የአስተሳሰብ መዛነፍ ለመፍጠር ሌት ተቀን የሚጥሩ ናቸው።

ይህ ከባሕሪያቸው የሚመነጭና ራስን በአግባቡ ቆም ብሎ ካለመመልከት እያደገ የሚሄድ የስብዕና መዛነፍ ፤ የፖለቲካ ካባ ለብሶ ሲገለጥ የቱን ያህል ለአንድ ማኅበረሰብም ሆነ ሀገር የአደጋ ምንጭ ሊሆን እንደሚችል እንደ ሃገር ብዙ ዋጋ በመክፈል አይተነዋል፤ እያየነውም ነው።

ለውጡን ተከትሎ ባለፉት አምስት ዓመታት እንደ ሀገር ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር በነዚህ ግለሰቦችም ሆነ የነሱ ስብስቦች/ቡድኖች/ ስንቴ እንደፈረሰች ለመቁጠር ያዳግታል፤ ከየአንዳንዱ የጥፋት ትርክታቸው ማግስት በእነርሱ አዕምሮ ሃገር ፈርሳ አድራለች ።

ከያንዳንዱ የግጭት ትርክታቸው ማግስት ሕዝብ በሕዝብ ላይ ተነስቶ፣ሀገር በደም ጎርፍ ተጥለቅልቃ፤በጣርና ሲቃ ፤በለቅሶና በዋይታ ተሞልታ መሽቶ የሚነጋ ይመስላቸዋል። ይህ ስለሀገርና ሕዝብ ያላቸው መሻትና የተልእኳቸው አልፋና ኦሜጋ ነው።

እነዚህ ግለሰቦች ከግጭት የሚያተርፉ ይመስላቸዋልና ያላቸውን ዕውቀት፣ጊዜና አቅም ሁሉ ለዚህ እኩይ ተልእኮ ያውላሉ ፤ ቆም ብለው ምን እየሠሩ እንደሆነ ለማየት ፈቃደኛ አይደሉም፤ ለራሳቸው ያላቸው የተሳሳተ ግምት የገዛ ጠላታቸው ሆኖባቸዋል። ስለሆነም በዚህ ክፉ ርግማን ውስጥ ሲዳክሩ መሽቶ ይነጋላቸዋል።

አንዳንዶች ለእነዚህ በሰላም እጦት በተመሰቃቃለ ማንነት ለሚሰቃዩ ግለሰቦች እና ቡድኖች የጥፋት እና የግጭት ትርክት ጆሯቸውን በመስጠት የገዛ ሰላማቸውን ፣ ከዚያም ባለፈ የማኅበረሰባቸውንና የሀገራቸውን ሰላም በሚፈታተን መንገድ ላይ ቆመው መገኘታቸው ነው።

ማንኛውም ለሀገሪ ተቋርቋሪ የሆነ ዜጋ የራሱን ሰላም ከዚያም ባለፈ የሚኖርበትን ማኅበረሰብና የሀገሪቱን ሰላም ለመጠበቅ ከእነዚህ ግለሰቦች እና ቡድኖች የጥፋት እና የግጭት ትርክቶች ጆሮዎቹን ማራቅ ይጠበቅበታል!

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሰላም የምንሻ ሁሉ የሰላሙ ሂደት ባለቤት ልንሆን ይገባል

በጋዜጣው ሪፖርተር

«አስተማማኝ ሰላም ለዘላቂ እድገትና ብልጽግና ነው» የምትለው ይቺ አባባል በተለያዩ ግዜያት በበርካታ ምሑራንና ፖለቲከኞች ስትነገር እንሰማለን። ምን አልባትም አብዛኛው ልሂቅ ከሚያስማሙ መሠረታዊ ሀሳቦች መካከል ቀዳሚዋም ትመስለኛለች። ለዚህ ማሳያችን ዛሬ አደጉ የምንላቸው ሀገራት በተለይም ባለፉት ስልሳና ሰባ ዓመታት ፈጣን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገት ያመጡት በቅድሚያ የተረጋገጠ ሰላም በሀገራቸው ማስፈን በመቻላቸው ነው።

እነዚህ ሀገራት ቀደም ባለው ጊዜ ውጪውም ሆነ ውስጣዊ ችግሮች ነበሯቸው። ለሰላማቸው ቅድሚያ ሰጥተው በመሥራታቸውና የውስጥ ሰላማቸውን በማረጋገጣቸው ዛሬ ሕዝባቸውን ከዳር እስከ ዳር ተጠቃሚ የሚያደርግ እድገትና ብልጽግናን ማስመዝገብ ችለዋል። እንደ ጎረቤታችን ሶማሊያ ደግሞ እርስ በእርስ ባለመስማማት ሕዝባቸውን ዛሬም ድረስ ለስቃይና ለስደት ብሎም ለእልቂት እየዳረጉ አሉ ።

በተለይም ይህ እውነታ በአፍሪካ ሀገራት በስፋት የሚስተዋል ነው። አፍሪካውያን ሀገራት ሰላማቸውን አስከብረው በልማት አሁን ካሉበት ኋላ ቀርነት ለመውጣት ብዙ መሻት ቢኖራቸውም በተለያዩ ምክንያቶች መሻታቸውን መኖር አልታደሉም። ዛሬም በእርስ በርስ ግጭቶች እየታመሱ ፤ ሕዝባቸውን ለረሀብና ለችጋር እንደተጋለጡ ነው ።

> **አፍሪካውያን ሀገራት ሰላማቸውን አስከብረው በልማት አሁን ካሉበት ኋላ ቀርነት ለመውጣት ብዙ መሻት ቢኖራቸውም በተለያዩ ምክንያቶች መሻታቸውን መኖር አልታደሉም። ዛሬም በእርስ በርስ ግጭቶች እየታመሱ ፤ ሕዝባቸውን ለረሀብና ለችጋር እንደተጋለጡ ነው**

እነዚህ ሀገራት «ቅድሚያ ለሰላም» በመስጠት የውስጥ ችግሮቻቸውን በራሳቸው አቅም በውይይት ለመፍታት በቂ ዝግጁነት ባለመፍጠራቸው፤ ሕዝባቸው ተፈጥሮ ያደለውን በረከት ተጠቅሞ በራሱ ካለበት ጉስቁልና እርዳታ ጠባቂነት ሊወጣ አልቻለም ።

ሀገራችን ኢትዮጵያም ያለፉትን ሀምሳ ዓመታት በተለያዩ ጊዜያት ብልጭ ድርግም በሚሉ የውስጥ ችግሮች በብርቱ ተፈትናለች ፤አሁንም እየተፈተነች ነው። የሩቁን ታሪክና ተረት ወደ ጎን ትተን ባለፉት ሦስት አራት ዓመታት ብቻ በሀገራችን የተከሰተውን ብንመለከት በአንዳንድ ሁኔታዎች ኢትዮጵያ አበቃላት እስከማለት የተደረሰባቸው ተደጋጋሚ ግዜያቶች ነበሩ።

ነገር ግን ውድቀታችንን የሚመኙ እንዳሰቡት ሳይሆን ቀርቶ ነገሮች ተዓምር ሊባል በሚል ደረጃና ፍጥነት ተለውጠዋል ። የዚህ ጅማሮ መነሻው ደግሞ በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የተደረገው የሁለትዮሽ ስምምነት ነበር። በእርግጥ የነበረውን ሁኔታ በቅርበት ሲከታተል ለነበረ ኢትዮጵያዊ ይቅርና የምሥራቅ አፍሪካን ፖለቲካ ለሚከታተል ማንኛውም ሰው እውነታ አንዳች ስሜት የሚያጭር ነበር። በወቅቱም በርካቶች በነቀፋም... በድገፋም.. በትችትም.. በመገረምም የሰጧቸው አስተያየቶች ለዚህ ማሳያዎች ይመስሉኛል።

በእውነትም አብዛኞቻችን ዘንድ እውን ስምምነቱን ተከትሎ የሰላም አየር ይሰፍን ይሆን የሚል ጥያቄ አስተናግደን እንደነበር እገምታለሁ። ምክንያቱም ነገሩ ሕልም እንጂ እውነት ስለማይመስል ነው። እያደር ግን ነገሮች ወደተቀመጠላቸው መስመር መግባት መጀመራቸውን ለመመልከት በቃን።

የሰላም ፍሬ ለሰው ልጅ እንደ ጥሩ ገበሬ ያለመታከት በሚደረግ ልፋት እንጂ እንደ እንስሳት ወፍ ዘራሽ ሆኖ ሊገኝ እንደማይችል የሚዘነጋ አይኖርም። ያለ መታከት ለሰላም መሥራትና መዘመር ያለበት ደግሞ በመንግሥት፤ በሀይማኖት አባቶችና በፖለቲከኞች ብቻ ሳይሆን እንደ ዜጋም በእያንዳንዱ ተግባርና አንደበት ሊሆን ይገባል።

ይህ መደረግ ያለበት ዋነኛው ምክንያት በመጀመሪያ ደረጃ መንግሥት ምንም ያህል ጠንካራ ቢሆን ያለ ሕዝብ ተሳትፎ የሚሠራቸው ሥራዎች ውጤታማ ሊሆኑ ስለማይችሉ ነው ። ሁለተኛው ደግሞ በሰላም መደፍረስ ቀዳሚ የገፈቱ ቀማሽ የሚሆነው የመንግሥት አመራር አልያም ፖለቲከኛው ሳይሆን ሰፊው ሕዝብ መሆኑ ነው።

ሕዝብ እንደ ሕዝብ በሁለንተናዊ መልኩ ለሰላሙ መቆም አለበት። በአሁኑ ወቅት በሀገራችን በተለያዩ ቦታዎች እየተፈጠሩ ያሉ የሰላም እጦቶች በባእድ ወራርያን ሳይሆን እርስ በእርሳችን ነው። እዚህ ላይ የችግሩ መነሻ ምንም ይሁን ምን የባዕዳን እጅ ይኑርበት አይኑርበት በመድረኩ ላይ ተዋናዮቹ እኛው ኢትዮጵያውያን እራሳችን ነን ።

የተለያዩ የጥፋት ትርክቶችን ፈብርከው በችግሮቻችን ላይ ቤንዚን ለሚያርከፈክፉ የግጭት ጠማቂዎች ፤ የማኅበራዊ ሚድያ ጀብደኞች ጆሮአችንን ከመስጠት ጀምሮ በትርክቶቻቸው ተታልለን በሰላማችን ላይ የመጀመሪያው ሰልፈኞች እየሆንን ያለነው እኛው ነን። ለዚህ ደግሞ የእለት ተእለት እንቅስቃሴያችንን ቆም ብሎ ማየት በቂ ነው ።

በውስጣችን ፈቅደን የተዘራብንን የጥላቻና የሁከት ዘር ተሸክመን ቀጣይ የጉዞ መስመራችን ምን ሊሆን እንደሚችል ነጋሪ የሚጠይቅ አይደለም። እንደ ግለሰብ ጥላቻንና ጸብ ተዘርቶብን ፍቅርን ለማጨድ የምንችልበት ፍጥረታዊ አካሄድ/አቅም የለንም።

መንግሥትም ውጪያዊውን ሁከትና ብጥብጥ ካለበት የሀገርና የሕዝብ ሰላም የማስከበር ሕገመንግሥታዊ ኃላፊነት አንጻር የሚቻለውን አማራጭ ይጠቀም ይሆናል እንጂ በኛ ውስጥ ፈቅደንና ወደን ያዘራነውን ክፉ ዘር ፍሬ እንዳያፈራ የማድረግ የተሟላ አቅም የለውም ።

የሀገር ሰላምን በማስፈን እና ጠብቆ በማስቀጠል ሂደት ውስጥ ዋንኛው ተዋናይ ሕዝብ ነው፤በራሱ የሰላም ሐዋርያ በመሆንና ለሰላም ዘብ በመቆም፤ይህ ደግሞ ሰላምን የሚገዳደሩ ሁኔታዎችን/ አቅሞችን በሙሉ ካለመቀበል ጀምሮ አምሮ እስከመታገል በሚደርስ ቁርጠኝነት ሊገለጥ ይገባል ።

ዛሬም በሀገራችን በብርቱ ምላሽ የሚሹ በርካታ ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥያቄዎች ቢኖሩም እነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ሊያገኙ የሚችሉት ሁሉም ዜጋ ለሰላም ቅድመ፣ ሲሰጥና ስለሰላም በኃላፊነት መንፈስ ሲንቀሳቀስ ብቻ ነው ።እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ሰላምን መረበሽም ዘላቂ መፍትሔ ሊሆነን አይችልም።

የየትኛውም አካል/የትኛውም ጥያቄ ዘላቂ መፍትሔ ይዞ እንዲመጣ የሕዝብን ሰላም በማይነሳ ፤ አብሮነትን በማያላላ ሕግ በማይጥስ መንገድ ሊሆን ይገባል። እያንዳንዱ ዜጋ እንደ ግለሰብም ሆነ ማኅበረሰብ ፤ አልያም እንደ ልሒቅ በራሱም ሆነ በሕዝብ ስም ጥያቄ ሲያነሳ ስለ ጥያቄው አቀራረብ ደግሞ ደጋግሞ ሊያስብ ይገባል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሚስተዋሉ ሁለት መሠረታዊ ችግሮች አሉ፤ አንደኛው በብዙዎቻችን ጥያቄ ውስጥ የፍላጎት መደራረብ መኖሩና ሁላችንም በጠየቅነው ልክ መንግሥት ምላሽ ሊሰጠን ይገባል የሚል ነው። ወቅታዊ ሁኔታን ፤ሀገራዊ ተጨባጭ እውነታን እያወቁ አላዋቂ ሆኖ በመገኘት ፤ጉዳዮችን የፖለቲካ ቁማር ካርድ አድርጎ መጠቀምን የሚመለከት ነው ።

ሁለተኛው ደግሞ የትኛውንም ጥያቄ ለመመለስ ጊዜ የሚፈልግ ትዕግስት የሚጠይቅ መሆኑን ካለመረዳት ሳይሆን ከችግሮች የፖለቲካ ትርፍ ከመፈለግ የሚመነጭ ነው። እነዚህ ችግሮች በአግባቡ በመረዳት ሕዝባችን ጥያቄዎቹን በሰላማዊ መንገድ ማቅረብን መልሱንም በትዕግስት መጠበቅ ይኖርበታል ፤በተለይም አሁን ካለንበት አስቸጋሪ ሀገራዊ እውነታዎች አንጻር ሁሉም ለሀገራዊ ሰላም ዘብ ሊቆምና ቅድሚያም ሊሰጥ ይገባል እላለሁ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## በዓልና የባሕል አልባሳት ፍላጎት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

የባሕል አልባሳት የኢትዮጵያዊ ማንነት መለያ፣ የበዓላት ጊዜ መዋቢያና መደመቂያም ናቸው።በዓል በመጣ ቁጥር ኢትዮጵያውያን አምረውና ድምቀው እንዲታዩ ከሚያደርጉ፣ በዓልን በዓል ከሚያሰኙ ነገሮች መካከል የባሕል አልበሳት ትልቁን ድርሻ ይይዛሉ።

ይህ ሁኔታ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ይበልጥ እየተጠናከረ መጥቷል።በአዘቦት ቀን እንኳን ሰዎች የባሕል አልባሳት ለብሰው ሲታዩ ዛሬ ደግሞ ቀኑ ምንድነው በዓል አለ እንዴ? ብሎ እስከመጠየቅ ተደርሷል።

የሠርግ ሥነ ሥርዓቶች፣ የጥምቀት በዓል ለባሕል አልባሳት ፍላጎት እየሰፋ መምጣት የራሳቸውን ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ።የቤተሰብ አባላት፣ ጓደኞች፣ ወዘተ ተመሳሳይ የባሕል አልባሳት እያሠሩ የሚለብሱበት ሁኔታም ሌላው በባሕል አልባሳት መፈለግ አዎንታዊ ተጽዕኖ ያሳደረ ጉዳይ ነው።

ምስጋና ለፋሽን ኢንዱስትሪው ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ አልባሳቱ ይበልጥ መዋብ ውስጥ ገብተዋል።አልባሳቱ በባሕላዊና በዘመናዊ መልኩ እንደ ለባሹ ፍላጎትና ምርጫ እየተሠሩ ለገበያ እንዲቀርቡ እየተደረገ ነው፤ተፈላጊነታቸውም በዚያው ልክ እየጨመረ ፤ከበዓላትም ውጪ እየተዘወተሩ ይገኛሉ።

በበዓላትም ቢሆን እንደ የበዓሉ አይነት፤ በዓሉን የሚመጥኑ የተለያየ አይነት የሀገር ባሕል ልብሶች ይለበሳሉ።ለአዲስ ዘመንና ለትንሳኤ በዓል የሚለበሱት አልባሳት በዓይነትም ሆነ በይዘት ይለያሉ።የአልባሳቱ ዓይነት በሸማቹ ፍላጎትና ምርጫ ላይ የሚመሠረት ቢሆንም በዲዛይን ተሠርተው ባማረ መልኩ ይቀርባሉ።ለዚህም ነው አሁን ላይ ባሕላዊ ይዘታቸውን ሳይለቁ ባማረ ዲዛይን ተሠርተው ልበሱኝ! ልበሱኝ! የሚያሰኙ የባሕል አልባሳት እየተበራከቱ መምጣታቸው።

በዛሬው ፋሽን ዓምዳችን ስለ ባሕላዊ አልባሳት ማንሳት የወደድነው አልባሳቱ የዛሬው የትንሳኤ በዓል አልባሳቱ በስፋት የሚለበሱበት በመሆኑ አያይዘን ስለአልባሳት ጥቂት እንበል ብለን።ለእዚህም በበዓላት ተፈላጊ የሆኑ የሀገር ባሕል አልባሳት ገበያ ቅኝት አድርገናል፤ለባህል አልባሳት ልዩ ትርጉም የሚሰጡ የልብሱን አዘውታሪና ዲዛይነርም አነጋግረናል፡፡

ኤልሳቤጥ አበበ ትባላለች።ለበዓል የምትለብሰውን የሀገር ልብስ ለዲዛይነር መስጠቷን ሰሞኑን ነግራናለች። ኤልሳቤጥ የባሕል ልብስ መልበስ ትወዳለች፤ ከበዓላት ቀናት ውጪም በአዘቦት ቀናት ጭምር የባሕል ልብስ መልበስ ታዘወትራለች፡፡

‹‹እንኳንስ በበዓል ቀን ይቅርና በሌላም ጊዜ ምክንያት ፈልጌ ነው የሀገር ልብስ የምለብሰው›› የምትለው አልሳቤጥ፤ ቤተክርስቲያን፣ ወደ ተለያዩ ጥሪዎች እና የሥራ ቦታዎች ስትሄድ ሳይቀር የሀገር ልብስ መልበስ እንደሚያስደስታት ትናገራለች፡፡

ይሁን እንጂ አሁን ላይ ያለው የልብሶች ዋጋ መናር ለመልበስ አያስመኝም የምትለው አልሳቤጥ፤ እንደሌላ ጊዜ በየበዓሉ የሀገር ልብስ ማሠራት ቀርቶ በዓመት አንድ ጊዜ ለመልበስ እንኳን ዋጋው የማይቻልና ኪስ የሚጎዳ እየሆነ መምጣቱን ትገልጻለች።

አሁንም ለትንሳኤ በዓል የሀገር ልብስ ለማሠራት የፈለገችበት ዋነኛ ምክንያት ከበዓሉ በኋላ ሌላ ፕሮግራም ስላላት ለዚያም ጭምር አስባ እንጂ ዋጋው ተመጣጣኝ ሆኖ እንዳልሆነም ትገልጻለች።ልብሱን ያሠራችበት ዋጋ 8ሺ ብር ነው፤ ይህም በዋጋ ትንሹ እንደሆነ ነው የምትናገረው።ትንሹ ዋጋ ተብሎ የሚጠራው እንኳን የኅብረተሰቡን የመግዛት አቅም ያገናዘበ አይደለም በማለት ጠቁማለች፡፡

‹‹የሀገር ልብሶቻችን እኮ የኛ ናቸው፤ እኛ ለብሰን ካልደመቅንባቸውና ካለጌጥንባቸው ማን ሊያጌጥባቸው ይችላል›› ስትል ገልጻ፣ በበዓላት ጊዜም ሆነ በማንኛውም ጊዜ በልብሶቹ የሚደምቀው እና የሚያምረው ከኛ በላይ የለምም ነው የምትለው።ብዙ ሰዎች በሀገራቸው ልብስ መድመቅ እየፈለጉና እያማራቸው ከዋጋቸው አንጻር መልበስ አዳጋች እንደሆንባቸው ትገልጻለች።

ቀደም ሲል ሁሉም ሰው የሚፈልገው ዓይነት የሀገር ልብስ በሚችለው ዋጋ ሸምቶ መልበስ ይችል ነበር ።ለዚህ የአደባባይ በዓላቶቻችን ምስክር ናቸው የምትለው አልሳቤጥ፤ አሁን ላይ አብዛኛው ሰው ሽፎንና የቻይና ልብሶችን እየሸመተ መልበስ መጀመሩን ትገልጻለች።የሀገር ልብስ ሁሉም ሰው በሚፈልገው ዓይነት በተመጣጣኝ ዋጋ ሸምቶ ሊለብሰው የሚችል መሆን አለበት እንጂ ከሰው አቅም በላይ እንዳይለበስ መደረግ የለበትም ትላለች።

የወንዶችና የሴቶችን የባሕል አልባሳት ዲዛይን በማድረግ የምትታወቀው ዲዛይነር ቅድስት ወልዴ በበኩሏ፤ የደንበኞችን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ልብሶቹን እንደምታዘጋጅ ትገልጻለች።ዲዛይነሯ ሁሉን ያማከሉ የተለያዩ የባሕል አልባሳትን ዲዛይን በማድረግና በመስፋት ለገበያ ታቀርባለች።

እንደየበዓሉ ሁኔታ ደንበኞች በሚፈልጓቸውና በሚመርጧቸው መጠን ልብሶችን እንደምታዘጋጅ የምትናገረው ዲዛይነር ቅድስት፤ በበዓል ጊዜያት ባሕላዊ ሆነው በሸመና የሚሠሩ ቀለል ያሉ ለባሕል የሚሆኑ ልብሶች ተመራጭ ናቸው ትላለች ።

በፋሲካ በዓልም ቀለል ያሉ ባሕሉን የጠበቁ ከባሕሉ ጋር አብረው የሚሄድ ጥለቶች እንዳሉም ትጠቁማለች፡ ፤ በተለይ አረንጓዴ ጥለት ያላቸው፣ ተጠልፈው ፤ተሰፍተውና ተሸምነው የሚለበሱ ጥበብ ነገሮች በዚህ በዓል እንደሚመረጡ ነው የጠቆመችው፡፡

‹‹የሀበሻ ቀሚስ ተፈላጊ ነው፤ ሰዎች የባሕል ልብስ መልበስ ይወዳሉ›› የምትለው ዲዛይነር ቅድስት፤ አሁን የአልባሳት ዋጋ መጨመር ከኑሮ ውድነት ጋር ተያይዞ ገበያውን እንዲቀዛቀዝ ማድረጉን እሷም ገልጻለች።

ልብሱን ለመሥራት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች መወደድ ዋጋውን ከፍ እንዲል ያደረገው መሆኑን ጠቅሳ፤ የዋጋው ውድነት ገበያ እንዲቀዛቀዝና ሸማቹ እንዳይገዛ ምክንያት እንደሆነም ነው ያመለከተችው።ከክር ጀምሮ ፤ለባለሙያ፣ ለሸማኔ ወዘተ. የሚከፈለው ክፍያ፤ ሁሉም ነገር ጨምሯል የምትለው ዲዛይነር ቅድስት፤ ይህ ልብሱ እንዲወደድ ችግር መፍጠሩን ጠቁማለች፡፡

የልብሶቹ ዋጋ እንደየልብሱ አይነት የተለያየ ቢሆንም ከትንሽ እስከ ትልቅ ድረስ ዋጋ የሚጠሩ ልብሶች እንዳሉም ጠቅሳ፣ ከ5ሺ ጀምሮ ከ20ሺ ብር በላይ የሚሸጡ ልብሶች እንዳሉም ታብራራለች።ዋጋው እንደየዲዛይኑና ጥበብ አይነት እንደሚለያይም ነው የተናገረችው፡፡

አብዛኛው ሸማች የሚፈልገው ባሕሉን የጠበቀውን ልብስ ነው የምትለው ቅድስት፤ ጥበቡ እንዳለ ሆኖ በዲዛይን ተደርጎ እንዲሠራ የሚፈልጉ እንዳሉም ትገልጻለች።እንደየሸማቱ ፍላጎት አልባሳቱ እንደሚዘጋጁም ትገልጻለች።ትልልቅ ሰዎች ባሕሉ እንዲጠበቅ ይፈልጋሉ፤ ወጣቶች ደግሞ በዲዛይን እንዲሠራ ይመርጣሉ የምትለው ዲዛይነር ቅድስት፣ የባሕል ልብስን በሁሉም እድሜ ደረጃ ያሉ ሰዎች የሚለብሱት በመሆኑ ሁሉን ያማከለ ሥራ እንደሚሠራ ነው የምትናገረው፡፡

‹‹የባሕል ልብሶችን በሚፈልጉት መልኩና ዲዛይን የሚያሠሩ ሰዎች ትዕዛዙን ቀደም ብለው ማዘዝ አለባቸው›› እንዳለባቸውም ዲዛይነር ቅድስት ታስገነዝባለች።ምክንያቱም የባሕል ልብስ ሥራው ከባድ መሆኑና ሸማኔ ለማዘዘ ቀን ስለሚፈልግ መሆኑን ትናገራለች፤፤ ከሁለት ወር በፊት በማሳወቅ የግድ መሆኑንም ነው ያመለከተችው።ሸማቶች ቀደም ብለው ቢያሳወቁ ጥሩ ነው ትላለች ፡፡

ዲዛይነር ቅድስት እንደምትለው፤ የባህል አልባሳትን የማዘጋጀቱ ሥራ ከዋጋ ንረቱ ጋር ተያይዞ ፈታኝ ሆኗል።የዋጋ ንረቱ ለሥራው እጅግ አዳጋች እየሆነ ነው ፤ በየጊዜው ዘርፉን የሚያዳክሙ አዳዲስ ነገሮች በየጊዜው ይፈጠራሉ፤ በዚህ የተነሳ ዘርፉን ለማሳደግ አልተቻለም፤ ገበያው የሚረጋጋበት መንገድ ቢፈጠር ገበያው ይረጋጋል ፤ ሁሉም በየአቅሙ የሚችለው ገዝቶ መልበስ ይችላል፡፡

ሙያው እንዲያድግ በማድረግ በዘርፉ ልቆ ለመውጣት ባለሙያው እንደፈለገ እንዲሠራ መድረግ አለበት የምትለው ዲዛይነር ቅድስት፤ ለዚህም በዋጋ ማረጋጋቱ ላይ መንግሥት ትኩረት እንዲሰጥ ጠይቃለች።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## የሲስተም እና መመሪያ ነገር...

ባለፈው ሰሞን ለአንድ ጉዳይ በአቅራቢያዬ የሚገኝ ወረዳ ሄጄ ነበር።እንደተለመደው የወረዳው ግቢ በትርምስ ተሞልቶ ማን ለምን ጉዳይ እንደመጣ በማይታወቅበት መልኩ የቅዳሜ ገበያ መስሏል።እኔ የሄድኩት ደግሞ ወሳኝ ኩነት የሚባለው ከገበያም በላይ የሚደምቅ ቦታ ነው።በጊዜ የደረስኩ ቢመስለኝም ሰልፉ ግን ተጠማዞ የትና የት ሄዷል።እንደማንኛውም ሰው ተሰለፍኩ።ሠራተኞቹ አሠራራቸው ዲጂታላይዝድ ነው ቢባልም መንቀራፈፋቸው ግን ጥልፍ እንደሚሠራ ሰው ነው።አስተሳሰብ ዲጂታላይዝ ካልሆነ ሥርዓት ዲጂታላይዝ ቢሆን ጥቅም እንደሌለው ሁነኛ ማሳያ ይሆናሉ፡፡

ከብዙ መቆየት በኋላ ደረሰኝ።መሣሪያ ተደግፍዋበት የሚሠራ የሚመስል አንድ ስልቹ ሰው ቆጣ ቆጣ እያለ ወደ መዝገብ ቤት መራኝ።መዝገብ ቤት ያለችው ደልዳላ ሴትዮ ከሰውየው በበለጠ በሥራውም ብቻ ሳይሆን በሕይወቷም የተበሳጨች ትመስላለች።ማነው የላከህ አለችኝ።ወደላከኝ ሰውዬ ጠቆምኳት።እኔ የማንንም ፋይል በመጎተት ክንዴ ተገነጠለ ፤ ለምን እነሱ ኮምፒዩተር ላይ አያዩላችሁም ብላ ተፈናጥራ ተነሳች።ፋይሉን ካለበት ጎትታ አምጥታ አገላብጣ ማየት ጀመረች።እርግጥ የኛም ቤት ፋይል ከመወፈርም በላይ በጣም አርጅቶ ለዓይንም ይከብዳል።የሆነ ነገር ጽፋ ወረቀቱን ሰጠችኝ ፤ ወደ ሰውየው ተመለስኩ።ወረቀቱን አየና በል ወደ ወረፋህ ተመለስና ተራህን ጠብቀህ ትስተናገዳለህ አለኝ።ተመልሼ ተቀመጥኩ፡፡

ተራዬ ሲደርስ ኮምፒውተር ላይ ወደተቀመጠ ወጣት ልጅ ሄድኩ።ለምን ቀስ ብለው እንደሚሠሩ አሁን ገባኝ።ልጁና ሲስተሙ ብዙም አይተዋወቁም።ስለዚህም ቀስ እያለ ነው የሚሠራው።የሲስተሙን አንዳንድ ክፍል እንደማይረዳው ከአሠራሩ ማየት ችያለሁ።መረጃዎችን እየጠየቀኝ ሞላ።ከዚያ ግን መሞላት ግዴታ ያልሆነበት ክፍል ላይ ደረሰ።መረጃ ሲጠይቀኝ ይህ ክፍል ግዴታ እንዳልሆነ ነገርኩት።ግዴታ ነው አለኝ።ግዴታ እንዳልሆነ ኮምፒውተሩ ላይ እንደሚያሳይ ባመላከተውም ሊሰማኝ ፈቃደኛ አልሆነም።ሞላው።መረጃው ተጠናቆ ሲወጣ እኔ ከምፈልገው በተቃራኒው ሆነ።ሁሉንም በተራ አናገርኳቸው።አንዳቸውም ስህተታቸውን ለማመን አልፈለጉም።ሲስተሙ ግድ ይለናል አሉ።ሲስተሙ የግድ እንደማይል ባሳያቸውም ሊቀበሉ አልፈቀዱም።ሸንፈት መሰላቸው።በኋላ አናግረው ተብዬ ወደ ቡድን መሪው ጋር ደረስኩ።ወጣት ነው።ጉዳዬን ከሰማኝ በኋላ ትንሽ እንድጠብቅ ነግሮኝ ሄደና ሌላ ጉዳይ ፈጽሞ ሲመጣ አወራን።መምሪያው ይፈቅዳል አለ።ሌሎቹ አይፈቅድም አሉ።እርስ በርስ ክርክር ተጀመረ።ክፍለ ከተማ እና ሌላ ወረዳ ደወሉ።በመጨረሻ መመሪያው እንደሚፈቅድ ተረጋገጠና በድጋሚ ተስተካክሎ ተሠራልኝ፡፡

ከአንድ ቢሮ ጠቅላላ ሠራተኛ መመሪያ በትክክል የሚያውቀው አንድ ሰው ብቻ መሆኑ አስገረመኝ።ብዙዎቹ መመሪያውን አያውቁትም ወይም የሚያውቁት በአንድ ወቅት የነበረውን ብቻ ነው።ሲለወጥ አልሰሙም ወይም አላስተዋሉም።ይሄ አንደኛው ችግር ነው።መመሪያ ተለዋዋጭ ነው።ያን ግን የሚረዳው ሰው ጥቂት ነው።ብዙው ሰው እንደ መንፈሳዊ ሕግ አንዴ ከሰፈረ የሚቀየር አይመስለውም፡፡

ዋነኛው ችግር ግን የመመሪያ እውቀት አለመኖር አይደለም።ስንፍና ነው።እንዳስተዋልኩት ብዙዎቹ አለማወቃቸውን ወይም ስህተታቸውን የሚሸፍኑት መመሪያው አይፈቅድም ወይም ሲስተሙ አይፈቅድም በሚል ሽፋን ነው።የትኛው መመሪያ መቼ የወጣው መመሪያ ቁጥር ስንት ቢባሉ ማስረዳት አይችሉም።እንዲሁ በደፈናው መመሪያው ይሉሃል።ሕዝብም መንግሥት ያወጣው መመሪያ ከሆነ መቼስ ምን አደርጋለሁ ብሎ እሺ ይላል።በዚህ የተነሳ መንግሥት ባላወጣው መመሪያ ሕዝብ ይጉላላል።ብዙው ሕዝባችን በተለይ እናቶችን እና አባቶች ዛሬም ቢሆን መንግሥትን የሚያምኑ ናቸው።የመንግሥት መመሪያ ነው ከተባሉ እሺ ብለው ነው የሚሄዱት።በዚህም የተነሳ ማግኘት የሚገባቸውን አገልግሎት ሳያገኙ ነው የሚሄዱት ማለት ነው።ይህ መንግሥት ገቢ ፤ ሕዝብን አገልግሎት ያሳጣል።ምሬትን ይወልዳል።ምሬት ደግሞ ሲጠራቀም አመጽን ይወልዳል።እንዲህ አይነቱ አመጽን የሚፈጥሩት እንዝላል ሠራተኞች ይሆናሉ ማለት ነው፡፡

ሲስተምም ላይ እንደዚያው።በጣም ያስገረመኝ ራሱ የጻፈው ጽሑፍ ላይ ያለን የፊደል ግድፈት ሲስተሙ ነው ሲለኝ ነው።ሲስተሙ በባለሙያዎች የተዘጋጀ ነው።ምን ተብሎ እንደሚጻፍ በግልጽ ተቀምጧል።status የሚልን ቃል states ብሎ ሲጽፍ ስህተት እንደሆነ ብነግረው ሲስተም ነው ብሎኝ ድርቅ አለ።በሁለቱ ቃላት መሐከል ያለው የፍቺ ልዩነት በጣም ሰፊ ነው።ይህ ዶክመንት በዓለም ዙሪያ የሚሠራ ዶክመንት ነው።ስለዚህ ይህ ዶክመንት የኢትዮጵያን መንግሥት አቅም የሚያሳይ ነው።ታዲያ 120 ሚሊዮን ሕዝብ የሚመራ መንግሥት እንዲህ አይነት ስህተት ተሳሳተ ቢባል ማን ያምናል።መንግሥት ተሳስቶ አይደለም ፤ ሲሰተሙ አስገደዶም አይደለም ፤ ሲስተሙ ላይ ያለው ሰው ንዝላልነት ግን ይህን አላስፈላጊ ስህተት ፈጥሯል፡፡

በጥቅሉ ብዙዎች መምሪያ እና ሲስተምን እነሱ ላለባቸው ንዝላልነት ፤ የቀናነት ችግር እና የሙስና ዝንባሌ እንደመጠቀሚያ እያደረጉት ነው።ይሄ በእርግጥ የእነሱ ችግር ብቻ ሳይሆን የብዙው ሕዝባችን ችግር ነው።እሱ የማያውቀውን እውቀት እንደ እውቀት የማይቆጥር ፤ እሱ ያልሰማውን መረጃ እንደ ፈጠራ ወሬ የሚያናንቅ ፤ ለአዲስ ነገር ክፍት ያልሆነ ሕዝብ ብዙ ነው።ጓዶች እውቀት ማለት እኛ የሰማነው እና የምናውቀው ብቻ አይደለም።እንዲያውም እኛ የማናውቀው ብዙ ነገር እንዳለ ማወቅ የእውቀት ጅማሮ ነው።ብዙ ሰዎች ዛሬ ላይ ስለ ዓለም ፤ ስለ ሀገር ፤ ስለ መንግሥት ፤ ስለ ሀይማኖት፤ ስለ ሌላውም እነሱ ጋር ያለው እውቀት የመጨረሻው እውቀት እንደሆነ በማመን በእርግጥኝነት ይናገራሉ።ይህ ስህተት ነው።እውቀት ተለዋዋጭ ነው።ነባራዊው ሁኔታም ተለዋዋጭ ነው።ሲስተምም መመሪያም ሕግም ተለዋዋጭ ነው።ለውጥ ሊኖር እንደሚችል ማወቅ እና መዘጋጀት እንጂ እኔ የማውቀው ብቻ ነው የመጨረሻው እውቀት ከዚያ ወዲህ አዲስ እውቀት አልመጣም ብሎ መታገል ስህተት ነው፡፡

ሲጠቃለል ፤ በመንግሥት ተቋማት የምትሠሩ ሰዎች እባካችሁ ስንፍናችሁን በመመሪያ ፤ በደንብ ፤ በሕግ ፤ በሲስተም አንሸፍነው።ይልቁንም ወቅታዊውን መረጃ በትክክል ማወቃችንን እርግጠኛ እንሁን ፤ ለማወቅም እንጣር።እንደ ሕዝብ ደግሞ ለአዲስ እውቀት በራችንን እንክፈት ፤ ያላወቅነው ነገር ሊኖር እንደሚችል በጥቂቱም ቢሆን እንጠርጥር፡፡

**ቸር እንሰንብት!**

# ነፃ ሃሳብ

# የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ . . . የፍትሕና የሰብዓዊነት የተጠያቂነትም ውሃ ልክ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

የዓለምን የፖለቲካ ሽኩቻ ከቀየሩና ተጠያቂነትን ካሰፈኑ የፖሊሲ ሥርዓቶች አንዱ ከላይ ለርዕሴ የመረጥኩት ጽንሰ ሀሳብ ነው። ጽንሰ ሀሳቡ በታማኝነትና በፍትሐዊነት፤ በተራማጅ እሳቤም ሰብዓዊነትን መሠረት አድርጎ የሚንቀሳቀስ ሲሆን በዋናነት ወንጀለኞችን ለፍርድ የሚያበቃ፤ ተበዳይን ደግሞ ለበደሉ የሚመጥን ካሣና መጽናናትን የሚሰጥ ነው።

በኢትዮጵያ ለሰብዓዊ መብቶች መከበርና ለሕግ የበላይነት መረጋገጥ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ተግባራዊነት ከመቼውም ጊዜ በላይ አስፈላጊ እንደሆነ በተለያዩ የመንግሥት አካላት መገለጹ ይታወሳል፤ እየተገለፀም ነው። የሰሜን ኢትዮጵያን ጦርነት ጨምሮ ባለፉት አራትና ከዛ በላይ ዓመታት ውስጥ የነበሩ፣ ማንነትን መሠረት ያደረጉ ግጭቶች የሽግግር ፍትሕን አስፈላጊነት ያጎሉ እንደነበሩ የፍትሕ ሚኒስትሩ ዶክተር ጌዲዮን ጤሞቲዎስ መግለጻቸው አይዘነጋም።

ያሉብን ወቅታዊ እና ሀገራዊ ችግሮች ፍትሕ የሚሹ መሆናቸው ግልጽ ነው። በተለይ በሰብዓዊነት ላይ የደረሱና እየደረሱ ያሉ የሕግ ጥሰቶች፣ በተለይ ማንነትን መሠረት ያደረጉ ሕዝባዊ ጥቃቶች በዳይና ተበዳይን ለሕግ በማቅረብ ረገድ አፋጣኝ መፍትሔ የሚሹ ናቸው።

እንደ ሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዓላማና እቅድ በንግግር የሚፈቱ፣ በእርቅ የሚቋጩ በካሣና በተጠያቂነት እልባት የሚያገኙ ሀገራዊ ችግሮች አሉ። የሁሉም ሂደት ፍጻሜ ፍትሐዊነት መሆኑ አጠያያቂ ባይሆንም ጎን ለጎን አብረው የሚመጡ የአንድነት እና የእኩልነት መንፈሶችም በዚህ ሂደት የሚታዩ ናቸው።

እንደ ባለሙያዎች አስተያየት፣ የሽግግር ፍትሕ አራት ዓላማዎች አሉት። በእኚህ ሁሉን አቀፍ ዓላማዎቹ በኩል ነው ተጨባጭ ለውጥን ሊያመጣ የሚችለው። የመጀመሪያው እውነትን መፈለግና ማወቅ፤ መረዳትም ነው። ለየትኛውም ፍትሕ ቀዳሚ መስፈርት ሆኖ የሚያገለግለው እውነት ነው። ከእውነት ተነስተን ነው ፍትሕ ሊያመጡልን ወደ'ሚችሉ፣ ወደ ሌሎች ደረጃዎች የምንሸጋገረው።

ሁለተኛው የተጎዱ ግለሰቦችን፣ አካባቢዎችን መልሶ ማቋቋም ነው። የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲን በተመለከተ ይሄ ፍትሕና ተጠያቂነትን ለማምጣት ሁለተኛው እርከን ነው። በመረጃና በዓይን እማኝ አማካኝነት በተደረሰ እውነት ላይ ተንጠራርተን የሰብዓዊ ጥሰት የደረሰባቸውን ወገኖች ልንታደግ የምንችለው በዚህ ዓይነቱ ሂደት ነው።

ሦስተኛው የሽግግር ፍትሕ ዓላማ የወንጀል ተጠያቂነትን ማስፈን ነው። በእውነት በተመራ አቅጣጫ ሰብዓዊነት ላይ ቆሞ የወንጀል ተጠያቂነት ላይ ይደርሳል። ምንም አሻሚ ነገር የለውም። ሂደቱ በራሱ ቅልብጭ ያለና ለፍትሕ መንገድ የሚጠርግ ሆኖ እናገኘዋለን።

አራተኛውና የመጨረሻው የዓላማ ሂደት ደግሞ ተመሳሳይ ነገር እንዳይከሰት ምን አይነት ለውጥና ማሻሻያ ያስፈልጋል? የሚለው ነው። ይህ እንግዲህ የሕግ ማሻሻያ ወይም የፖሊሲ ለውጥ ሊሆን ይችላል። ከዚህ ባለፈ እውቀትና ምክንያታዊነትን ባስቀደመ መልኩ የምክክርና የተግባቦት ሂደት ላይ ሊመሠረት ይችላል።

በእነዚህ አራት ዓላማዎች መካከል ወሳኝ የሚባል ነገር የለም። አራቱም ወሳኝ ሆነው ለውጥ የሚያመጡ ዓላማ ማሳኪያዎች ናቸው። የሚጠበቀውን አስተማማኝ የፍትሕና የተጠያቂነት ለውጥ ለማስፈን አንዱ ከአንዱ መቆራኘት ይጠበቅበታል። ከእውነት ወደ ሰብዓዊነት፤ ከዛም ወደ ተጠያቂነትና "ቀጣይ ምን ይደረግ?" ወደ'ሚል ተጠየቅ የተሸጋገረ የዓላማ ሂደት ነው ሊታደገን የሚችለው።

ልዩነት ውበት የመሆኑን ያክል አንዳንዶቻችን ለንትርክ እንጠቀምበታለን። ውበት ያደረጉት በብዙ አጊጠውበታል። ልዩነት ያደረጉት እንደዚሁ በብዙ ከስረውበታል። የሆነው ሆኖ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ

**የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ልዩነታቸውን ለነውጥ በተጠቀሙ ግለሰቦችና ቡድኖች ፖለቲካና ፖለቲከኞች ውስጥ ገብቶ በሰብዓዊነት ላይ ጉዳት ያደረሱን የሚሞግት የፍትሕ ውሀ ልክ ነው**

ልዩነታቸውን ለነውጥ በተጠቀሙ ግለሰቦችና ቡድኖች ፖለቲካና ፖለቲከኞች ውስጥ ገብቶ በሰብዓዊነት ላይ ጉዳት ያደረሱን የሚሞግት የፍትሕ ውሀ ልክ ነው።

የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዓለም አቀፍ እውቅና ያለው ከትላንት ወደ ዛሬ የተሻገረ ሞጋች የፍትሕ ሚዛን ነው። ከነባሩ የፍትሕ አካሄድ ጎን የቆመ ግን ደግሞ በተለየ ሁኔታ እውነት እና ፍትሕን ይዞ ለጭቁኖች የሚወግን የሽግግር ፖሊሲ ነው። ከቃሉ እንደምንረዳው የፍትሕ ፖሊሲው ሽግግር ነው። ከጦርነት ወደ ሰላም፣ከሰላም ወደ ተጠያቂነት፣ ከተጠያቂነት ወደ ካሣ የሚደረግ ሽግግር።

የነበሩና ያሉ ሀገራዊ ችግሮችን እያጠራ ወደ ሰላም የሚወስድና አንድነትን የሚፈጥር ሁሉን አቀፍ ተልዕኮ ነው። ዓለም ላይ ሁሉም ሀገራት በሚባል ደረጃ በሽግግር ፍትሕ ጸንተው የቆሙ ናቸው። እንደ ሀገርና እንደፖለቲካ ሥርዓቱ ሁሉም ሀገር የራሱ የሆነ ችግርና መከፋፈል ይኖረዋል።

በዚህ ሳያበቃ ፖለቲካው በወለዳቸው እንከኖች የሚሰቃዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ይኖራሉ። ይሄ ብቻ አይደለም ዘርና ብሔር እየተቆጠረ መርጦ ባልተወለደበት ማንነቱ እየተለየ የሚቀጣ ይኖራል። በዚህም ሳያበቃ በጦርነትና በእርስ በርስ ግጭት የተጎዱ ዜጎች ይኖራሉ። እነዚህ ሁሉ ከዋናው የፍትሕ ሥርዓት ባለፈ ፍትሕ የሚያገኙት በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ በኩል ነው።

የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ መሠረቱ ከዲሞክራሲ ግንባታ ጋር አብሮ ነው። በተለይ የሁለተኛውን የዓለም ጦርነት መገባደድ ተከትሎ በሰብዓዊነት ላይ ለሚደርሱ ፖለቲካዊ ግፎች ተጠያቂነትን ለማስፈር ከየትኛውም ጊዜ በላይ ሩቅ ተጉዟል።

ፖለቲካ ከሀገር ለሀገር ነው። ይሄን እውነት የሳቱ፣ ጽንፍ የረገጡ ፖለቲከኞች ራሳቸውን ለመጥቀም ሲሉ የሚሄዱበት ከሥርዓት ያፈነገጠ አካሄድ ሀገርና ሕዝብን ጎድቶ ያውቃል። ከፍ ሲልም በብሔርና በጎሳ እየተቧደኑ በፖለቲካ አለመግባባት የተፈጠሩ ችግሮች የሰውን ልጅ ለዘመናት አስቃጥቶታል።

ከሀገራት ልምድ እንደምንገነዘበው፣ ከውስን ቡድኖች የመነጩ፣ እነዚህን መሰል ያልተገቡ አካሄዶች እንዲከሽፉና ተጠያቂነት እንዲኖር የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ የአንበሳውን ድርሻ ሲወስድ ቆይቷል። መጪው ጊዜ የሰላምና የአንድነት እንዲሆን ችግሮች በእርቅና በምክክር፣ በውይይትና በተግባቦት እንዲፈቱ የመሠረት ድንጋይ ሆኖ የሠራና እየሠራ ያለ ሰላም መር አስተሳሰብ ነው።

የሽግግር ፍትሕ ጣልቃ ገብነት ማንንም ሲጎዳ አልታየም። በውጪ ሀገራት ጣልቃ ገብነት የሚታይ ሳይሆን የዛን ሀገር ሕግና ደንብ ተከትሎ የሚሠራ ነው። በሌላ መንገድ በሥርዓት ለሥርዓት የሚሠራ የሕግና የደንብ ውጤት ነው። የሚፈራ ከሆነ ሊፈሩት ከቻሉ ወንጀለኞች ብቻ ናቸው የሚፈሩት። ምክንያቱም ወንጀለኞችን ተጠያቂ ለማድረግ የሚሠራ ስለሆነ።

በሀገራችን ባለፉት ጊዜያት አቅም ሆነ በቅርቡ በተካሄደው የሰሜኑ ጦርነት ጎጂና ተጎጂ መኖሩ የማያጠያይቅ ቢሆንም፣ ከዚህ ወዲያ ፍትህ የሚፈልጉና እውነት የራቃቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ስለመኖራቸው እሙን ነው። ለእንዲህ አይነቱ ፖለቲካ ወለድ ችግርና ድምጽ አጥተው ድምጻቸው ለተዋጠባቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ መፍትሔ ነው።

የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ የሥርዓት ሕግ ነው። አይቶና መዝኖ ፈትሾና አረጋግጦ ለፍትሕና ለተጠያቂነት በሩን የከፈተ፣ ሁሉን አቀፍ ጽንሰ ሀሳብ ነው። በተለይ እንደ እኛ ሀገር ላሉ፣ በዘርና በብሔር ለተቧደኑ ተቧድነውም ላላበቁ በብኩርና ለሚጋፉ የሥልጣን ጥመኞች ደንበኛ ማስታገሻ ነው።

ከበርካታ ውጣ ውረዶች በኋላ፣ ዓለም ሰንኮፏን ጥላ በአዲስነት ቀና ያለችው እንዲህ ባለው የሽግግር ፍትሕ እሳቤ ነው። ዩጎዝላቪያና ቺሊ የዚህ ሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ተቋዳሽ ሀገራት ናቸው። አፍሪካ ውስጥም ተመሳሳይ ነገር መኖሩን እንደ ሩዋንዳና ደቡብ አፍሪካ ባሉ ሀገራት መረዳት ይቻላል። በአፍሪካ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ እሳቤ በበረታ መንገድ መቀንቀን የጀመረው የነጮችን የቅኝ ግዛት ተልዕኮ ታኮ ነው።

በተለይ በቅኝ ግዛት ወቅት በነበረውና ከዛ በኋላም በተፈጠረው የነጮች የበላይነት የፈጠረው የመብት ጥሰትና የሰብዓዊነት እንግልት እንዲሁም ደግሞ እንደ ሩዋንዳ ባሉ፤ በዘርና በብሔር የማንነት ጥያቄ በተነሳባቸው ሀገራት የሽግግር ፍትሕ ባለውለታ አልነበረም ማለት አይቻልም።

የሩዋንዳ የዘር ፍጅት በሽግግር ፍትሕ ነው የተቋጨው። በደቡብ አፍሪካ የአፓርታይድ ሥርዓት ማብቂያ ከማግኘቱም ባለፈ የሰብዓዊ ጥሰት የፈጸሙ አካላት በዚህ የሽግግር ፍትሕ በኩል ተዳኝተዋል። ቺሊና አንዳንድ የላቲን አሜሪካ ሀገራት ይሄን መንገድ በመምረጥ ተበዳይን በመካስ፣ በዳይ ለፍርድ የሚቀርብበትን ሂደት ሥራ ላይ አውለዋል።

በቀላል አማርኛ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ "የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ" ልንለው እንችላለን። የዲሞክራሲ ግንባታ ሂደት ግን ከፍ ብለን በጠቀስናቸው አራት የፍትሕ ፖሊሲ ዓላማዎች በኩል የሚያልፍ ነው። ያም በእውነት፣ በሰብዓዊነት፣ በተጠያቂነትና ተመሳሳይ ችግሮች እንዳይፈጸሙ በማድረግ በኩል ነው።

ፍትሕን በማስፈን፣ ተጠያቂነትን በማለማመድ ከሕዝብ ወደ መንግሥት፤ ከመንግሥት ወደ ሕዝብ የሚወርድ የሽግግር ፍትሕ ያስፈልጋል። መንግሥት እየጠየቀና ሕዝብ እየተጠየቀ፣ መንግሥት እየተናገረና ሕዝብ እያዳመጠ የሚመጣ የተሟላ የሽግግር ፍትሕ የለም።

የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ያለሕዝብ ተሳትፎ ምንም ነው። ለሕዝብ ፍትሕ እስከቆመ ድረስ ሕዝብን ባሳተፈና ባማከለ መንገድ ነፍስ የሚዘራ ነው። ነጻ በሆነ መንገድ ሕዝብን ቀርቦ በማወያየት እንዲሁም ለሥራው ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረውለት በዚህ መሰል እንቅስቃሴ ውስጥ የሚያተርፍ እንጂ በጫናና በመሰል አካሄዶች ወደ ፍትሕ የሚያመራ አይደለም።

ሕዝብ ካለፈው ተምሮ መጪውን ተስፋ በማድረግ የጋራ ሀገር እንዲገነባ በሕዝብና በመንግሥት መካከል የገባ የእርቅና የተጠያቂነት ፖሊሲ ነው። ይህ ፖሊሲ እንደ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በእርቅና በአስታራቂነት የሀገርን ቀጣይነት የሚያረጋግጥ ሲሆን፤ ጎን ለጎንም በሀገርና በሰብዓዊነት ላይ ጥሰት የፈጸሙ አካላትን እንዲጠየቁ አቅጣጫ የሚያስቀምጥም ነው።

የፖለቲካ አስተሳሰብ ለሁሉም ማኅበረሰብ እኩል ካልወገነ ይሄ በራሱ እንደመብት ጥሰት የሚቆጠር ነው። ከመብትና ከግዴታ ጋር በተያያዘ አስገዳጅ በሆነ ሥርዓት የዜጎች መብት ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ከሆነ ጉዳዩ የመብት ጥሰት ያለበት የአንድ ወገን ውግንና ይሆናል።

እንዲህ ያለው ፖለቲካዊ ሥርዓት ነጻና ፍትሐዊ፣ ተጠቃሚነትንም ያረጋገጠ ማኅበረሰብ መፍጠር ላይ ጥያቄ ይነሳበታል። እነዚህን መሰል ክፍተቶች ዜጎች በፖለቲካ ተጽዕኖ ውስጥ እንዲወድቁ ከማድረጉም ባለፈ የመብት ጥሰት ሆኖ የሚቀመጥ ነው የሚሆነው። ይህን መሰል ሥርዓት እንዲስተካከል ካስፈለገ የሽግግር ፍትሕን የመሰለ ብሔራዊ ምክክር ያስፈልጋል።

ሀገራችን በአሁኑ ሰዓት ማኅበራዊና ሀገራዊ ለውጥን በሚያመጡ በሁለት ንቅናቄዎች ውስጥ ናት። አንዱ ወደ ሥራ ሊገባ እያኮበኮበ ያለው የብሔራዊ ምክክር ኮሚሽን ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ ለጽሑፌ መነሻ ሀሳብ ያደረኩት የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ነው። ሁለቱም አሁን ላለችው ሀገራችንና አሁን ላለው ብሔር ተኮር ፖለቲካ የመፍትሔ ምንጭ ይሆናሉ ተብሎ ይታመናል።

የሁለቱም የንቅናቄ ዓውድ ፍትሕን ማስፈንና ተጠያቂነትን ማምጣት ነው። ተራማጅ በሆነ የሀሳብ የበላይነት ሰላም ተኮር በሆነ እንቅስቃሴ ነውጠኞችን ማጥራትና ተጎጂዎችን መካስ ላይ ያተኮረ ነው። የሁለቱም ንቅናቄ ማዕከል ሕዝብ ነው። ሕዝብን ጠይቆና አወያይቶ በመረጃ በተደገፈ እውነት ወደፊት መቀጠል ነው።

ሀገራችን ሕልውናዋ ጥያቄ ውስጥ በገባበት በዚህ ሰዓት ሰላም ለማምጣትና ፍትሕን ለማስፈን የእነዚህ ሁለት ኃይሎች ወደ ሥራ መግባት ብዙ ነገሮችን ያስተካክላል። ከድህነትና ከእርስ በርስ ጦርነት በቀር ዘመኑን የሚመጥን የጎላ ታሪክ የሌላት ሀገራችን ሰንኮፏን ጥላ ወደ ፊት እንድትቀጥል ሕዝባዊ ምክክር ማስፈለጉ እሙን ነው።

ከዚህ በተጓዳኝ እንደ ነውር የምንቆጥራቸውንና የምናፍርባቸውን የእርስ በርስ አለመግባባቶች በመፍጠር በሀገርና በሕዝብ ላይ ጉዳት ያደረሱ አካላትን ለሕግ ከማቅረብ አኳያ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን፤ መጪው ጊዜ በእርቅና በፍቅር፣ በሰላምም የምንቀበለው የጋርዮሽ እንዲሆን ከእነዚህ ሁለቱ አበይት ርዕሰ ጉዳዮች ጋር ሕዝብ መተባበር ግዴታው ይሆናል።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# በኦሮሚያ ክልል የዝናቡና ግብርና ሥራው የተመቻቹበት የበልግ ወቅት

ስምስም መንግሥቱ

ከየካቲት እስከ ግንቦት፣በበጋው ደግሞ ጥቅምትና ኅዳር ወራት ያሉት ወቅቶች መደበኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑ ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ሶማሌ ክልል፣ ኦሮሚያ ክልል ቦረናና ጉጂ ዞኖች፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰብና ሕዝቦች ክልል ቆላማ አካባቢዎች ወሳኝ መሆናቸውን ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የተገኘው መረጃ ያመለክታል። በእነዚህ አካባቢዎች ባለፈው ዓመት በነዚህ ወቅቶች ይጠበቅ የነበረው ዝናብ ባለመጣሉ አካባቢዎቹ ለከፋ ድርቅ ተጋልጠው እንደነበር ይታወቃል፤በድርቁም የሰው ሕይወት ባያልፍም ከፍተኛ ጉዳት ግን ደርሷል፤ በተለይም በኦሮሚያ ክልል ቦረና በሶማሌ ክልል የተለያዩ ዞኖች በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ከብቶች ማለቃቸውን መረጃዎች አመልክተዋል። በቅርቡም በድርቁ ከ6 ሚሊዮን በላይ ከብቶች መሞታቸውን መረጃዎች አመላክተዋል።

ድርቁ አንዳንድ የበልግ አብቃይ አካባቢዎችንም በእጅጉ ማጥቃቱ ይታወቃል። በእነዚህ አካባቢዎች ወይ ዝናቡ ባለመጣሉ አልያም ዘግይቶ በመጣሉ የተነሳ በግብርና ሥራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳረፉን መረጃዎች ያመለክታሉ።

በተያዘው የበልግ ወቅት መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ መጣሉን የኢትዮጵያ ሚትዮሮሎጂ ኢንስቲትዩት መረጃ ያመለክታል። የጣለው ዝናብ ለእርሻ ሥራም ለከብቶች መኖ ለማግኘትም በአረንጓዴ አሻራ ለተተከሉ ችግኞችና ለአጠቃላይ የአካባቢ ጥበቃ ሥራ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩን ነው የሚትዎሮሎጂ ባለሙያዎች የሚናገሩት።

የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩትም የአየር ጠባይን በመተንተን አስቀድሞ መረጃ ሲሰጥ ቆይቷል። የበልግ ዝናብ ሊዘገይ እንደሚችል፣ሲመጣም ሊኖረው የሚችለውን አዎንታዊ ተጽዕኖ በየጊዜው ያሳውቅም ነበር፤ በዚህ ላይ በመመሥረትም ነው የበልግ የግብርና ሥራ በተለያየ መንገድ ቅድመ ዝግጅት ተደርጎ ወደ ሥራ የተገባው።

በሁሉም የበልግ አብቃይ የሀገሪቱ አካባቢዎች ጥሩ የሚባል የዝናብ ስርጭት እንደተገኘ ከየአካባቢው የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ። የግብርና ሥራውም በቅድመ እቅዱ መሠረት እየተከናወነ እንደሆነም እየተጠቆመ ይገኛል።

የበልግ የግብርና ሥራ ሦስተኛ ወሩን ጀምሯል። ስለ ቅድመ እቅዱና አሁን ስላለው ወቅታዊ ሁኔታ፣በግብርና ሥራው ለሚያጋጥሙ ያልተጠበቁ ችግሮች ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ስላለው ዝግጁነት እንዲሁም ስለሚጠበቀው ውጤት የበልግ አብቃይ ከሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች አንዱ የሆነውን የኦሮሚያ ክልል እንቅስቃሴ በዛሬው የግብርና ዓምዳችን እንቃኛለን።

የክልሉ ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ በሪሶ ፈይሳ እንዳሉት፤ ወደ 10 የሚሆኑት የክልሉ ዞኖች በልግ አብቃይ ናቸው። በዞኖቹም ወደ አንድ ነጥብ አንድ ሚለዮን ሄክታር መሬት በተለያየ ዘር በመሸፈን ምርት ለመሰብሰብ ነው በቅድመ እቅድ የተያዘው። በቅድመ እቅድ ሥራውም ለአርሶ አደሩና ሙያዊ ድጋፍ የሚሰጡ የግብርና ባለሙያዎችን በሥልጠና የማዘጋጀት ሥራ በማከናወን ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ተካሂዷል፤ የግብዓት አቅርቦትም አስቀድሞ ነው የተከናወነው። ክልሉ የግብዓት አቅርቦት ሥራውን ያከናወነው የመኸር የግብርና ሥራን ታሳቢ በማድረግም ጭምር ነው።

በዚሁ መሠረትም ወደ ሰባት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ለማስገባት አቅዶ በማስገባት ላይ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥም ወደ ሦስት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ገብቶ ለበልጉ ሥራ እንዲውል እየተደረገ ነው። የፀረተባይና ተያያዥ የሆኑ የግብርና ግብአቶችም በበቂ ሁኔታ እየቀረቡ ይገኛሉ። ግብአቶቹም በገበሬዎች መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ዩኒየኖች አማካኝነት ለአርሶ አደሩ ተደራሽ እንዲሆን ተደርጓል።

እሳቸው አንዳሉት፤ በዚህ በኩል በእስካሁኑ የበልግ ግብርና ሥራ ያጋጠመ ክፍተት የለም። በምርጥ ዘር አቅርቦት ረገድም ቢሆን የበቆሎ ምርጥ ዘር ወደ 47ሺ ኩንታል፣ የስንዴ ምርጥ ዘርም ከ20ሺ ኩንታል በላይ ተሰራጭቷል። የማሰራጨቱ ሥራ በአግባቡ እንዲከናወንም በዞንና በወረዳ ግብረ ኃይል ወይም ታስክ ፎርስ ተቋቁሞ ነው እየተሠራ ያለው።

ግብረ ኃይሉ መረጃዎችን በመሰብሰብ ችግሮች በሚያጋጥሟቸው አካባቢዎች በመገኘት የሚፈታ ነው ያሉት ኃላፊው፣ ከግብዓት አቅርቦት ጀምሮ ያለው ሥራ በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ በመሆኑ የበልግ የግብርና ሥራ ውጤታማ እንደሚሆን ከሥራው ሂደት መገምገም ተችሏል

**በኦሮሚያ ክልል የበልግ የግብርና ሥራው በቅድመ እቅዱ መሠረት እየተከናወነ ይገኛል። በእስካሁኑ ሥራም በእቅድ የተያዘው አንድ ነጥብ አንድ ሚሊየን ሄክታር መሬት የማረሥ ሥራ ተጠናቅቋል። እስከ አሰፈው ሳምንት መጀመሪያ ድረስም 700ሺ ሄክታር መሬት በተለያየ የሰብል ዘር ተሸፍኗል**

ይላሉ።

በዚህ የበልግ ወቅት በስፋት የሚከናወነው የሰብል ልማት በቆሎና ስንዴ እንደሆነ ይታወቃል።ባለፉት የግብርና ወቅቶች ደግሞ የበቆሎ ምርጥ ዘር አቅርቦት ላይ ክፍተት እንዳለ በስፋት ይነሳ ነበር። ይነሳ የነበረው ክፍተትም የበቆሎ ምርጥ ዘር አቅርቦት ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል እንደመሆኑ ክልሉ በፀጥታ ስጋት ውስጥ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እንደሆነ ይታወሳል።

እዚህ ላይ አሁን ስላለው ነባራዊ ሁኔታ ለአቶ በሪሶ አንስተንላቸው በሰጡት ማብራሪያ ፤ ከበቆሎ ምርጥ ዘር አንዱ የሆነው ‹ሊነር› የሚባለው የበቆሎ ምርጥ ዘር ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ወለጋ፣ ጅማ ላይ ነው የሚገኘው ሲሉ ጠቅሰው፣ ይህ ዘር በስፋት በአርሶ አደሩ የሚፈለግ በመሆኑ አቅርቦቱ ከፍላጎቱ ጋር የተጣጣመ አለመሆኑ እንጂ ዘሩን መሰብሰብ ተችሏል ብለዋል። የሚፈለገውን ያህል ግን አይደለም ሲሉም ጠቁመዋል።

አቶ በሪሶ ይህን ዘር ሊተኩ የሚችሉ ምርጥ ዘሮች ለማቅረብ ጥረት እየተደረገ መሆኑንም ጠቅሰው፣ ዘሮቹ በምርታማነታቸው፣በውስጣቸው በያዙት ንጥረ ነገር፣የምግብ ፍላጎትን በማሟላትና በገበያ ላይ ባላቸው ተፈላጊነት የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል ይላሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ በዚህ ረገድም ባለሙያውም ሆነ አርሶ አደሩ በቂ ግንዛቤ ይዞ ዘሮቹ ጥቅም ላይ እንዲውሉ እየተደረገ ነው። ከአንድ መቶ ሺ ኩንታል በላይ እንዲዘጋጅ ተደርጎ ከዚህ ውስጥም ወደ 47ሺ ኩንታል ተሰራጭቷል። ከምርጥ ዘር ጋር ተያይዞ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በዚህ መንገድ አማራጮችን በመፈለግ ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ሲሆን፣ የግብርና ሥራ ቅድመ ዝግጅቱ በዚህ መልኩ ነው እየተከናወነ የሚገኘው።

በክልሉ የበልግ የግብርና ሥራው በቅድመ እቅዱ መሠረት እየተከናወነ እንደሆነ የጠቆሙት የክልሉ ግብርና ቢሮ የእርሻ ዘርፍ ኃላፊ አቶ በሪሶ፣ በእስካሁኑ ሥራም በእቅድ የተያዘው አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት የማረስ ሥራ ተጠናቅቋል ማለት ይቻላል ሲሉ ገልጸዋል። እስከ አለፈው ሳምንት መጀመሪያ ድረስም 700ሺ ሄክታር መሬት በተለያየ የሰብል ዘር መሸፈኑን አስረድተዋል።

እንደ ክልሉ ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ ገለጻ፤ ከቅድመ እቅድ እስከ ክንውን ያለው ሥራ ግምገማ የአርሶ አደሩ ዝግጁነት፣የባለሙያው ድጋፍና አመራሩም እየሰጠ ያለው አቅጣጫ በድምሩ ውጤታማነቱን ያመላክታል። ከቀደሙት ተመሳሳይ ወቅቶች ጋር የተከናወነው ሥራ በንጽጽር ሲቀርብ በሁለንተናዊ እንቅስቃሴም ሆነ ባለው የዝናብ ስርጭት የተሻለ ነገር መኖሩን በግምገማ ተለይቷል።

በኦሮሚያ ክልል በልግ አብቃይ ከሚባሉ አካባቢዎች አርሶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር የሚኖርበት ጉጂ ዞን አንዱ ነው። በአካባቢው በተከታታይ ለአራት ዓመታት ባጋጠመ የዝናብ እጥረት ለድርቅ በመጋለጡ እንስሳት መኖ ማጣታቸው፣ አርሶአደሩም ባለማምረቱ በእጅጉ መጎዳቱ ይታወቃል። በዚህ የበልግ ወቅት አካባቢው ላይ ስላለው ነባራዊ ሁኔታ አቶ በሪሶ ላቀርብንላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ በምሥራቅ ጉጂም ሆነ በምዕራብ ጉጂ ላይ የዝናብ ስርጭቱ ጥሩ ነው መሆኑን ነው የገለጹልን። ምዕራብ ጉጂ በዚህ ወቅት የበቆሎና ስንዴ ልማቱ በስፋት እየተከናወነ መሆኑን ጠቅሰው፣ ዘንድሮ ከአካባቢው ከፍተኛ የሚባል ምርት እንደሚጠበቅም ጠቁመዋል። የዘር አቅርቦቱም በአርሶ አደሩ ጭምር እየቀረበ መሆኑን ተናግረዋል። በከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢም ለእንስሳቱ የሚሆን የሳር ግጦሽ በዝናቡ አማካኝነት እየተገኘ ነው ያሉት ኃላፊው ፣ በአካባቢው የክልሉ መስኖና አርብቶ አደር ቢሮ በኃላፊነት እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

በግብርና ሥራ ውስጥ ያልተጠበቁ የተፈጥሮ ክስተቶች መኖራቸው ተፈጥሮዓዊ ነው። ሰው ሠራሽ ችግርም ቢሆን በሥጋትነት ይጠቀሳል። ግን ዝግጁ መሆን ይጠበቃል። በዚህ ረገድ ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ስላለው ዝግጁነትም አቶ በሪሶ ሲያብራሩ ፡- በተፈጥሮ ከሚጠበቁት ወይንም እንደስጋት ከሚነሱት የዝናብ ማነስና መብዛት አንዱ እንደሆነ ይናገራሉ።

በዚሁ መሠረትም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሚትዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት በአንዳንድ ቦታ የዝናብ መብዛት፣ በአብዛኛው ግን መደበኛ የዝናብ ስርጭት እንደሚኖር ትንበያ መስጠቱን አቶ በሪሶ አስታውሰዋል። ቢሮው የትንበያ መረጃውን መሠረት በማድረግ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ዝናብ በሚበዛባቸው አካባቢዎች ውሃ ከማሳ ውስጥ የማስወጣትና በተለያየ ዘዴ የሰብል ልማት ሥራው እንዲከናወን እየተሠራ እንደሆነ አስረድተዋል። የልማት ሠራተኛው ከአርሶ አደሩ እንዳይርቅ፣ አርሶ አደሩም ተግቶ እንዲሠራ በማድረግ በዝናብ መብዛት በኩል ያለውን ስጋት ለመቀነስ ዝግጅት መደረጉን ገልጸዋል።

እንደ አቶ በሪሶ ማብራሪያ፤ የዝናብ እጥረት ያጋጥማቸዋል ተብለው በተለዩት አካባቢዎችም የሚደረገው ጥረት ተመሳሳይ ነው። አርሶ አደሩ የውሃ ጠብታን በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲያውል ግንዛቤ በመፈጠሩ በተለያየ አጋጣሚ የተገኘውን የዝናብ ጠብታ ወደ ማሣ በማስገባት ጥቅም ላይ እንዲያውል በክትትልና ድጋፍ እየታገዘ እንዲከናወን አቅጣጫ ተቀምጦ እየተሠራ ነው።

በዚህ ወቅት ሰው ሠራሽ ችግር ተብሎ እንደስጋት የሚነሳው ከአለመረጋጋት ጋር ተያይዞ ያለው የፀጥታ ሁኔታ እንደሆነም ኃላፊው ጠቁመው፣ ይህንንም ባለው የመንግሥት መዋቅርና በተደራጀ አሠራር እንዲሁም የግንዛቤ ሥራዎችን በመሥራት ለመፍታት የሚደረግ ጥረት ይሆናል ብለዋል።

እሳቸው አንዳሉት፤ እስካሁን ባለው ግን የበልግ የግብርና ሥራን የሚያስተጓጉል የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሠራሽ ችግሮች አላጋጠሙም። አሁን እየተደረገ ባለው የበልግ የግብርና ሥራም በሁሉም ሰብል 22ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ነው በቅድመ እቅድ የተያዘው። በክልሉ በተፈጠረው ምቹ የአየር ፀባይና ከላይ እስከታች በንቅናቄ እየተከናወነ ባለው ሥራ እቅዱ ይሳካል የሚል እምነት ተጥሏል።

ስለግብርና ሜካናይዜሽን አጠቃቀም በስፋት የሚነሳው በመኸሩ እና ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በመንግሥት ቁርጠኝነት በተጀመረው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የግብርና ወቅቶች ነው። በበልጉ ላይ ያለው ተሞክሮ ፣ምን እንደሚመስል አቶ በሪሶ እንደገለጹት፤ በክልሉ በየትኛውም የግብርና ሥራ ወቅቶች የግብርና ሜካናይዜሽንን መጠቀም የተለመደ ነው። በልግ አብቃይ በሆኑ የክልሉ አካባቢዎች አርሲና ባሌ፣ምሥራቅና ምዕራብ ሐርጌና ጉጂ ዞኖች፣ ምሥራቅ ሸዋ በከፊል የግብርና ሜካናይዜሽን በስፋት ይጠቀማሉ። ለበልጉ የእስካሁን የግብርና እንቅስቃሴ ጥሩ የሆነ ውጤት መታየት የግብርና ሜካናይዜሽን ከፍተኛ እገዛ አድርጓል።

አቶ በሪሶ አያይዘውም ከዚህ የበልግ ግብርና ሥራ ጎን ለጎን የሚጠበቀው ሥራ የደረሰውን የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት አዝመራ ከሥር ከሥር መሰብሰብ ነው፤ ይህም እየተከናወነ ይገኛል ብለዋል። ወደ አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሄክታር ነው ለበጋ ስንዴ መስኖ ልማት ተዘጋጅቶ በዘር የተሸፈነው የሚሉት አቶ በሪሶ፣ ከዚህ ውስጥ ከሦስት መቶ ሺ ሄክታር መሬት በላይ የሚሆነው ሰብል ለመሰብሰብ መድረሱን አስታውቀዋል። ከዚህ ውስጥም ከግማሽ ሄክታር መሬት በላይ ከሚሆነው ምርት መሰብሰቡን ጠቅሰው፣ እንቅስቃሴውም ጥሩ የሚባል ነው ይላሉ።

ክልሉ የሁለቱን የግብርና ሥራ ወቅቶች ብቻ ሳይሆን ለዋናው የመኸር የግብርና ሥራም ከወዲሁ እየተዘጋጀ መሆኑንም አቶ በሪሶ ጠቅሰዋል። በመኸሩ ወደ አንድ መቶ ሺ ሄክታር መሬት በተለያየ ሰብል ለመሸፈን ዝግጅት መደረጉን አስታውቀዋል። ክልሉ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ሀገራዊ የምርት መጠንን ከፍ ለማድረግ በግብርና ሥራው ከባለሙያ ጀምሮ እስከ በላይ አመራር ትኩረት መሥጠቱን ጠቅሰው፣ አርሶአደሩም ቁርጠኛነቱን የሚያሳዩ ትግበራዎች እያሳየ እንደሚገኝ ገልጸዋል። ይህ የጋራ ርብርብም ለስኬት የሚያበቃ እንደሆነም አስረድተዋል።

ተከታታይ የሆነው የግብርና ሥራ ያልተቆራረጠ ክትትልና ድጋፍ፣የግብዓት አቅርቦት ይፈልጋል። በዚህ የተነሳም ጫና ሊያሳድር እንደሚችል ይገመታል። ጫናው በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ በሚጠበቀው ውጤት ላይ ሊያሳድረው የሚችለው ተጽዕኖ ይኖር እንደሆንም አቶ በሪሶ ተጠይቀው፤ ‹‹ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚባክን ጊዜ መኖር የለበትም፤ በጫና ውስጥም ሆኖ ውጤታማ መሆን ይጠበቃል።›› ሲሉ መልሰዋል። በዚህ እሳቤ ነው ከላይ እስከ ታች በጋራ ሆነን እየሠራን ያለነው ሲሉም ነው ያረጋገጡት። አርሶ አደሩም እንዲሟላለት ለሚፈልጋቸው ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት የሚቻለው ሠርቶ ውጤት ማምጣት ሲቻል ነው ያሉት ኃላፊው፣ ‹‹በሥራ እየታየ ያለው ውጤትም ሞራል የሚገነባና በዚህ መንፈስ ነው እየተንቀሳቀስን ያለነው ›› ብለዋል።

በበልግ የግብርና ሥራ እንደሀገር የተያዘው እቅድ ሁለት ነጥብ ሁለት ሄክታር መሬት በማረስ በዘር ለመሸፈን እንደሆነ ከግብርና ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመለክታል። በዚህ የበልግ የግብርና ሥራ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው ደግሞ አነስተኛ ይዞታ ባላቸው የአርሶ አደሮች ማሳ ላይ የሚከናወነው ሥራ ነው። የበልጉ ምርት አምስት በመቶው ለሀገራዊ ምርት ፍጆታ እንደሚውል ከሚኒስቴሩ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። በምርትም ወደ 24 ሚሊዮን ኩንታል ለመሰብሰብ በእቅድ ተይዟል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

## ተስፋ የሰነቀው የወንዶች አዳሪ ትምህርት ቤት

ጽጌረዳ ጫንያለው

አዳሪ ትምህርት ቤቶች ልዩ ችሎታና ተሰጥዖ ያላቸውን ተማሪዎች በመለየት ልዩ ድጋፍ በማድረግ ይታወቃሉ። እንደ አፍሪካ ባሉ አገራት ግን አዳሪ ትምህርት ቤቶች የሚፈለገውን ያህል ትኩረት እንዳልተሰጣቸው ይነገራል። በኢትዮጵያም ቀድሞ ለአዳሪ ትምህርት ቤቶች ይሰጥ የነበረው ትኩረት አሁን ላይ እየተሰጠው ነው ለማለት የሚያስደፍር ነገር የለም።

የአዳሪ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ጥራትን ከማረጋገጥ አኳያ የማይተካ ሚና እንዳላቸው ግን ተደጋግሞ ሲነገር ቆይቷል። ለዚህም ማሳያም የዘንድሮ የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ የፈተና ውጤት ነው።በዘንድሮው ሀገር አቀፍ ፈተና አዳሪ ትምህርት ቤቶች አነሰ ቢባል 90 በመቶ ተማሪዎቻቸውን ለከፍተኛ ትምህርት ማብቃታቸው ይታወሳል። ከነዚሁ ትምህርት ቤቶች ከ50 በመቶ በላይ ያመጡም በርካቶች ናቸው።እነዚህ የዛሬ የአዳሪ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በመጪዎቹ ዘመናት በማናቸውም መስኮች ሀገርን በብቃት ፊት አውራሪ ሆነው ያገለግላሉ ተብለው ተስፋ ተጥሎባቸዋል።

እነዚህ ትምህርት ቤቶች ከእውቀት ማዕዳቸው ውስጥ ለተማሪዎች ምርጡን መስጠት የሚያስችል አቅም ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ፣ ተማሪዎች ንቃተ ሕሊናቸውን እንዲያዳብሩ፣ የመወዳደር ፍላጎትን ባሕል የሚያደርጉም ናቸው።ትምህርት ቤቶቹ ከመደበኛ ትምህርት በተጨማሪ ሌሎች እንቅስቃሴዎች ተግባራዊ የሚደረጉባቸው፤ ወደ ነፃነት ልምምድ ውስጥ የሚገቡባቸው የእውቀት ደብሮች ስለሆኑ በሁሉም የተመረጡ ናቸው።

ትምህርት ቤቶቹ ተማሪዎች የነፃነት ስሜትን እንዲያገኙ፣ አዲስ ጓደኝነትን እንዲፈጥሩና በዙሪያቸው ካሉት ጋር ማኅበራዊነትን እንዲመሠርቱ ዕድል የሚሰጡ ናቸው።


አዳሪ ትምህርት ቤቶች ሌላ ቦታ የማይገኙ የትምህርት እድሎችን የሚሰጡም ናቸው።ተማሪዎች በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ተግባርን እንዲከውኑም ያበረታታሉ።እነዚህ ሁሉ ጥቅሞች ያሏቸው በመሆናቸውም እንደሀገር አሁን ላይ ካሉት በተጨማሪ 50 ዘመናዊ፣ ደረጃቸውን የጠበቁ አዳሪ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት ታስቧል።የትምህርት ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በአንድ ወቅት እንደተናገሩት፤ እነዚህን ትምህርት ቤቶች መገንባት እንደሀገር በርካታ ጠቀሜታዎችን ያስገኛል።በመሆኑም የግንባታ ፕሮጀክት ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ ተገብቷል።ዘመኑን የጠበቀ ሥራ ለማከናወን በማሰብም ከዲዛይን ዝግጅት ጀምሮ የኢትዮጵያ አርክቴክቶች ማኅበር ተሳትፎበታል።

በኢትዮጵያ 48ሺህ ትምህርት ቤቶች ቢኖሩም 98 በመቶው ከደረጃ በታች እንደሆኑ የጠቆሙት ሚኒስትሩ፣ ኢትዮጵያ ደረጃቸውን የጠበቁ የአካልና የአዕምሮ ማበልጸጊያ ትምህርት ቤቶች ያስፈልጓታል። ከእነዚህ መካከል ደግሞ አዳሪ ትምህርት ቤቶች እንደ አንድ የማበልፀጊያ ማዕከል መወሰድ ይኖርባቸዋል።ያሉትን ማሳደጉ እንደ ተጠበቀ ሆኖ፣ በአዲስ መልኩ ዘመናዊ የሆኑ አዳዲስ አዳሪ ትምህርት ቤቶችን መገንባት እንደሚገባም ተናግረዋል።

የአዳሪ ትምህርት ቤቶቹ ሥራ በሀገር አቀፍ ደረጃ እቅድ ቢያዝም በክልል ደረጃም መሠራት እንዳለበት መግባባት ላይ ተደርሷል።በዚህም በርካቶች ውጤታማ ሥራ እያከናወኑ ነው።ይህን ተግባራዊ ለማድረግም የልማት ማኅበራት ሚና አስፈላጊ ነው። መንግሥት ብቻ ሥራውን መውሰድ የለበትም።

በዚህ ረገድ አዲስ አበባ ላይ የልማት ማኅበራት ባለመኖራቸው ይህንን ማድረግ አልተቻለም።ስለዚህም የከተማ አስተዳደሩ ኃላፊነቱን ወስዶ መሥራት እንደሚኖርበት ይጠበቃል።በዚህም ነባር ትምህርት ቤቶችን ወደ አዳሪ ትምህርት ቤቶች በመቀየር፣ ተማሪዎችን በጾታ ከፍሎና እስከ 62 ሚሊዮን ብር በጀት መድቦ እንዲሠራ ሆኗል፡፡

ከእነዚህ መካከል አንዱ የሆነው የወንዶች አዳሪ ትምህርት “ገላን ልዩ የወንዶች ሁለተኛ ደረጃ አዳሪ ትምህርት ቤት” ነው። ትምህርት ቤቱ የተመሠረተው



ፎቶ ፡- አዮብ ተፈሪ

ከዛሬ አራት ዓመት በፊት በ2012 ዓ.ም ነው።

አዳሪ ትምህርት ቤቱን በርዕሰ መምህርነት የሚያገለግሉ አቶ ካሳሁን መርጋ እንደሚናገሩት፤ ትምህርት ቤቶች መኖራቸው እንደ ሀገር ጥቅም አለው።አንዱና ዋነኛው ጥቅም ደግሞ የነገ ሀገር አስቀጣይ ትውልዶችን በብቃት ማፍራት ነው።ከጊዜ ወደ ጊዜ እየታየ የመጣው የትምህርት ጥራት ጉዳይ በመደበኛ ትምህርት ቤቶች ብቻ የሚቀጥል ከሆነ ብዙ ነገር ያሳጣናል።እናም አዳሪ ትምህርት ቤቶችን ልምድ መቀመሪያ ማድረግ መቻል ብዙ ነገሮችን ይለውጣል።

መንግሥት ከትምህርት ሽፋንና ተደራሽነት አንጻር እስከዛሬ ብዙ ሠርቷል።ዛሬ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተማሪዎች ትምህርት ቤት ገብተዋል።ሆኖም የጥራቱ ነገር አሁንም አንገብጋቢ ነው።እናም ትኩረቱን ወደዚህ በማዞር የተለያዩ መንገዶችን እየተከተለ የሚገኝ ሲሆን፤ አንዱም አቅም እያላቸው የተሻለ የትምህርት ዕድል ላላገኙ ተማሪዎች ዕድል በመስጠት፤ በመንግሥት ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎችን በተለየ አቅማቸው መልምሎ ወደ አዳሪ ትምህርት ቤቶች በማስገባትና ልዩ ድጋፍ በማድረግ ማብቃት ነው።

የአዳሪ ትምህርት ቤቶችን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የተመረጡ መምህራን ሳይቀር ይቀጠራሉ።የገላን ልዩ የወንዶች ሁለተኛ ደረጃ አዳሪ ትምህርት ቤት መምህራንም በዚህ መልክ የመጡ ናቸው።በኮተቤ ዩኒቨርሲቲ በተዘጋጀ ፈተና ውስጥ አልፈው የተማሪዎችን አቅም እየገነቡም ይገኛሉ።እየወረደ ያለውን የትምህርት ጥራት ለማሻሻል ካሉት አማራጮች መካከል አንዱ ይህ እንደሆነ አያጠያይቅም የሚሉት አቶ ካሳሁን፤ አቅሙ ኖሯቸው የሚያግዛቸው ቤተሰብ የሌላቸውን ልጆች ከማስተማርና የነገ ተስፋዎች እንዲሆኑ ከማድረግ አኳያ እነዚህን የመሰሉ አዳሪ ትምህርት ቤቶች እጅግ አስፈላጊ ናቸው።በተጨማሪም ትምህርት ቤቶቹ የማቋረጥ ምጣኔን ከመቀነስ፤ ልዩ ተሰጥዖን ከማውጣት፤ አዳዲስ ነገሮችን ለሀገር ከማበርከት አኳያ የማይተካ ሚና ይኖራቸዋል።

የገላን አዳሪ ትምህርት ቤት በዚህ አይነት መልኩ መደራጀቱና ድጋፍ እየተደረገለት መቀጠሉ ለተከታታይ ሦስት ዓመታት ምንም ተማሪ ሳይወድቅ ወደ ዩኒቨርሲቲ ማስገባት ችሏል።በተጨማሪም ተማሪዎች የውጪ እድል አግኝተው የነገ ተስፋቸውን እንዲያለመልሙ አግዟል።አዳሪ ትምህርት ቤቱ ከሌሎች ለየት የሚያደርገው በርካታ መለያዎች ያሉት እንደሆነ የሚያነሱት ርዕሰ መምህሩ፤ አንዱ የወንዶች አዳሪ ትምህርት ቤት መሆኑን ይጠቅሳሉ።እንደ ሀገርም ብቸኛ መሆኑን ያብራራሉ።

ትምህርት ቤቱ በአደረጃጀቱም ልዩ ነው።ለምሳሌ፡- በዋና ርዕሰ መምህር ብቻ ሳይሆን በሦስት ምክትል ርዕሰ መምህራን ጭምር የሚመራ ሲሆን፣ ሌሎች ጋር ያሉት ምክትል ርዕሰ መምህራን እንደሚሠሩት አይነት ሥራም አይደለም የሚሠሩት።ልክ እንደ ዩኒቨርሲቲዎች ሁሉም የሚመሩት ዘርፍ አላቸው። የተማሪዎች አገልግሎት፣ ፋይናንስና አስተዳደር እንዲሁም አካዳሚክ ዘርፍ በሚል የተከፋፈሉ ሚናዎች አላቸው።

ትምህርት ቤቱ “ዜሮ ክላስ” የሚባል ትምህርት አለው።ክፍል መግባት ከመጀመሩ በፊት የሚሰጥ የትምህርት አይነት ነው።በዚህ ተጠቃሚ የሚሆኑት ደግሞ 12ኛ ክፍልና የተወሰኑት 11ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው።በተጨማሪም ከመደበኛው ክፍለ ጊዜ ውጪ፣ ከሰዓት በኋላም ሁለት ክፍለ ጊዜ የትምህርት መስጪያ ተደርጎ ይሠራል።የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ለፈተና ብቁ እንዲሆኑ መምህራን በራሳቸው ተነሳሽነት የብቃት መለኪያ ጥያቄዎችን ያዘጋጃሉ። ይህም ዘወትር ቅዳሜ የሚከናወን ነው።ተማሪዎች በሌሎች ዓለማት ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑም በትምህርት ቤቱ ፈረንሳይኛና አረብኛ ትምህርትም ይሰጣል።

ገላን ትምህርት ቤትን ከሌላው የሚለየው እንደ ትምህርት ቤት ቅዳሜ ሙሉ ቀን የሥራ ቀን አድርጎ መሥራቱ ነው።በአቅም ደከም ያሉትን ተቀብሎም ያስተምራል።ይህ ማለት እንደ ሌሎቹ አዳሪ ትምህርት ቤቶች ከፍተኛ ውጤት ያመጡትን ብቻ አይደለም ማለት ነው። የመቀበል አቅሙ እስኪሞላ ድረስ መጠነኛ ውጤት ያመጡትንም ያስተናግዳል።ምክንያቱም ለብዙዎች እድል መስጠት የሚቻለውና የትምህርት ቤቱ ብቃት የሚለካው ደከም ያሉትንም መያዝና ማብቃት ሲቻል ነው ብሎ ያምናል።በዚህም ከመምህራን እስከ አስተዳደር ሠራተኞች ድረስ ዋጋ እየከፈሉ ተማሪዎችን ያግዛሉ፤ ያበቃሉም።

እንደ ሀገርም ይሁን እንደ ከተማ አስተዳደር በመንግሥት የሚደገፍ ትምህርት ተቋም ቢኖር አንደኛው ይህ አዳሪ ትምህርት ቤት ነው።በዚህም እንደ ሌሎች ተቋማት በዓመት የሚከፍለውን አሠራር ዘርግቶ ያከናውናል።ከእነዚህ መካከል ለተማሪዎች የሚሰጠው የዱቤ ሕክምና አገልግሎት አንዱ ነው።

ትምህርት ቤቱ የመቀበል አቅሙ 500 ተማሪ ሲሆን፤ በየዓመቱ ደግሞ ዘጠነኛ ክፍል የሚገቡ 100 ተማሪዎችን ይመለምላል።ለየት የሚያደርገውም አንድ መሠረታዊ ነገር ይህ ነው።በዘንድሮው የትምህርት ዘመን ከትምህርት ቢሮ በወረደለት አቅጣጫ መሠረት በአዲስ አበባ ያሉትን ትምህርት ቤቶች (የግሎችን ጨምሮ) በሙሉ በማወዳደር ተቀብሏል።ቁጥራቸው ደግሞ ከተቀበላቸው 100 ተማሪዎች ውስጥ 20 ተማሪዎች የግል ናቸው።ይህ መሆኑም የግልና የመንግሥቱ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ልምድ ይቀሳሰማሉ በሚል ታስቦበት መሆኑን አቶ ካሳሁን ይናገራሉ፡፡

አቶ ካሳሁን እንደሚናገሩት፣ በገላን አዳሪ ትምህርት ቤት ለተማሪዎች ፈተና ከመቶ ከ70 በታች ማምጣት የተከለከለ ነው።ነገር ግን በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ይህንን ውጤት ያመጡ ካሉ ተለይተው እንዲታገዙ ይደረጋሉ።ለዚህም አንድ መምህር 13 ተማሪዎች ተመድቦለት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያማክራል።በዚሁ መሰረትም፣ በቅርቡ 34 ተማሪዎች ተለይተው የማብቃት ሥራ እየተከናወነ ይገኛል።

የአዳሪ ትምህርት ቤት መኖር በርካታ ነገሮችን የሚቀይር እንደሆነ የሚናገሩት ርዕሰ መምህሩ፤ ተሞክሯቸውን ሲያጋሩ ተማሪዎች ከትምህርት በኋላ ባላቸው ሕይወት ሳይቀር የሚቀየሩበት ነው።ለምሳሌ በአመለካከት፣ በክህሎት፣ በእውቀትና ለሌሎችም ምሳሌ የሚሆኑበት ነው።የትምህርት ስብራት የሆነውን መጠነ መድገም፣ ማቋረጥ የሚሉትን ሀሳቦች የሚቀንስም ነው።

በአዳሪ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በልዩ ክትትልና እንክብካቤ ያድጋሉ።አቅም ባለው መምህር ይታገዛሉ።ሙሉ የትምህርት ቤት መገልገያዎችን ሩቅ ሳይሄዱ በቀላሉ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። ቤተመጻሕፍት፣ቤተ ሙከራ፣ ኮምፒውተሮችንና መምህራኖችን በቀላሉ የሚያገኙበት አጋጣሚ ለአብነት ይጠቀሳል። የመማሪያ አካባቢ ምቹነትም እንዲሁ እንደልባቸው የሚያገኙበትን እድል ይሰጣቸዋል።

ተማሪዎች ተመሳሳይ አስተሳሰብ ካላቸው እኩዮቻቸው ጋር እንዲገናኙ ያስችሏቸዋልም።ይህ ደግሞ ተደጋግፎ በመሥራት የላቀ ደረጃ ላይ ለመድረስ ያስችላቸዋል።በተጨማሪም አቅም የሌላቸው ልጆች የወላጆቻቸውን ችግር እያዩ እንዳይሰቃዩ የሚያደርግም ነው።ይህ ደግሞ ለተማሪዎች የባሕሪ ለውጥ እጅግ አስፈላጊ ሲሆን፤ ለወላጆችም ቢሆን እፎይታን ይሰጣል።

ተማሪዎች ለሕግና መመሪያ ተገዢ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋልም።ከፍተኛው ቦታ ላይ ተወዳድሮ የማሸነፍን ልምድ እንዲቀዳጁ መሰል ትምህርት ቤቶች ወሳኝ ናቸው። ከዚያ ባሻገር ጠንክሮ መሥራት፣ እውነት፣ ራስን መግዛት፣ ሰዓት አክባሪነት፣ መቻቻልን የመሳሰሉ ምርጥ ሰብዓዊ ባህሪያትን እና አመለካከትን ያዳብሩበታል።

አዳሪ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በቡድን የመሥራት ባህልን የሚያዳብሩበት፤ ጥቅሙንም የሚረዱበት፣ እኩል ነፃነትን የሚተገብሩበት፣ ሥራዎችን ጀምሮ መጨረስን ባሕል የሚያደርጉበትም ነው።ባሕላዊ እውቀታቸውን የሚያዳብሩበት፣ መግባባትን የሚያመጡበት (የተግባቦት ክህሎታቸውን የሚያዳብሩበት)፣ ዓለም አቀፍ ጓደኝነትን የሚፈጥሩበት ልዩ ዕድል የሚሰጥም ነው።

እንደ ዋና ርዕሰ መምህሩ ገለፃ፣ አዳሪ ት/ቤት ከሁሉም በላይ እንደሀገር ተወስነው እንዳይቀመጡ የሚያስችል ነው።ለምሳሌ ኮርሶቹ የዓለም አቀፍ ተማሪን የማናገር፣ የማንበብ እና የመፃፍ ችሎታዎችን ያሻሽሉላቸዋል።በዚህ ደግሞ በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ ጭምር ሄደው መማር ይችላሉ።ውጤታማነታቸውም በዚያው ልክ ያድጋል።

የአካቶ ትምህርትን በተመለከተም ሁሉንም ጥቅሞች በአካቶ መማር ሲቻል የሚመጡና የበለጠ የሚዳብሩ እንደሚሆኑ ዋና ርዕሰ መምህሩ ተናግረዋል።በእርሳቸው እምነት ጊዜው የሚፈልገው የአካቶ ትምህርትን ነው የሚል ነው።ጥናቶችም የሚሉት አካታች ትምህርት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ነው።ስለሆነም ትምህርት ቢሮም ሆነ ከተማ አስተዳደሩ ያስብበታል የሚል ተስፋ አላቸው።

በአካቶ መማር ብዙ ጥቅሞች አሉት።አንዱ በሕይወት ዘመናቸው ሊያጋጥማቸው የሚችለውን ፈተና ከአሁኑ አውቀውት ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ያግዛል።ትዳር መሥርቶ ለመኖርም ብዙ ልምዶችን ያስቀስማል።መግባባት ባሕል እንዲሆን ያደርጋል።ማኅበራዊ መስተጋብርን ያጠናክራል።በተጨማሪም በአመለካከት የዳበሩና ተወዳዳሪ የሆኑ ዜጎችን ይፈጥራል።ይህ ሲባል ግን ችግሮቹ መለየትና በሕግ መያዝ ይኖርባቸዋል።በትምህርት ቤቱ ውስጥ ሲማሩ ምን ድረስ መቀራረብ እንዳለባቸውም መወሰን ያስፈልጋል ባይ ናቸው።

በተፈጥሮ ደካማ የሆነ ሰው የለም።በዚህም ልጆች ላይ የምንሠራው ሥራ ከልብ ከሆነ እንደሀገር ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ይቻላል የሚሉት አቶ ካሳሁን፤ ትምህርት ቤቱ የትንሽ ዓመታት ቆይታ ያለው ቢሆንም ብዙዎችን ቀይሯል፤ የተሻለ መንገድንም አሳይቷል።በተቻለ መጠን ስኬታማ የሚያደርገውን ተግባርም አከናውኗል።ያም ሆኖ የፈለግነው ላይ ደርሰናል ብለን አናስብም ይላሉ።«ተቋማችን ተስፋ ያላቸው መጠነኛ ተግባራትን ቢፈፅምም ብዙ ነገሮች ግን ይጎሉታል።ጅምር ላይ ያለ ነው።ነገር ግን፣ ተማሪዎቻችን ተስፈኞች ናቸውና ለብዙ ስለሚታጩ ያንን ለማሳካት እንጥራለን» ሲሉም ጉዟቸው ምን ያህል ሀላፊነት የተሞላው እንደሆነ አብራርተዋል።

የስኬት መለኪያው ዓመት ሳይሆን ሥራ እንደ መሆኑ መጠን የ“ገላን ልዩ የወንዶች ሁለተኛ ደረጃ አዳሪ ትምህርት ቤት” ተሞክሮ ለብዙዎች ትምህርት ይሰጣልና ሌሎችም ቢከተሉት መልካም ይሆናል።

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# ‹‹አሁን አዲሲቷ ኢትዮጵያ እየተገነባች ነው ››

- አቶ ቀጀላ መርዳሳ
የባሕልና ስፖርት ሚኒስትር

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

**የዛሬው የወቅታዊ ዓምድ እንግዳችን በኢትዮጵያ በፖለቲካ ውስጥ ሰፊ ተሳትፎ አላቸው። ይበጀኛል ባሉት መንገድም የፖለቲካ እንቅስቃሴያቸውን ሲያካሂዱ ዘመናትን አልፈዋል። ከሀገር ውጭ እስከ ሀገር ውስጥ ትግል አድርገዋል። ይበጃል ያሉትን የፖለቲካ መስመርና ርዕዮተ ዓለም በመከተል እስከ በረሃ ወርደዋል። በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥሪት ውስጥ የራሴ የሚሉትን ሚና ተወጥተዋል። ከሀገር ውጭ ሆነው ትግል ከማቀጣጠል ይልቅ ሀገሬ ልግባ ብለውም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የአገሪቱ መሪ ከሆኑ በኋላ ከስደት ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል። በአሁኑ ወቅት የባሕልና ስፖርት ሚኒስትር ሆነው በማገልገል ላይ ናቸው-አቶ ቀጀላ መርዳሳ። እኚህ ሚኒስትር ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ቆይታ አድርገዋል።**

**አዲስ ዘመን፡- ከለውጡ ወዲህ ያለችው ኢትዮጵያ እና ከለውጡ በፊት የነበረችዋን ኢትዮጵያ እንዴት ያዩዋታል?**

**አቶ ቀጀላ፡-** ይህ ጥያቄ ሰፊው ነው። መልሱም እንደዚያው ሰፊ ማብራሪያ ይፈልጋል። ታሪክንም ዘለግ ብሎ ማየት ያስፈልጋል። ቀደም ሲል ጀምሮ ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦችና የኃይማኖቶችን መብት የማይከበርባት ሀገር ነበረች። በዚሁ ምክንያትም በርካታ ተቃውሞዎች ነበሩ። በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎችም ግጭቶችም ነበሩ። ሰፊው ሕዝብም ትግል አድርጓል። የቅርብ ጊዜውን እንኳን ብንመለከት የአፄው መንግሥት መውደቅ መንስኤው ይኸው ነው፡

1960ዎቹ የተማሪዎች እንቅስቃሴ በሰፊው ተቀጣጠለ። በዚህ ሂደት 1966 ዓ.ም የንጉሣዊ አገዛዝ ወደቀ። መሬትም ለአርሶ አደር ተብሎ ታወጀ። በዚህ ደርግ የራሱን አዋጅ አወጀ። 1968 ዓ.ም ደርግ አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት ተፈጠረ ብሎ አዋጅ አስነገረ። ይሁንና በዚህ ሥርዓትም የሕዝቦች መብትና ጥያቄ በበቂ ሁኔታ አልተመለሰም ነበር። በዚህም ውስጥ ጥያቄ ያላቸው አካላት የተለያዩ ትግሎች ማድረግ ጀመሩ።

ደርግም ከ10 ዓመት የማስተዳደር ጊዜ በኋላ የፖለቲካ ቅርጽ ለውጥ ቢያደርግም መገፋፋቱ ነበር። በዚህም የተነሳ 1983 ዓ.ም የደርግ ሥርዓትም በትግል ከሥልጣን ተወግዶ የተሻለ ሥርዓት ወደ ስልጣን መጣ። ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ሆነች። በደርግ ጊዜ ይጠራበት ከነበረው ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ወደ ፌደራላዊ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ተቀየረ። ሕገ መንግሥትም ረቀቀ። በዚህም ሕገ መንግሥት ውስጥ ወሳኝ የሚባሉ ሃሳቦች ሰፈሩ። ራስን በራስ የማስተዳደር፣ የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ ዴሞክራሲ በሀገሪቱ እንዲያብብ በሚል አንኳር ሆነው ተቀመጡ። የመንግሥት ሥርዓቱም ብሔር ብሔረሰቦችን ያማከለ እንዲሆን ብሎም ዜጎች በባሕላቸው፣ ቋንቋቸውና መልክዓ ምድራዊ አስተዳደሮችን ታሳቢ ያደረገ ሥርዓት እንዲተገበረም ሆነ።

በዚህ ሂደት ውስጥ አገሪቱ ፌደራላዊ ብትሆንም አንድ ፓርቲ በጉልበት የአገሪቱንም ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊና የበላይነት ተቆናጠጠ። የአገሪቱንም ኢኮኖሚ ተቆጣጥሮ ማስተዳደር ጀመር። ይህ ኃይል ደግሞ ከአንድ ብሔር የመጣ ነው። በዚህ ጊዜም እኩልነት ጠፋ። በብሔሮች ብሔረሰቦችና የሰው ልጆች መካከልም ልዩነቱ ግልጽ ሆነ። በሃብታም እና ድሃ መካከልም ሰፊ ልዩነት መታየት ጀመር። በዚህ ጊዜም የኢትዮጵያውያን ትግል እንደ አዲስ ጀመረ።

ትግሉ ቀጠለ። ወጣቶች መራር ትግል አካሄዱ። በተለይም 2005 ዓ.ም እስከ 2010 ዓ.ም ማዕበል የመሰለ ትግል ተደረገ። በዚህም የኢሕአዴግ ሥርዓት ወደቀ። ኢሕአዴግ ሙሉ ለሙሉ ባይወድቅም ከራሱ ውስጥ በመጣ ኃይል ለውጥ መጣ። በዚህም በመንግሥት ሥርዓት ውስጥም ለውጥ መጣ። ከሚዲያ እና ምሑራን ጀምሮ ከውጭ አገር ወደ ሀገር ውስጥ ገቡ። አዳዲስ ገጽታዎች መታየት ጀመሩ። በሂደት ትክክለኛ የብሔር ብሔረሰቦች



ፎቶ፡- ከፋይል

እውነታ እና ትግል ፍሬ እያፈራ መጣ። ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያ፤ እውነተኛ ፌዴሬሽን እየተጠናከረ፣ የተለያዩ ጠንካራ የልማት ተቋማት እየተፈጠሩ፣ ውስብስብ የፖለቲካ ሂደቶችን ሪፎርም በማድረግ አሁን አዲሲቷ ኢትዮጵያ እየተገነባች ነው።

ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ፖለቲካ የተረሱ ብሔር ብሔረሰቦች በአሁኑ ወቅት በማዕከላዊ መንግሥት እና ፖለቲካ ውስጥ በደንብ እየታዩ ነው። ቀድሞ ውሳኔ ሰጪነትም ላይ አቅም አልነበራቸውም። ይሁንና ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ ትልቅ ለውጥ እየመጣ ነው። የኦሮሞ ሕዝብ ታሪክም በአግባቡ እየተገለፀ ነው። በእርግጥ አሁንም ችግሮች አሉ። ይህን አሁንም የማይቀበሉ እና ዴሞክራሲን የማይፈልጉ አሉ። የኢትዮጵያን መፍረስ የሚፈልጉም አሉ። እነዚህ አካላት ያልገነቧት ኢትዮጵያ አትጥማቸውም። ኢትዮጵያን በመገንባት ሂደት ውስጥ እነርሱ ያላቀበሉት ብረት፤ ያልነኩት ፖለቲካ አይጥማቸውም። ሆኖም ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ብሔር ብሔረሰቦች ከመቼውም ጊዜ በላይ እንደ አንድ ሀገር ዜጋ እየታተሩ ያሉት አሁን ነው ማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ክልሎች ራሳቸውን እያስተዳደሩ መምጣት ለኢትዮጵያ ቀጣይነት አደጋ ነው ብለው የሚያምኑ አካላት አሁንም አሉ። በዚህ ሐሳብ ይስማማሉ?**

**አቶ ቀጀላ፡-** የማኅበረሰብ አንድነት አገር ያጠናክራል እንጂ አያዳክምም። የተደራጀ ማኅበረሰብ ነው ለአገር ዋልታ የሚሆነው። ቤት ሲሠራ ከአንድ ነገር ብቻ አይሠራም። አንዱ ማገር፤ አንዱ ዋልታ፤ ሌላው ሲሚንቶ ሌላው ደግሞ ሌላ እየሆነ ነው የሚገነባው። ሀገርንም ከአንድ ባሕል፣ ቋንቋና ማንነት እና እምነት መገንባት አይቻልም። የሰው ልጅ ሰውነትም ሲገነባ በዚሁ መጠን ነው። የተለያዩ ነገሮች አሉት።

በእርግጥ በአንድ ወጥ የሆነ ነገር ይገነባል ብለው የሚያስቡ አሉ። ይህን ግን አሁን ዓለም ላይ ማግኘት አይቻልም። ይህ ብዙ ዓመት ኢትዮጵያ ውስጥ ተሞክሮ አልተሳካም። ብዙ መንግሥታት ሞክረው አልተሳካላቸውም። ይህ የማይሆንበት ምክንያት አንድ ሰው ዝም ብሎ ሃይማኖቱንና ማንነቱን መተው አይፈልግም። አሁንም ይህን የሚያስቡ አሉ። ሰው እየተማረ ነው። ስለ መብቱ እየጠየቀ ያለበት ዘመን ነው። በዚህ ዘመን በዚህ ደረጃ ማሰብ ያረጀ ያፈጀ አስተሳሰብ ነው። በመሆኑም ይህ ዋጋ አልባ ነው። ይህ አስተሳሰብ ከወደቀ ሦስት አስርተ ዓመታት አልፈዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ለውጥም ከመጣ ወዲህ በሀገሪቱ ብሔር ጠል የሆነ አስተሳሰብ የሚስተዋለው ችግር መነሻው ምንድን ነው ብለው ያስባሉ?**

**አቶ ቀጀላ፡-** ለዘመናት የመጡበት ታሪክ ነው። ምኞታቸው የነበረውም ጥላቻ ነው። ሌላው የተነገራቸው እና የተተረከላቸው ተረትና ምሳሌም የራሱ ሚና አለው። ይህን መሰል ንግግር እና አስተዳደግ አደገኛ ነው። ለዚህም ሁሌ እክል ይፈጥራሉ። በዚህ ውስጥ ያደጉት ናቸው አሁን ችግር እየፈጠሩ ያሉት። ከዚህ በዘለለ ኢትዮጵያን በመታደግ የኦሮሞ ሕዝብ ሚናም ጉልህ ነው። በኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ውስጥ የኦሮሞ ሕዝብና አመራሮች ትልቅ ሚና አበርክተዋል።

ኦሮሞ ከገዳ ሥርዓት ጀምሮ የጠለቀ እውቀት እና የሰዎችን መብት የሚያከብር ሥርዓት የገነባ ነው። አልፎ አልፎ የሚስተዋሉ ብሔር ጠል አስተሳሰቦች አግባብነት የላቸውም። ይህ በሂደት የሚስተካከል ነው። አንዳንድ አስተሳሰቦች ከቅናትና ጥላቻ የመነጩ ናቸው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም ሲልም ግጭቶች ነበሩ። ነገር ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመጣ ብቻ የሚያስመስሉት ሆን ብለው ነው። ይህ ዓላማው በሆነ ብሔር ላይ ያነጣጠረ እኩይ አስተሳሰብ ነው። በታሪክ ውስጥ በርካታ ነገሥታት ላይ የማጥላላትና የንቀት ዘመቻዎች ነበሩ። ለአብነት ልጅ እያሱ ላይ ከፍተኛ ሴራ ይሠራ ነበር። ይህ የሆነው ለለውጥ ስለታገሉ እና ዘር ሐረጋቸውን በመምዘዝ ነው። በሌሎችም ላይ እንዲሁ ይደረግ ነበር። አሁንም እንደ ዘመነ መሳፍንት የሚያስቡ አሉ።

በአሁኑ ወቅም በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ላይ እየተደረገ ያለው የማጥላላት ዘመቻ እና አካሄድ ከዚህ ታሪክ የተቀዳ ነው። በመሆኑም እነዚህ ነገሮች ታሳቢ በማድረግ የሚሠሩ ሰዎች ትዝብት ውስጥ እየወደቁ ነው። ይህ አካሄድ ያለፈበት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ያለው የሚዲያ ዘመቻ ሀገሪቷን ወደ ቀውስ ለመክተት የሚጥር ነው ። በዚህ ላይ ምን ታዘቡ?**

**አቶ ቀጀላ፡-** ሚዲያው በሁለት ዓይነት እንየው። የመንግሥት ሚዲያ በቦርድ የሚመራ እና በመንግሥት ኃላፊዎች ተመድበው የሚመራ ነው። ሌላው ውጭ ሆነው የሚዘወርና የሚፈልጉት የሚያቀጣጥሉ አክቲቪስቶች የሚመራ ነው። ሀገር ውስጥ ሆነው ፈቃድ ከመንግሥት ወስደው መንግሥት ላይ የሚጮኹ አሉ። መንግሥትን መተቸት ችግር የለውም። ግን ሚዲያ የራሱ የሆነ መተዳደሪያ ሕግ አለው። ሁሉም ወሰን አለው። ዴሞክራሲ በራሱ ሕግ አለው። ዴሞክራሲ መብት አለኝ ብሎ ሰውን ማንቋሸሽ አይቻልም። ነፃነት ብሎ የሌላውን መብትና ነፃነት መንፈግ አይፈቀድም። በርካታ የዚህ ሀገር ሚዲያዎች ወሰን አልፈዋል። እነዚህ ምላሳቸው ረጅም ነው። ዝም ብለው ይዘባርቃሉ። በዴሞክራሲ ሀገር ለሕግ ይቀርባሉ። ከአምስት ዓመት ወዲህ የዴሞክራሲ ሥርዓት ይስፋ በሚል ለቀቅ ተደርጓል። ግን ሕዝብን ከሕዝብ የሚጋጭ ሥራ እየሠሩ ነው። በተለይም ብሔር በተለየ ሁኔታ ተለይቶ ይተቻል። ይህን ጥላቻ የሚያስተላልፉት በሕግ መጠየቅ አለባቸው።

በአማራ እና ኦሮሞ ስም ሚዲያ ይዘው የሚያጫጩሁ አሉ። ይህ ግን አብዛኛውን ሕዝብ አይወክልም። ሕዝብ ከሕዝብ ጋር ችግር የለበትም። አብረው የሚኖሩና የሚነግዱ ናቸው። የተጋቡና ማኅበራዊ መስተጋብራቸውም የተጠናከረ ነው። ይህን በዓይናችን እያየን የሚሆነውንም እየተመለከትን ነው። በመሆኑም አንዱ ሕዝብ ከሌላው ጋር ችግር እንደሌለበት መረዳት ይቻላል። በመሆኑም ችግር ፈጣሪዎችን መንግሥት በማየት መለየት አለበት። በዚህ አጋጣሚ መንግሥት የእነዚህን አካላት አደገኛ አካሄድን መንግሥት እንዲያስተካክል ጥሪ ማስተላለፍ እፈልጋለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- መንግሥት በሀገሪቱ ሠላም ለማስፈን በሚደረገው ጥረት በአፍሪካም ሆነ በዓለም መድረክ አድናቆት እየተቸረው፤ እየተመሰገነም ነው። በኦሮሚያ ክልልም በተመሳሳይ ከኦነግ ሸኔ ጋር በሠላማዊ ሁኔታ ለመነጋገር ምን እየሠራ ነው?**

**አቶ ቀጀላ፡-** ጥሩ ነው። ጉዳዩ በሕዝብ እንደራሴዎች ተነስቶ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ምላሽ ሰጥተውበታል። ከምላሻቸው የተረዳነው እና ቀደም ሲልም ስንናገር የነበረው እንደ ኦሮሞ ነፃነት ግንባርም ቀደም ብሎ ሲጠየቅ የነበረው በጠመንጃ ብቻ መነጋገር አዋጭ አይሆንም። የሰላም አማራጭን መከተል ይገባል። ማንኛውንም ችግር ቁጭ ብሎ መነጋገር እና በሠላማዊ መንገድ መፍታት ይመከራል፤ በጣም አዋጭ የሚሆነውም ይህ ነው። ይህ ከምንም አስፈላጊ ነው። ፀብ ወይንም ጦርነት አማራጮችን ሁሉ አሟጦ ተጠቅሞ ምንም አማራጭ ሲጠፋ የሚገባበት የመጨረሻው መጨረሻ አማራጭ ነው። ከምንም በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው ሠላማዊ ንግግር እና ድርድር ነው።

እነዚህ ሸኔ ተብለው የሚጠሩት ያስቀመጡት ነገር አለ ወይ የሚለውን ማወቅ ያስፈልጋል። መንግሥት ከሸኔ ጋር ለመነጋገር ፍላጎት እንዳለው ተናግሯል። በሸኔ በኩል ለንግግር ዝግጁ መሆናቸውን እየሰማን ነው። ነገር ግን ለንግግር ዝግጁ መሆን በራሱ ሌላ ዝግጅት ይፈልጋል። ዝግጅት ሲባል ብዙ ነገር ያካትታል። በመሠረታዊነት ከመንግሥት ጋር ያለው ተቃርኖ ምንድን ነው የሚለው መለየት ይገባል። ያለው ልዩነት ምንድን ነው ብሎ ማየትና ማወቅ ይገባል። መሠረታዊ የፖለቲካ ልዩነቶች ምንድን ናቸው ብሎም በጥንቃቄ እና ጥልቀት ማየት ተገቢ ነው።

በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ የመንግሥትን እና የራሳቸው ልዩነት ማወቅና ማሳወቅ ላይም ግልጽ የሆነ አካሄድ መኖር አለበት። ከአመራር አኳያ ደግሞ እነዚህን ችግሮች ቁጭ ብሎ በመነጋገርና በመወያየት እልባት የሚሰጥ መኖር አለበት። ምናልባት በሚዲያ የሚታወቁና ጥቂት በስም የሚታወቁ ግለሰቦች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ ሰዎችን ብቻ ማነጋገር በቂ ላይሆን ይችላል። በእርግጥ የተበታተኑ ናቸው። በመሆኑም እነዚህን አካላት አንድ ላይ ሰብስቦ መነጋገር ላይ ፈተናዎች ይገጥመናል። እንኳስ በተበታተነ ደረጃ ያሉትን ቀርቶ በተደራጀ ሁኔታ ያሉት እንኳን ይህንን ሃሳብ እቀበላለሁ፤ አልቀበለውም በሚል እሰጣ እገባ አለ። ሌላው ቀርቶ እኛ ወደ አገር ውስጥ ስንገባ አንገባም ብለው የቀሩ አሉ። የተወሰኑ ግለሰቦች ሰላማዊ ትግል ብለው የቀሩት የድርጅቱ አካል ነበሩ።

አሁን ያሉት አመራሮች ቀደም ሲል ከነበረው

# ወቅታዊ



**በሌሎች ሀገራት ተፅዕኖ ስር ወድቀን፤ በልመና ስንዴ እየኖርን እና በጦር መሣሪያ እየተጋደልን መኖር ሳይሆን የሰለጠነች እና ራሷን የቻለች አገር መኖር አለባት**

ደከም ያሉ ናቸው። ስለዚህ እነዚህ የተበታተኑትን ሰብሰብ አድርጎ ማወያየት ይገባል። ወይንም ከእነርሱ ሰው ተመርጦ የሚወያይና ዲፕሎማት የሆነ ሰው ሊኖራቸው ይገባል። በመሆኑም ተወካዮቻቸውን በግልጽ ማሳወቅና መወያየት ይጠበቅባቸዋል። በመሆኑም እነዚህ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለባቸው። ከጦርነት ትግል ወደ ሰላማዊ ሁኔታ መምጣት አለባቸው። እኔም ይህን እደግፋለሁ።

መንግሥት ከሸኔ ጋር ለመነጋገር ፍላጎት ማሳየቱ የሚበረታታ ነው። ይህን በመልካም ነገር እንወስዳለን። ቀድሞም ስንወተውት የነበረው ይህንኑ ነው። ለጦርነት ትግል አሁን ጊዜው አይደለም። ጂኦ ፖለቲክሱም አመቺ አይደለም። እየተጋጨን ያለው ከማን ጋር ነው የሚለውንም ማየት ያስፈልጋል። አፈሙዝ ለማንገብ በመሬት ላይ ያለው ሐቅ ምንድን ነው ብሎ ማየት ይገባል። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ጠመንጃ ማንገት አያስፈልግም። አሁን ሥልጣን ላይ ካለው መንግሥት ጋር በመናበብ ሀገሪቱን ማገዝ ይገባል። የተበላሸውን አብሮ ማስተካከልም ይቻላል በሚል ነበር ወደ ሀገር የመጣነው።

በመሆኑም ወደ ሰላማዊ መንገድ በመምጣት የኦሮሞ ሕዝብን ከሰቆቃና ችግር መታደግ ይገባል። የኦሮሞ ሕዝብ ከባድ ችግር ውስጥ ነው። በደርግም ሆነ በቀደመው ሥርዓት ሁለት የሚዋጉ አካላት እርስ በእርስ ይዋጋሉ እንጂ እንደ አሁኑ ቤት ንብረት አይቃጠልም ነበር። ሸኔዎች የኦሮሞን ሕዝብ ማዕከል አድርገው መዋጋታቸው አግባብ ባለመሆኑ፤ እንዲሁም ጫካ ያሉት ሕዝብን ላልተፈለገ መከራ መዳረጋቸውን ተገንዝበውና አስፈላጊ አለመሆኑን በመረዳት የመንግሥትን አክብሮታዊ ጥሪ መጠቀም አለባቸው። ይህ ጊዜ ስለሚያልፍም በአግባቡ መጠቀምና ወደ ሰላም መምጣት አለባቸው የሚል መልዕክትም አለኝ። ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ መፍታትም የሚመከር የዘመኑ አካሄድ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በቀጣይ ምን ዓይነት ኢትዮጵያን ማየት ይፈልጋሉ?**

**አቶ ቀጀሳ፡-** ወደድንም ጠላንም የአገሪቱን ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በአንድነት ያስተሳሰረ ገመድ አለ። ታሪክ እና ባሕል አጋምዶናል። አብዛኛው ደግሞ ሥሪታችን አንድ ነው። ውልደታችውም አንድ ነው። ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሆና የሰው መብት የሚከበርባትና ብሔር ብሔረሰቦች ራሳቸውን የሚያስተዳድሩባት ብሎም ፌደራላዊት ሀገር ሆና በጋራ ማስተዳደር የሚችሉበት ወንድማማችነት የነገሰባት ኢትዮጵያን እመኛለሁ። በነፃነት የተሞላች ኢትዮጵያን ማየትና የብሔሮችና ብሔረሰቦች መብት የሚከበርበት አገር መሆን አለባት። ሕግና ሕግ ብቻ የሚያከብር የሚኖርባት ሀገር እንድትሆን ምኞቴ ነው። በሌሎች ሀገራት ተፅዕኖ ስር ወድቀን፤ በልመና ስንዴ እየኖርን እና በጦር መሣሪያ እየተጋደልን መኖር ሳይሆን የሰለጠነች እና ራሷን የቻለች አገር መኖር አለባት።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ቀጀሳ፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።


## በጉምሩክ ኮሚሽን አ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የተያዙና የተወረሱ የልዩ ልዩ ዕቃዎች እና ተሽከርካሪዎች ሽያጭ ማስታወቂያ ቁጥር 40/2015

አዲስ አበባ ቃሊት ጉምሩክ ቅጽ/ቤት የተተው፣ የተወረሱ እና በኮንትሮባንድ ተይዘው የሚገኙ የተለያዩ ንብረቶችን (ተሽከርካሪዎችን ማሽነሪዎች ሞባይሎችን፣ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን የተለያዩ የተዘጋጁ አልባሳት እና ሌሎች የተለያዩ ዕቃዎችን) ባለበት ሁኔታ እና ቦታ በግልፅና በሃራጅ ጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል ከዚህ በታች በቅፁ በተጠቀሰዉ ቀንና ሰዓት ለጨረታ የሚቀርቡ ንብረቶች ዝርዝር መረጃ ተዘጋጅቶ ከሀሙስ ሚያዝያ 12 ቀን 2015 ዓም ጀምሮ ለተጫራቾች በሚቀርብ የጨረታ ሰነድ ላይ የሚታወቅ መሆኑ እንገልጻለን፡:

በመሆኑም

1. በቅርንፍ ጽ/ቤታችን በጨረታ በቀረቡት ዕቃዎች ላይ ለመወዳደር የሚፈልግ ማንኛውም በርፉ የፀና የንግድ ፍቃድ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፍኬት እና የዘመኑን ግብር የከፈለ ስለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት የተሰጠ ማስረጃ ሰነዶች ኮፒ እና የጨረታ ማስከበሪያ ቼክ ወይም (C.P.O) ከመጫረቻ ሰነዱ ጋር አያይዞ በኢንቮሎፕ ወይም በፖስታ ለጨረታ በተዘጋጀዉ ሳጥን ዉስጥ ማስገባት የሚኖርበት ሲሆን ለሃራጅ ጨረታ ደግሞ ከጨረታ አንድ ቀን በፊት ይዞ ማስመዝገብ ይኖርበታል።
2. የሚሸጠው ዕቃ ተሽከርካሪ ከሆነ ማንኛውም ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ኢትዮጵያዊ በተቁ 1 የተገለፁ ቅድመ ሁኔታዎቹን ማሟላት ሳያስፈልገው የጨረታ ማስከበሪያ ቼክ ወይም (CPO) ከመጫረቻ ሰነዱ ጋር አያይዞ በኢንቮሎፕ ወይም በፖስታ በማሸግ ለጨረታ በተዘጋጀዉ ሳጥን ዉስጥ በማስገባት በጨረታው ሊሳተፍ ይችላል።
3. ተጫራቾች የግልጽ ጨረታውን ሠነድ ከሀሙስ ሚያዝያ 12 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ዘወትር በስራ ሰዓት የማይመለስ ብር 100.00 (አንድ መቶ ) (መክፈል በቅ/ጽ/ቤቱ በመገኘት የጨረታ ሠነዱን መግዛት የሚችሉ ሲሆን የሃራጅ ጨረታውን ደግሞ በተመሳሳይ ቀንና ሰዓት በነጻ ማግኘት ይችላሉ።
4. በግልፅ እና በሃራጅ በጨረታ ለመሳተፍ ተጫራቾች ለሚወዳደሩባቸዉ ዕቃዎች የሰጡትን ዋጋ አምስት በመቶ (5) ለጨረታ ማስከበሪያ ቼክ (CPO) በቅ/ፅ/ቤቱ አድራሻ ስም በባንክ አሰርተዉ ማስያዝ ይኖርባቸዋል።
5. ለተሽከርካሪ ሀራጅ ጨረታ እና የዕቃ ሐራጅ - ጨረታ ላይ ለመሳተፍ ለእያንዳዱ ተሽከርካሪ እና ለሚወዳደሩባቸዉ ዕቃዎች ብር 100,000.00 የጨረታ ማስከበሪያ ቼክ (CPO) ተጫራቹ ማስያዝ አለበት።
6. ተጫራቾች በሚከተለው የጨረታ ቀናት (ስኬጁል) መሰረት መጫረት ይችላሉ።

| ተ.ቁ | የቅ/ጽ/ቤቱ ስም | የጨረታው አይነት | የንብረት መመልከቻ ቀን የጨረታ ሰነድ ከወሰዱ ቀን ጀምሮ | የጨረታው የመዝገቢያ እና የመክፈቻ ቀንና ሰዓት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አ.አ ቃሊቲ ሃራጅ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት | ሃራጅ | እስከ 16/08/2015 | ሚያዝያ 17/08/2015 4:00 ሰዓት ጀምሮ ይካሄዳል። |
| | | ግልፅ | እስከ 17/08/2015 | ሚያዝያ 18/08/2015 3:45 ተዘግቶ በዚያውኑ ቀን 4:00 ሠዓት ይከፈታል። |

7. የጨረታው መክፈቻ ቦታ-ኢአ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ ጽ/ቤት የሚካሄድ ሲሆን ጨረታው ተጫራቾች /ህጋዊ ወኪሎቻቸው/ ባሉበት ወይም በታዛቢዎች ፊት ይከፈታል
8. ለጨረታው አሸናፊ ተጫራቾች ለጨረታው ዋስትና ያስያዙት (CPO) ከሚከፍሉት ዋጋ የሚታሰብላቸው ሲሆን ለተሸናፊ ተጫራቾች ደግሞ የጨረታው ውጤት ከተገለፀ በ3 የስራ ቀናት ውስጥ ተመላሽ ይደረግላቸዋል።
9. አሸናፊ ተጫራቾች ማሸነፋቸውን ከተገለፀላቸው ቀን ጀምሮ በ5 ቀናት ውስጥ ያሸነፉበትን ገንዘብ ገቢ በማድረግ ዕቃውን ማንሣት ይኖርባቸዋል:፡
10. ከላይ በተ/ቁ 8 በተገለፁት ቀናት ዉስጥ ክፍያዉን ገቢ ያላደረጉ እና ንብረቱን ተረክበው ያልወሰዱ ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበርያ ያስያዙት እና ለንብረቱ የከፈሉት ዋጋ ለመ/ቤቱ ገቢ ሆኖ ዕቃው በድጋሚ ለሽያጭ ይቀርባል
11. መ/ቤቱ ጨረታዉን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው

**ስተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር**

## በጉምሩክ ኮሚሽን አ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

# ዓለም አቀፍ

## በሱዳን በተነሳው ግጭት 56 ሰላማዊ ሰዎች መገደላቸው ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በሱዳን ለስልጣን ሽሚያ በአገሪቱ ጦር እና በልዩ ኃይል ሚሊሻ አባላት መካከል የሚደረገው ግጭት ቀጥሎ ቢያንስ 56 ሰላማዊ ሰዎች መገደላቸው ተነገረ።

የሱዳን ጦር ኃይል እና ራፒድ ሰፖርት ፎርስ ተብሎ የሚጠራው ፈጥኖ ደራሽ ልዩ የሚሊሻ ኃይል በሱዳን መዲና ካርቱም ፕሬዚዳንታዊ ቤተ መንግሥት፣ ብሔራዊ ቴሌቪዥን ጣቢያ እና ወታደራዊ ማዘዣ ጣቢያዎችን ለመቆጣጠር ውጊያ ሲያደርጉ ቆይተዋል።

ቅዳሜ ሌሊት ለእሁድ አጥቢያ በሁለቱ ኃይሎች መካከል የሚደረገው ውጊያ ቀጥሎ ስለመካሄዱ ነዋሪዎች ገልጸዋል።

በመዲናዋ ካርቱም 17 ሰላማዊ ሰዎችን ጨምሮ 25 ሰዎች መገደላቸውን አንድ የዶክተሮች ስብስብ ቡድን ገልጿል። በአጠቃላይ በመላ አገሪቱ ቢያንስ 595 ሰዎች ተጎድተዋል ብሏል ይህ ኮሚቴ። በሱዳን ከተገደሉት መካከል ሦስት የዓለም ምግብ ድርጅት ሠራተኞች መሆናቸው ተገልጿል።

ፈጥኖ ደራሽ ኃይል፣ ወደ አገሪቱ ጦር ስለሚቀላቀልበት ሁኔታ እንዲሁም ኃይሉን ማን ይመረዋል በሚለው ጉዳይ አለመግባባት ተፈጥሮ ባለፉት ቀናት ውጥረት ሰፍኖ ነበር። ከካርቱም በተጨማሪ አማዱርማን፣ ባህሪ እና ፖርት ሱዳን ግጭት እንዳላ የዓይን እማኖች ገልጸዋል።

ቅዳሜ እለት ግጭቱ ከጀመረ በኋላ እርስ በርስ የሚጣረሱ መግለጫዎች ከተዋጊዎቹ በኩል ሲወጡ ነበር።

ፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ በካርቱም የሚገኘውን አየር ማረፊያ፣ ብሔራዊ ቴሌቪዥን ጣቢያ፣ ጦር ማዘዣ ስፍራዎች እንዲሁም ቁልፍ ድልድዮችን ተቆጣጥሬያለሁ ይላል።

ጦሩ በበኩሉ የጦር ጀቶችን በመጠቀም የፈጥኖ ደራሽ ልዩ ኃይሎች ጦር ሰፈርን መምታቱን ገልጾ፤ ቁልፍ የሚባሉ ቦታዎችን ተቆጣጥሬ እገኛለሁ ብሏል።



ጀነራል መሐመድ ሐምዳን ዳጋሎ

የአብደላ ሃምዶክ ሲቪል አስተዳደር በመፈንቅለ መንግሥት ከስልጣን ከተወገደ በኋላ አገሪቱ ከእአአ 2021 ጀምሮ በሉዓላዊ ምክር ቤት አማካይነት በጦር ጀነራሎች ስትመራ ቆይታለች።

የአገሪቱ ጦር አዛዥ ጀነራል አብደል ፈታህ አል-ቡርሃን የሉዓላዊ ምክር ቤቱ ዋነኛ ሰው ሲሆኑ፤ የፈጥኖ ደራሹ ልዩ ኃይል አዛዥ የሆኑት ጀነራል መሐመድ ሐምዳን ዳጋሎ ደግሞ ምክትል ናቸው።

በሱዳን ስልጣን ወደ ሲቪል አስተዳደር ለማሸጋገር በሁለቱ የጦር አመራሮች መካከል አለመግባባት ተፈጥሮ ቆይቷል።

ስልጣን ለሲቪል አስተዳደር ሲሸጋገር የልዩ ኃይል አባላቱ ወደ አገሪቱ ጦር መቀላቀል አለባቸው በሚለው ከስምምነት ቢደረስም ሁለቱ የጦር ጀነራሎች መቼ በሚለው ሊግባቡ አልቻሉም።

ጀነራል አል-ቡርሃን የሚሊሻ አባላቱ በሁለት ዓመት ውስጥ ወደ አገሪቱ ጦር መግባት አለባቸው ሲሉ ሄምቲ በሚለው ቅጽል ስማቸው የሚታወቁት ጄኔራል ሞሐመድ



ጀነራል አብደል ፈታህ አል-ቡርሃን

ሐምዳን ዳጋሎ ግን የሚመሩት ኃይል ጦሩን የሚቀላቀለው ከ10 ዓመት በኋላ ነው ይላሉ።

ታዲያ ለቀናት ውጥረት ነግሶ ከቆየ በኋላ በሁለቱ ኃይሎች መካከል ከትናንት በስቲያ ግጭት ተቀስቅሷል።

ጀነራል አል-ቡርሃን በአገሪቱ ጦር ላይ ክህደት ተፈጽሟል ሲሉ ሄምቲ ደግሞ ሕግ እያስከበርን ነው ይላሉ።

100 ሺህ አባላት ያሉትን ኃይል የሚመሩት ሄምቲ በሱዳን እጅግ ጠንካራ ተጽእኖ ፈጣሪ የሚባሉ ግለሰብ ናቸው። ሄምቲ የሚመሩት የሚሊሻ ቡድን በከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት የሚወነጀል ሲሆን እአአ 2003 በጀመረው የዳርፉር ግጭት አማጺዎችን ተዋግቷል።

ከዳርፉር በተጨማሪ የሄምቲ ጦር በሊቢያ እንዲሁም ከሳውዲ መራሹ ኃይል ጎን በመሰለፍ በየመን መዋጋቱን ቢቢሲ ዘግቧል፡፡

የፈጥኖ ደራሽ ሚሊሻ አባላቱ ሜሮዌ ተብሎ በሚጠራ ስፍራ የግብጽ ወታደሮች እጃቸውን ሰጥተዋል ብለው በተንቀሳቃሽ ምስል የተደገፈ ማስረጃ አቅርበዋል።

የግብጽ ጦር ግን የጦር አባላቱ ሱዳን የተገኙት ከሱዳን ወታደሮች ጋር ያጋራ ልምምድ ለማድረግ መሆኑን ገልጾ የጦር አባላቱ ደህንነትን ለማረጋገጥ ከሱዳን ባለስልጣናት ጋር እየተነጋገርኩ ነው ብሏል።

የካርቱም ነዋሪዎቹ ግጭቱ ይከሰታል ብለው እንዳልጠበቁ አንድ ነዋሪ ለቢቢሲ ተናግሯል።

ድንገት የተቀሰቀሰው ግጭት ተማሪዎችን ጨምሮ ከቤታቸው ርቀው ያሉ መንቀሳቀስ እንዳይችሉ አድርጓቸዋል።

ግጭቱ ከተቀሰቀሰ በኋላ ሰላማዊ ሰዎች እራሳቸውን ለመሸሸግ በዋና ጎዳናዎች ላይ ሲሯሯጡ ታይተዋል።

በመዲናዋ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ብረት ለበስ እና ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች ታይተዋል። በካርቱም አየር ማረፊያም በተኩስ ልውውጥ ምክንያት የመንገደኞች አውሮፕላን በእሳት ተያይዟል።

የሳውዲ አረቢያው ሳዑዲ ኤየር ኤርባስ አውሮፕላኑ በእሳት መያያዙን ገልጿል። የሳዑዲ እና የግብጽ አየር መንገዶች ወደ ካርቱም የምናደርገውን በረራ ለጊዜው አቋመናል ያሉ ሲሆን፤ ጎረቤት አገር ቻድ ደግሞ ከሱዳን የሚያዋስናትን ድንበሯን ዘግታለች።

ግጭቱ ከቀሰቀሰ በኋላ ምዕራባውያን አገራት ሁለቱ ኃይሎች ልዩነቶቻቸውን በንግግር እንዲፈቱ ጥሪ አቅርበዋል።

ዩናይትድ ኪንግደም፣ አሜሪካ እና የአውሮፓ ሕብረት ግጭቱ በአስቸኳይ መቆም አለበት ብለዋል። የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ ደግሞ ጀነራል አል-ቡርሃን እና ጀነራል ዳጋሎን በስልክ ማነጋገራቸው ተገልጿል።

በካርቱም ያለው የሩሲያ ኤምባሲም በአገሪቱ ያለው ሁኔታ አሳስቦኛል ካለ በኋላ ሁለቱ ኃይሎች በአስቸኳይ ተኩስ ማቆም አለባቸው ብሏል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድም ኃይሎቹ ግጭት አቁመው ወደ ንግግር እንዲመለሱ ጠይቀዋል።

**ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር**
**በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም**

## ተግባር ተኮር የጎልማሶች መሠረታዊ ትምህርት በከምባታ ጠምባሮ ዞን

**በስጥሻቸው ልዑልሰገድ**

ባለፉት አመታት በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን የተማረ የሰው ሀይል መጨመርና የማህበረሰቡን አኗኗር ለመለወጥ እንዲያስችል የጎልማሶች መሰረታዊ ትምህርት ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል:: የከምባታ ጠምባሮ ዞን እየተሰጠ ባለው በጎልማሶች መሠረታዊ ትምህርት እና በተለያዩ ሙያዊና የእደጥበብ ሥልጠናዎች የበርካታ ጎልማሶችን የአኗኗር ዘዴና ህይወት የሚያሻሽሉ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛል::

የዞኑ የትምህርት መምሪያ ኃላፊ አቶ አምባዬ አበራ እንደሚሉት፤ በዞኑ 578 የማህበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላት መኖራቸውንና ከነዚህም መካከል የሺንሽቾ ከተማ የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከልን ጨምሮ አምስት በአርአያነት (በሞዴልነት) ተወስደው ውጤታማ ሥራዎች እየተሠሩባቸው ያሉ ማዕከላት እንዳሉ ይጠቁማሉ::

የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ በተማሪ ላይ ብቻ የሚሰራ ስራ ውጤታማ ሊሆን አይችልም የሚሉት ኃላፊው፤ "ማህበረሰቡ በራሱ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሊሳተፍ ይገባዋል:: ከተማረ ቤተሰብ የሚመጡ ተማሪዎች የተሻለ ተማሪ የመሆን እድላቸው ከፍተኛ መሆኑ በጥናትም የተረጋገጠ ነው:: የጎልማሶች ትምህርትም ሲጠና ይህንን መሰረት ተደርጎ ነው::" ይላሉ::

በዞኑ በ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በጎልማሶች መሰረታዊ ትምህርት 34 ሺህ 94 ተማሪዎች ተመዝግበው በመማር ላይ ሲሆኑ፤ በተያዘው አመት የጎልማሶች ትምህርት



አቶ አምባዬ አበራ

የሚሰጥባቸውን ጣቢያዎችን ሞዴል ጣቢያ ለማድረግ እየተሰራ ነው:: የጎልማሶች መሰረታዊ ትምህርት የሚከታተሉ ተማሪዎች የማንበብ የመፃፍና የማስላት ክህሎትን ከመማር ባሻገር ለሶስት ወር ስልጠና በመውሰድ በመኖሪያ አካባቢያቸው የእንጨት ስራ እና የሽመና ስራን ጨምሮ የተለያዩ ስራዎችን ይሰራሉ::

ከሁለት አመታት በፊት በዞኑ የተሰጠውን የትምህርት ብርሃን ምዘና ወስደው ያለፉ 15 ሺ 028 ጎልማሶች መሆናቸውንና ከነዚህም መካከል የተወሰኑት መደበኛ ትምህርት ገብተው ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ሁኔታዎች እየተመቻቸላቸው ነው:: አብዛኛዎቹ በማዕከላቱ የወሰዱትን የተለያዩ የእጅና የእደጥበብ ሙያዎችን መሠረት በማድረግ ወደ መረጡት ሥራ እንደተሠማሩ ጨምረው የሚያስረዱት ኃላፊው፤ በዚህ አመት በዞን ደረጃ ሁሉንም ማዕከላት ከማጠናከር ጎን ለጎን እንደ ሺንሽቾ ከተማ የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከል ያሉ በአርአያነት የሚጠቀሱ በርካታ ማዕከላትን ለማፍራት በትኩረት እየተሠራ መሆኑንም ይገልፃሉ::

የማዕከሉ አስተባባሪ የሆኑት አቶ ማትዎስ ጡሜቦ፤ ማዕከሉ መሠረታዊ ትምህርት እና የተለያዩ የእጅና የእደጥበብ ሙያዎችን ከማሰልጠን በተጨማሪ ንብ ማነብን፣የዶሮ እርባታን፣እንስሳት እርባታን፣የእንስሳት መኖ ልማትን፣የጓሮና የመስኖ እርሻ አዘገጃጀትና እንክብካቤን በተግባር ወይም ሠርቶ ለማሳየት የሚረዳ ከ24 ሄክታር በላይ የመሬት ይዞታ ያለው መሆኑን ጠቅሰው፤ ለአብነት ያክል በዘንድሮ የበጋ ወቅት በባለደርሻ አካላትና አጋር ድርጅቶች በመታገዝ አቅራቢያው ካለ ወራጅ ወንዝ በጄኔሬተር ውሃ በመሳብ ከአስር ሄክታር በበለጠ መሬት ላይ ስንዴ ማምረታቸውን ይናገራሉ::

አስተባባሪው እንደሚናገሩት፤ የከተማ ግብርና በደንብ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የግብርና ባለሙያዎች የከተማ ግብርና ላይ መሳተፍ የሚፈልጉ ጎልማሶች ስልጠና ወስደው እንዲሰሩ ሰፊ እድል ይሰጣል:: ጎልማሶች የተማሩትን በተግባር ሰርተው የሚያሳዩበት ማሳ የተዘጋጀ ሲሆን፤ በአመቻቾቻቸው ክትትል የተማሩትን በተግባር ሰርተው ካሳዩ በኋላ በቤታቸው ጓሮ የከተማ ግብርናን ተግባራዊ ደርጋሉ:: የጎልማሶች ትምህርትን ከመከታተል ባለፈ ጎልማሶች በማዕከሉ የገንዘብ ቁጠባ ይጀምራሉ፣ እናም እንደየፍላጎታቸው በግልም ሆነ በቡድን የተለያዩ ስራዎች ላይ ይሰማራሉ::

በ1980 ዓ.ም መቋቋሙንና ባደረገው አስተዋጽኦም ዞኑንና ክልሉን በመወከል የተለያዩ ጊዜያት የተሸለመ መሆኑን የሚጠቅሱት አቶ ማትዎስ፤ ማዕከሉ በዚህ ደረጃ ውጤታማ እንዲሆን የራሳቸውን አስተዋጽኦ ያበረከቱትን በየደረጃው ያሉ ባለድርሻና አጋር አካላት አመስግነዋል::

አመቻች አባይነሽ ዳንኤል፤ በማዕከሉ ባደረገችው የሁለት አመት ቆይታ ጎልማሶች ምንም ሳያውቁ ወደ ማዕከሉ መጥተው ቁጥርና ፊደል ከመለየት አልፈው ማንበብና ማስላት ሲችሉ ለትምህርት የነበራቸው መልካም ያልሆነ አመለካከት ተቀይሯል:: ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት የመላክና በትምህርት ውጤታማ እንዲሆኑም የመከታተልና የመደገፍ ተነሳሽነታቸው የጨመረ መሆኑን ትገልጻለች::

አመቻች አባይነሽ፤ በማዕከሉ ለጎልማሶች ቀጣይ ህይወት የሚጠቅሙ የተለያዩ የሙያና እደጥበብ ሥልጠናዎች እንደሚሰጡ ጠቅሳ፤ ለማሳያነትም ሽመናን፣ ልብስ ስፌትን፣ የእንጨት ሥራ ስልጠና በማእከሉ ለጎልማሶች ይሰጣል::


ወረታ ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ኃላ.የተ.የግ.ማህበር ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች
መልካም የትንሳኤ በዓል እንዲሆን እየተመኘ
ከዚህ ቀደም ከሚያቀርባቸው ምርቶች በተጨማሪ
የቮልቮ ግሩፕ አካል የሆነውን
SDLG Loader
ወደ ሀገር ውስጥ አስመጥቶ በገበያ ላይ ማዋሉን ይገልፃል፡፡
Wereta International Business Plc
ወረታ ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ኃላ.የተ.የግ.ማህበር
SDLG
Reliability in Action
L956F
WHEEL LOADER
ያስመጣናቸው ምርቶች ውስን ስለሆኑ
ቀድመው ይግዙና ተጠቃሚ ይሁኑ፡፡
መልካም በዓል!
ምንጊዜም ልናገለግልዎ ዝግጁ
ነን ይደውሉልን ወይም
ይምጡና የሽያጭ
ቢሮዎቻችንን ይጎብኙ!
አድራሻ፡-
ቦሌ መድሐኒዓለም
ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት ኒው
ብራይት ታወር ህንፃ 3ኛ ፎቅ ቢሮ
ቁጥር 301 - 307
ስልክ 011663-00-20፣
011 6 566767
0903-30-30-30
0966-26-99-78
0912-36-03-56
ቅርንጫፍ መ/ቤት፡ ቃሊቲ ሸዋ
ዳቦ አካባቢ ስልክ
0911-02-08-50
EFQM
Congratulations SDLG for winning
EFQM Global Excellence Award
One of the top three quality awards in the world
SDLG
Member of the Volvo Group

# ስፖርት




# በዛሬው የቦስተን ማራቶን ለድል የሚጠበቁ ኢትዮጵያውያን

**ቦጋለ አበበ**

በዓለም አትሌቲክስ የወርቅ ደረጃ የተሰጠው ታላቁ የቦስተን ማራቶን ዛሬ ለ127ኛ ጊዜ ይካሄዳል። ከመቶ በላይ አገራት የተውጣጡ ከሠላሳ ሺ በላይ ተወዳዳሪዎች በሚፋለሙበት በዚህ ውድድር እንደተለመደው የኢትዮጵያና የኬንያ አትሌቶች ለድል ይጠበቃሉ፡፡ በተለየ መልኩ ግን ሦስት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የአትሌቲክስ አፍቃሪዎችን ትኩረት መሳብ ችለዋል።

የ2022 የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ዩጂን ኦሬጎን ላይ በድንቅ አጨራረስ የማራቶን የወርቅ ሜዳሊያውን ያጠለቀችው ጎይተቶም ገብረሥላሴ በዛሬው የቦስተን ማራቶን ትኩረት መሆኗ የተጠበቀ ነው። የሃያ ስምንት ዓመቷ የወቅቱ የማራቶን ሻምፒዮን ለመሆን የበቃችው አርባ ሁለት ኪሎ ሜትሩን 2:18:11 በሆነ ሰዓት በማጠናቀቅ እንደነበረ ይታወሳል። ጎይተቶም በ2021 የበርሊን ማራቶን ማሸነፏ የሚታወስ ሲሆን ከዓመት በኋላም በ2022 የኒውዮርክ ማራቶን ሦስተኛ ሆና ማጠናቀቅ ችላለች። ይህም የማራቶን ስኬቷ በዛሬው የቦስተን ማራቶን በርካቶች ዓይናቸውን እንዲጥሉባት አድርጓል።






**አትሌት ጎይተቶም ገብረሥላሴና ሌሊሳ ዴሲሳ በዛሬው ቦስተን ማራቶን ለድል ታጭተዋል፣**

በማራቶን የኢትዮጵያ የሴቶች ክብረወሰን በመስበር 2፡14.58 ሰዓት ያስመዘገበችው ሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት አማኔ በሪሶ በዛሬው የቦስተን ማራቶን ትኩረት የተሰጣት ሆናለች። ይህች የሠላሳ ስድስት ዓመት አትሌት እኤአ በ2016 ይህንኑ የቦስተን ማራቶን ማሸነፍ የቻለች ሲሆን፣ እኤአ በ2012 እንዲሁም በ2016 የቺካጎ ማራቶንን በድል ፈጽማለች። በተጨማሪም እኤአ በ2009 እና 2010 የፓሪስ ማራቶንን አከታትላ ማሸነፍ የቻለች ሲሆን በርቀቱ ያላት ደማቅ ስኬት ዛሬ ለድል እንድትጠበቅ ምክንያት ሆኗል። ሕይወት ገብረማርያምና አባብል የሻነህም በዛሬው ቦስተን ማራቶን ድል ለመጎናፀፍ ትግል የሚያደርጉ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ናቸው።

የሁለት ጊዜ የኦሊምፒክ የ5ሺ ሜትር የብር ሜዳሊያ አሸናፊ የሆነችው ኬንያዊቷ ሄለን ኦብሪ በዚህ መድረክ እንደምትሳተፍ ማረጋገጫ መስጠቷን ተከትሎ በኢትዮጵያውያንና ኬንያውያን መካከል የሚደረገውን ፉክክር በጉጉት እንዲጠበቅ አድርጎታል፡፡ ኦብሪ በ12 ዓመት የፕሮፌሽናል አትሌትነት ሕይወቷ ይህ ሁለተኛ የሙሉ ማራቶን ውድድሯ ሲሆን፣ ባለፈው ዓመት በኒውዮርክ ማራቶን ለመጀመሪያ ጊዜ ተሳትፋ በ6ኛነት ማጠናቀቋ ይታወሳል፡፡ ከሦስት ሳምንታት በፊት ደግሞ ዛሬ በምትፎካከርበት ቦስተን በግማሽ ማራቶን ተወዳድራ የቦታውን ክብረወሰን 1፡07.21 በማሻሻል ጭምር ማሸነፏ ይታወሳል፡፡

በወንዶች መካከል በሚደረገው ፉክክር የሠላሳ ሶስት አመቱ ኢትዮጵያዊ አትሌት የአሸናፊነት ቅድመ ግምቶችን ማግኘት ችሏል። ይህ አትሌት ለቦስተን እንግዳ አይደለም፣ሌሊሳ ዴሲሳ ይህን ውድድር ሁለት ጊዜ በማሸነፍ ቦስተን ላይ ትልቅ ዝና አለው። የመጀመሪያ ድሉን እኤአ 2013 ላይ ማሳካቱ የሚታወስ ሲሆን፣ ከሁለት ዓመት በኋላም 2015 ላይ ተመሳሳይ ድል በእጁ አስገብቷል። ሌሊሳ የመጀመሪያ ድሉን ቦስተን ላይ ባስመዘገበበት ውድድር መጨረሻ የደረሰው የቦንብ አደጋ የሚታወስ ሲሆን እሱም ሜዳሊያውን ቦንብ ፍንዳታ ሕይወታቸውን ላጡ ሰዎች መታሰቢያ እንዲሆን ማበርከቱ አይዘነጋም። ይህም አትሌቱን በቦስተን ከተማ እጅግ ታዋቂና በርካታ ደጋፊዎች እንዲኖሩት አድርጓል። ሌሊሳ እኤአ በ2018 የኒውዮርክ ማራቶንን ከማሸነፉ ባሻገር 2019 ላይ በኳታር ዶሃ የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ወርቅ ማጥለቁ ይታወሳል። ይህ ከብዙ ጥቂት የማራቶን ስኬቱ ሲሆን ዛሬ ለሦስተኛ ጊዜ በቦስተን ማራቶን አሸንፎ የማይረሳ ታሪክ ይፅፋል ተብሎ ተጠብቋል።

በሁለቱም ፆታዎች በቀዳሚነት ያሸነፉ አትሌቶች በነብስ ወከፍ 150 ሺ ዶላር ሽልማት የተዘጋጀ ሲሆን፣ ክብረወሰን ያሻሻሉ አትሌቶች ደግሞ ተጨማሪ 50 ሺ ዶላር ጉርሻ የሚያገኙ ይሆናል። ከ2ኛ-10ኛ ባለው ደረጃ የሚያጠናቅቁ አትሌቶችም ከ75 ሺ እስከ 5,500 ዶላር ሽልማት እንደሚያገኙ ታውቋል።


## Invitation to Bids
## OWEB /NCB/10/2015

1. Oromia Water & Energy Bureau has secured budget from the Government for the procurement of **Supply of Electromechanical equipments for different projects**
2. Therefore, interested eligible bidders are invited to participate

| No | Description of works | Remark |
|---|---|---|
| 1 | Supply of Electromechanical equipments for different projects | |

3. Bids accompanied by bid bond of not less than 1% of the bid price in Ethiopian birr or not More than **500,000** birr in the form of CPO or Bank Guarantee and must be submitted to the above mentioned office.
4. Bid shall be delivered bid documents to Oromia Water and Energy Bureau, 4th floor and Tel. +251-011-5-509622 on or before 11:59 AM 09/05/2023 GC. Bids shall be open at 2:00 PM / 09/05/2023 GC. On the same date in the presence of the bidder's representatives at the office of the Bureau's hall 4th floor.
5. A complete bid documents in English can be purchased from the above mentioned office up on payment of non-refundable fee birr 600 / Six hundred/ by submission of a written application to the address indicated below.
6. Bidders should present renewed license, Registration certificate issued from authorized Ministry, Tax payer certificate, Registration card For VAT & TIN together & copy of ID card.
7. Oromia Water & Energy Bureau reserves the right to reject Bids partial or fully.

**Address: Oromia National Regional State's President Office Compound Oromia Water & Energy Bureau 4th Floor Room left wing No. P.O. Box 8630 Tel. 0115509622, Fax. 0115517756 Bole, Flamingo, In front of Tomy Tower Finfinne/Addis Ababa**

**Oromia Water & Energy Bureau**

## Invitation to Bids
## OWEB /NCB/09/2015

1. Oromia Water & Energy Bureau has secured budget from the Government for the procurement of **Water well drilling & construction of 9(Nine) Bore hole found in west Arsi zones of Oromia.**
2. Therefore, interested eligible bidders are invited to participate lots

| No | Description of works | No. of lots | No of Boreholes |
|---|---|---|---|
| 1 | Water well drilling & construction of 9 Boreholes | 3 | 9 |

3. Bids accompanied by bid bond of not less than 1% of the bid price in Ethiopian birr or not More than 500,000 birr in the form of CPO or Bank Guarantee and must be submitted to the above mentioned office.
4. Bid shall be delivered bid documents to Oromia Water and Energy Bureau, 4th floor and Tel. +251-011-5-509622 on or before 11:59 AM 09/05/ 2023 GC. Bids shall be open at 2:00 PM 09/05/2023GC. On the same date in the presence of the bidder's representatives at the office of the Bureau's hall 4th floor.
5. A complete bid documents in English can be purchased from the above mentioned office up on payment of non-refundable fee birr 600 / Six hundred/ by submission of a written application to the address indicated below.
6. Bidders should present renewed license, Registration certificate issued from authorized Ministry, Tax payer certificate, Registration card For VAT & TIN together & copy of ID card.
7. Oromia Water & Energy Bureau reserves the right to reject Bids partial or fully.

**Address: Oromia National Regional State's President Office Compound Oromia Water & Energy Bureau 4th Floor Room left wing No. PO Box 8630 Tel. 0115509622, Fax. 0115517756 Bole, Flamingo, In front of Tomy Tower Finfinne /Addis Ababa**

**Oromia Water & Energy Bureau**